# የካታኮምቡ ሰማዕት



ከአማረ ማሞ

@A

# የካታኩምቡ ሰማዕት

For more spiritual Book search our official Telegram Channel

@AmharicSpritualBook

በአማረ ማሞ ተተረጐመ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ
የምሥራች ድምፅ የመገናኛ ዘዴች አገልግሎት
ኅትመት መገናኛ ዘዴ ክፍል

ዐዲስ አበባ፥ 2013 ዓ.ም.

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

መጀመሪያ በ1954 ዓ.ም. ታተመ፡፡
ሁለተኛ በ1959 ዓ.ም. ታተመ፡፡
ሦስተኛ በ1960 ዓ.ም. ታተመ፡፡
አራተኛ በ1984 ዓ.ም. ታተመ፡፡
አምስተኛ በ1989 ዓ.ም. ታተመ፡፡
ስድስተኛ በ2008 ዓ.ም. ታተመ፡፡
ሰባተኛ በ2013 ዓ.ም. ታተመ፡፡

ኮምፒዩተር ለቀማና
ጽሑፍ አቀማመጥ:- ፀጌ ወልዴ
አርትዖትና እርማት:- አበበ ከበደ ወርቁ
የልባስ ሥዕል:- ወንድወሰን ገብረ ትንሣኤ

# መግቢያ

«መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያደርሳሉ» የሚል አንድ ጥንታዊ ተረት አለ። በ1952 ዓ.ም. መጨረሻ ግድም ሮምን የጎበኙ ሁሉ የዚህን አነጋገር እውነተኛነት ሳይረዱ የቀሩ አይመስለም።

ከተማይቱም ወደ መቶ በሚጠጉ የልዩ ልዩ አገሮች ሰንደቅ ዓላማዎች አጊጣለች። ከአራቱ ማዕዘን ዓለማት በአየር÷ ባሕርና በየብስ ወደ ሮም የሚጎርፈው ሕዝብ ብዛት ቊጥር ስፍር የለውም። በየማዕዘኑ ወዲህ ወዲያ የሚለው ሕዝብ ብዛት ሲታይ የዓለም ነገዶች ሁሉ «በላለማዊነቱን መዲና» ለመሳለም የመጡ ይመስላል። የዚህ ሁሉ ምክንያት በከተማይቱ ውስጥ የተፈጸመው የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ውድድር ነበር።

ሮም በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ለጐብኝዎችዋ የምታበረክታቸው ብዙ ታሪካዊ ቅርሶች አሉአት። የፈረሱ ሕንፃዎች÷ የወደቁ ዓምዶች÷ የቆሙ ቅስቶች÷ እጅና እግራቸው የማይለይ ሐውልቶች÷ ግሩም የሆኑ አደባባዮችና አብያተ ክርስቲያናት የአያሌ መቶ ዘመናት ታሪካዊ ትዝታ በሰው አእምሮ ውስጥ ይቀሰቅሳሉ። ሮም የታሪክ÷ የጥበብ÷ የታላቅነት÷ የመውደቅና የመነሣት መዲና እንደ ነበረች የቆሙትም ሆነ የፈረሱት ቅሬታዎች ይመሰክራሉ።

አንድ አገር ጐብኝ በሮምና በአንባቢዋ ሊያይ የሚችለው ውበትን ጥበባዊ ትንግርቶችንና ታላቅነትን ብቻ አይደለም። በከተማይቱ ረጅም ታሪክ ውስጥ ብዙ የግፍና የአረመኔነት ተግባሮች በሰዎች ላይ እንደ ተፈጸሙ የሚያስረዱ ብዙ መታሰቢያዎች ይገኛሉ።

ወደ ሮም የሚያደርሱ ብዙ መንገዶች እንዳሉ ሁሉ ከሮም የሚያወጡትም የዚያኑ ያህል ናቸው። ከእነዚህም መካከል በታሪካዊነቱ የታወቀው አፒያ አንቲን የተባለው ጐዳና ይገኛል።

በዚህ ጐዳና በኩል አድርገን አንድ ታታሪካዊ ስፍራ ለመጐብኘት ብዙ ሰዎች በአንድ ረጅም አውቶቡስ ውስጥ ተቀምጠናል። ከሹፌሩና ከጉዞአችን መሪ በስተቀር የቀረነው አገር ጐብኝዎች ነበርን። የጉዞአችን መሪ ድምፅ ማጉያውን አፉ ላይ ደቅኖ በአራት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ያስረዳናል። በመጨረሻም የመንገዱ ርቀት ሳይሰማን ካሰብንበት ስፍራ ደረስን።

ከዚያም የምናውቀውን ቋንቋ ወደሚናገሩት ፍራንሲስካን መነኩሴ ጠጋ ካልን በኋላ÷ ጨለማና ቀዝቃዛ ከነገሠበት ካታኮምብ በሚል ስም ወደ ታወቀው ዋሻ ውስጥ ገብተን ጉብኝታችንን ቀጠልን።

ያስተናብሩን የነበሩትም መነኩሴ የስፍራውን ታሪክ እየዘረዘሩ ያስረዱን ጀመር። ጉብኝቱ አንድ ሰዓት ያህል ፈጀ። በመጨረሻውም ይመሩን የነበሩት መነኩሴ ከዋሻው ውስጥ ወደ ተሠራው መሰብሰቢያ ክፍል እንድንገባ ካደረጉ በኋላ የሚከተሉትን ቃላት ተናገሩ፦ «... እኔ አሁን ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ምክር ልሰጣችሁ አልተዘጋጀሁም። ዳሩ ግን ይህ ያያችሁት ስፍራ ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊ ስሜት በውስጣችሁ የሚፈጥር መታሰቢያ እንደሚሆናችሁ አምናለሁ።»

ያየነው ምን ነበር?

ካታኮምብ በሚል ስም የታወቁት ዋሻዎች ከ100 - 312 ዓ.ም. በክርስቲያኖች ላይ በደረሰው ስደትና መከራ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምዕመናን ከቄሣሮች ማዕበላዊ ቍጣ የሚጠለሉበትና በሰማዕትነትም ሲያርፉ የሚቀበሩበት ስፍራ ነበር። በዚያ በመከራው ዘመን ክርስቲያኖች ከዚህ የምድር ማጎፀን በስተቀር ሌላ መጠጊያ አልነበራቸውም።

በሮም አንባቢ ይህንን የመሰሉ አያሌ ዋሻዎች ይገኛሉ። ዋሻዎቹ ሁሉ ቢቀጣጠሉ ርዝመታቸው ወደ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ይደርሳል ይባላል። በእነዚህ አሠቃቂ በሆኑ ካታኮምቦች ውስጥ እንዲኖሩ የተገደዱት የምዕመናንና የሰማዕታት ሠራዊት ይደርስባቸው የነበረው መከራና ሥቃይ በልብ ወለድ አቀራረብ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተዘርዝሮ ይገኛል።

አንባቢዎችም የስፍራውን ሁናቴና በዚያን ዘመን በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ ይደርስባቸው የነበረውን ስደትና መከራ እንዲረዱት በማሰብ ይህን አንድ ስሙ ካልታወቀ ደራሲ የተጻፈውን «የካታኮምቡ ሰማዕት» የተባለውን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ተርጕሜ ሳቀርብ ደስታ ይሰማኛል።

«የሰማዕታት ደም የክርስቲያንነት ዘር ነው።»

ዐዲስ አበባ 1954 ዓ.ም.

አማረ ማሞ



ኮሎሲዩም

# ኮሎሴዩም

«ለሮማውያን መፈንጠዣ ተጨፈጨፉ»

ሮም ታታላቅ የሆነ በዓል አክብራ የምትውልበት ቀን ነው፡፡ በብዛት የሚቈጠሩ ሰዎች ከየማዕዝናት ሲጐርፉ ይታያሉ፡፡ ካፒቶሊን የተባለውን ኮረብታ አልፎ በሕዝብ አደባባይ፥ በሰላም መቅደስና በጢጦስ ቅስት እንዲሁም በቄሣር ቤተ መንግሥት በኩል የሚወስደውን መንገድ ተከታትሎ የሚርመሰመሰው ሕዝብ ብዛት ይህ ነው አይባልም፡፡ ሁሉም የሚገሰግሰው ኮሎሴዩም በሚል ስም ወደ ታወቀው የስፖርት አደባባይ ነበር፡፡ ይህም ግዙፍ ሕንፃ ከመቶ በላይ በሆኑ በሮቹ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ሊቀበል ቢችልም ፈጽሞ በቃኝን የማያውቅ ነበር፡፡

ሕንጻው ክብ ሆኖ የተሠራ ነው፡፡ ወደ ውስጥ ሲገቡ ለትንግርት የሚታዩ ብዙ ትርእይቶች አሉት፡፡ በመጀመሪያ ሰፊ የሆነው የትርእይት አደባባይ ማዕከላዊ ስፍራውን ይዞ ይገኛል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የመቀመጫ ረድፎች በቁመት ከመቶ ጫማዎች በላይ የሆነውን የሕንፃውን ክብ ግድግዳ ከበውት ሲታዩ ለዓይን ያስደንቃል፡፡ ከዚህም በቀር በማዕከላዊ የትርእይት አደባባይ ዙሪያ በብዙ የሚቈጠሩ የአውሬዎች ማጕሪያ ዋሻዎች፥ የእሥረኞችና የተዋጊዎች መኖሪያ ክፍሎች ይታያሉ፡፡

በዚህ ታላቅ ሕንጻ ውስጥ ገብቶ የታጐረው ሕዝብ በዕድሜም ሆነ በኑሮ ደረጃ የተለያየ ነበር፡፡ ይህን የመሰለ የሕዝብ ትርእይት ከዚህ ቀደም ታይቶ አይታወቅም፡፡ የሕዝቡ ብዛት ተመልካችን በአድናቆት ላይ ይጥላል፡፡

በሕንፃው ውስጥ የተሰበሰቡት ከመቶ ሺህ በላይ የሆኑት ሰዎች አንድ ዓይነተኛ ዓላማና ፍላጎት ነበራቸው፡፡ እያንዳንዳቸውን ወደዚህ ስፍራ እያነፈነፉ እንዲመጡ ያደረጋቸው የደም ፍላጎታቸውን ለማርካት ነበር፡፡ ስመጥሩ የሆነውንና ጥንታዊውን የሮምን ሥልጣኔና ገናናነት ካስነወሩት ነገሮች አንዱ ይህን የመሰለው የደም ጥማት በሕዝቦችዋ ዘንድ መታየት ነበር፡፡

በዚህ ስፍራ ውስጥ በብዙ የጦር ሜዳዎች ላይ የጀብዱ ሥራዎችን ያዩና ያሳዩ ጦረኞች ነበሩ፡፡ ዳሩ ግን እንደ ፈሪዎች ተ ግባር ሊቈጠር የሚችለው የጭቆናና የአረመኔነት ትርእይት በፊታቸው ሲፈጸም ሲያዩ የቍጣ መንፈስ በውስጣቸው አይቀሰቀስም ነበር፡፡ የታላላቅ ሰዎች ልጆችም በዚሁ ስፍራ ነበሩ፡፡ እነርሱም ቢሆኑ ይህ

የጭከና ተግባር የአገራቸውን ክብር የሚቀንስ ሆኖ አላገኙትም፡፡ ፈላስፎች÷ ባለ ቅኔዎች÷ ካህናት÷ ገዥዎች÷ ከታላላቆች ጀምሮ እስከ ተራ ሰዎች ድረስ የታላቁን ሕንፃ መቀመጫዎች አጣበውታል፡፡ ዳሩ ግን የመኳንንቱ ጭብጨባና ጩኸት ከመደዴው ሕዝብ ወካታ በምንም አያንስም ነበር፡፡ ይህ የጭከና ተስቦ ያልነካው ሰው በዚህ ስፍራ ቢገኝ÷ የሕዝቦችዋ ልብ ይህን በመሰለው የግፍ ተግባር ከተመረዘ÷ ሰሮም ምን ተስፋ አላት? ብሎ መጠየቁ አይቀርም፡፡

ከመቀመጫዎቹ ከፍ ብሎ አንድ ወንበር ይታያል፡፡ በዚያም ላይ የሮሙ ቄሣር ዴክዮስ ተቀምጦበታል፡፡ በዙሪያውም የሮም ኃያላንና ታላላቅ ሰዎች ስፍራ ስፍራቸውን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የቄሣር የክብር መኰንኖች ነበሩ፡፡ እነርሱም በአደባባዩ ላይ ለሚፈጸሙት ትርእይቶች አቃቂር እያወጡ ሲሣሣቁ ይሰማሉ፡፡ ከሩቅ በሚሰማው ሣቃቸው በመፈንጠዛቸውና በሚያምረው ልብሳቸው ምክንያት ሕዝቡ አትኩሮ የሚመለከተው እነርሱን ነበር፡፡

ብዙ ለመግቢያ የሚሆኑ ትርእይቶች ከታዩ በኋላ ዋናው ጨዋታ ተጀመረ፡፡ ብዙዎች ተዋጊዎች ባላቸው ጥበብና ሙያ ግብ ግብ እየገጠሙ በተመልካቾች ፊት መውደቃቸው የሕዝቡን ስሜት ከልብ ያሰፈ ቀሰቀሰው፡፡ የበለጠ ትርእይት ለማየት ያላቸው ጉጉት ከመቀመጫቸው እያስነሣ ያስጮኻቸው ጀመረ፡፡

በተመልካቾቹ ዘንድ ከልክ ያሰፈ የተደነቀው ከሞሪታኒያ አገር የመጣው ተዋጊ አደባባዩ ውስጥ ሲገባ ታየ፡፡ ይህ ሰው በቁመትም ሆነ በጉልበት ጉልያድን የሚወዳደር ነበር፡፡ ጉልበትን ከቁመት ጋር አስተባብሮ የያዘ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡

ከሞሪታኒያው ተወላጅ ጋር እንዲጋጠም ባታቪያ ከተባለው አገር የመጣ አንድ የጨበጣ ጦር ተዋጊ ወደ ትርእይቱ አደባባይ ገባ፡፡ ይህም ሰው በጉልበትም ሆነ በሰውነት ከሞሪታኒያው ተወላጅ ምንም አያንስም፡፡ በሁለቱ ተዋጊዎች መካከል ተመልካችን የሚያስደንቅ አንድ ልዩነት ይታይ ነበር፡፡ የሞሪታኒያው ተወላጅ መልኩ የቀይ ዳማ÷ ጸጉሩ ዞማ÷ ዓይኖቹ የሚያበሩ ነበሩ፡፡ የባታቪያው ተወላጅ ደግሞ መልኩ ነጣ ያለ÷ ጸጉሩ ወርቅማ÷ ዓይኖቹ አርቀው የሚመለከቱ ነበር፡፡ በማንኛውም ረገድ ሁለቱ ተዋጊዎች የተስተካከሉ በመሆናቸው ይኸኛው ያሸንፋል ብሎ ለመወሰን አስቸጋሪ ነበር፡፡ የሞሪታኒያው ተወላጅ ቀደም ብሎ ብዙ የውጊያ ትርእይቶችን ያሳየ በመሆኑ ሳይደክም አይቀርም ብለው የሚያስቡ አያሌ ሰዎች ነበሩ፡፡

ሁለቱ ተዋጊዎች በታላቅ ቅልጥፍና ግብ ግብ ገጠሙ:: እህልና ውኃ የማያስኘውን የባታቪያውን ተወላጅ አስካዘበር ሞሪታናዊው ፈጣንና ግሩም በሆነ አኳኋን ይመክት ጀመር:: ሞሪታናዊው ፈጣንና አጥቂ ቢሆንም በማይበገረው ተቋቋሚው ላይ የማየል ዕድል ሊያጋጥመው አልቻለም::

ወዲያውም ምልክት ተሰጠና ተዋጊዎቹ ወደ ስፍራቸው ገቡ:: ይህም የተደረገው ለተዋጊዎቹ በመራራት ሳይሆን እንዲያ ተስገብግቦ የሚጠባበቀውን የሮማውያን የደም ጥማት ለማስታገሥ የሚቻልበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ አረፍ እንዲሉ ነበር:: እነዚህ ሁለት ተዋጊዎች ተመል ሰው እንደሚመጡ ሁሉም ሳይረዳው አልቀረም::

ሁለቱ ተዋጊዎች እንደ ወጡ በብዛት የሚቈጠሩ ሰዎች ወደ አደባባዩ ገቡ:: ሁሉም ጦር የጨበጡ ነበሩ:: ወዲያው ግብ ግብ ገጠሙ:: ውጊያውም ወገን ለይቶ የሚደረግ አልነበረም:: ሁሉም እርስ በእርሱ ይጨፋጨፍ ነበር:: ይህን የመሰለው ትርእይት የጨዋታውን አደባባይ በደም በሚያጥለቀልቅበት ጊዜ የተመልካቾቹ አንጀት ይርስ ነበር:: ትርእይቱም አያሌ ሰዎችን በአነስተኛ ጊዜ ውስጥ እንዲያልቁ ያደርጋቸው ነበር::

አደባባዩ ውስጥ ሽብር ሆነ:: አምስት መቶ የሆኑ ጦር የጨበጡ ሰዎች ደማቸውን እየዘሩ ይተራመሳሉ:: አንዳንድ ጊዜ አንድ ስፍራ ላይ እጅብ ይላሉ:: በሌላ ጊዜ ደግሞ በአደባባዩ ሁሉ ተሰራጭተው የነፍስ አውጭኝ ሲሯሯጡ ይታያሉ:: አደባባዩን የሬሣ ክምር አልብሶታል:: የተረፉትም ያለ ምሕረት ይገዳደላሉ:: አሸናፊዎቹ ወዲህና ወዲያ እየተሯሯጡ ያገኙትን እየቀነደቡ ይጥሉታል:: የመጨረሻዎቹ ቀሪዎችም በአንድ ስፍራ ላይ እጅብ ብለው ይከሳከሳሉ:: በመጨረሻም ውጊያው እየበረደ ሄደ:: ከአምስት መቶ ሰዎች ውስጥ አንድ መቶ ሰዎች ቀሩ:: አብዛኛዎቹም የቈሰሉና የደከሙ ነበሩ:: ወዲያው አንድ ምልክት ተሰጠ:: ሁለት ሰዎች አደባባዩ ውስጥ ጥልቅ ሲሉ ታዩ:: እየሮጡም እጅብ ብለው ወደሚጨፋጨፉት ሰዎች ደረሱ:: እነዚህም ሁለት ሰዎች ሞሪታናዊውና የባታቪያው ተወላጅ ነበሩ:: እነርሱም ባረፈ ጕልበታቸው በደከሙት ሰዎች ላይ እንደ መዓት ወረዱባቸው፤ በአደባባዩ ላይ እልቂት ሆነ:: ሁለቱ ኃይለኞችም ግራና ቀኝ እየተዘዋወሩ ውጊያ ያደከማቸውን ምስኪኖች እየመተሩ ጣሉአቸው:: በመጨረሻው ሁለቱ ብቻ በአደባባዩ ላይ ቆመው ቀሩ:: ጆሮ የሚያደነቍር ጭብጨባና ጩኸት ከተመልካቹ ሕዝብ ዘንድ ቀረበላቸው::

ሁለቱ ጉባዮች እንደገና ተጋጠሙ። የሬሳው ክምር ከአደባባዩ እስኪነሣ ተመልካቾቹ እነርሱን ብቻ ይመለከቱ ነበረ። በሁለቱ መካከል የሚደረገው ውጊያ እንደ መጀመሪያው ጊዜ እየተፋፋመ ሄደ። ሞሪታናዊው ቀልጣፋ የባታቪያው ተወላጅ ግን ጠንቃቃ ነበር። በመጨረሻ ሞሪታናዊው ክፉኛ ጦሩን ሰነዘረ። የባታቪያው ተወላጅም በብልሃት ከመከተ በኋላ በበኩሉ ጦሩን ሰነዘረ። ሞሪታናዊው ወደ ኋላ አፈገፍጋለሁ ሲል ጦሩ ከእጁ ወደቀ። የባላንጣውም ጦር ግራ እጁን ቀርድዶ ጣለው። ሞሪታናዊው ወደቀ። በዚያ የተሰበሰበው መቶ ሺህ ሰው ደስታውን ከፍ ባለ ጩኸት ገለጠ። ዳሩ ግን ይህ ትርዒቱ ማክተሚያ ሲሆን አልቻለም። ወዲያው ሠራተኞቹ መጥተው ሁለቱን ተዋጊዎች ገላገሉአቸው። ነገር ግን ይህ ድርጊት የምሕረት አለመሆኑን ተመልካቾች ብቻ ሳይሆን ቍስለኛውም ሳይረዳው አልቀረም። ወደ ፊት የተደገሰለት ነገር ነበር።

በቁማሩ ዙሪያ ከተሰበሰቡት መኰንኖች አንዱ ለጓደኛው ለማርሴሉስ «የባታቪያው ተወላጅ የሚቻል አይደለም» አለው።

«እንዲህ አድርጎም የለ፤ ካልክስ ሉኩሉስ እስከ ዛሬ ድረስ ይህን የመሰለ ትርእይት ዐይቼ አላውቅም። ሁለቱም ተዋጊዎች ከዚህ ቀደም ካየናቸው ሁሉ የበለጡ ናቸው።»

«ገና ምኑን ዐይተህ። ከሁለቱም የሚበልጥ ኃይለኛ ገና ይመጣል።»

«አይደረግም ማን የሚሉት ነው?»

«በጨበጣ ጦር ተዋጊው ማክር ነዋ! እርሱን የሚወዳደር እስከ ዛሬ ዐይቼ አላውቅም።»

«ዝናውን ሰምቼአለሁ። ዛሬ የሚመጣ ይመስልሃል?»

«አዎን፤ ጭምጭምታ ሰምቼአለሁ።»

የሁለቱ መኰንኖች ንግግር አውሬዎች ከሚጠበቁበት ዋሻ በመጣ ድምፅ ተቋረጠ። የተሰማው ድምፅ የበረሃ አውሬዎች በረሃብ በሚሠቃዩበት ጊዜ የሚያሰሙት የቍጣ ጩኸት ነበር።

ወዲያው አንድ የብረት መዝጊያ ከበሩ አናት ላይ በቀሙ ሰዎች ተከፈተ። አንድ ነብር ወደ አደባባዩ መካከል ወለም ዘለም ሲል ታየ። ነብሩ ከጥቂት ቀናት በፊት ከአፍሪቃ የመጣ ነበር። ሦስት ቀን ሙሉ ምግብ ሳያገኝ በብቸኝነት በዋሻ ውስጥ መቀመጡ የተፈጥሮ ቍጣውን አባብሶ ለሚያየው ሁሉ የሚያስፈራ አድርጎት ነበር። ጅራቱን ወዲህና ወዲያ እያማታ በዙሪያው የተቀመጡትን ሰዎች ደም በለበሱ ዓይኖቹ እየገረመመ አደባባዩን ይዞር ጀመር። ዳሩ ግን የተመልካቾቹ ዓይን

አንድ ሌላ ነገር ተመለከተ። ከአንድ በኩል አንድ ሰውዬ ወደ አደባባዩ ገባ። ሰውዬውም የነውሩ መሸፈኛ እንዲሆነው ከታጠቀው ትንሽ ጨርቅ በስተቀር ራቁቱን ነበር። በእጁ የተሰመደውን አጭር ጦር ይዞ ወደ አደባባዩ መካከል በቄራጥነት ይራመድ ጀመር።

ዓይኖች ሁሉ በእርሱ ላይ ትክል አሉ። «ማከር ማከር» የሚል ጩኸት ቊጥሩ ከመጠን ካለፈው ተመልካች አንደበት ተሰማ።

ነብሩም ማከርን ዐየው። አስፈሪ የሆነ ጩኸት አሰማ። ማከርም ፍንክች ሳይል ካለበት ቆሞ ትክ ብሎ ይመለከተው ጀመር። ነብሩም ከተድሞው በበለጠ አኳኋን ጅራቱን ወዲህና ወዲያ እየቆላ በቀጥታ ወደ ማከር ተጠጋ። እጠገቡም ደርሶ ለጥ ብሎ አደባ፣-ከጥቂት ጊዜ በኋላ በማከር ላይ ጉብ ለማለት እንደ ፍላፃ ተወረወረ። ይህ ሁሉ ሲሆን ማከር ተዘጋጅቶ ነበር። ነብሩ ወደ እርሱ ሲወረወር በታላቅ ቅልጥፍና ወደ ግራ ዘወር አለ። ነብሩም ስቶት መሬት ላይ ወደቀ። በዚያን ጊዜ ማከር በያዘው ጦር ነብሩን ከልቡ ላይ ቀበቀበበት። የአውሬው ሙሉ ሰውነት ኰርምትምት አለ። ጥቂት ጊዜ ከተንፈራገጠ በኋላ አሠቃቂ የሆነ የጣር ጩኸት አሰምቶ እዚያው አሸልቦ ቀረ።

በዚህን ጊዜ ከተመልንቾቹ የተሰማው ጭብጨባ እንደ ነጐድጓድ አስተጋባ።

ማርሴሉስ÷ «ድንቅ ነው!» ሲል ጮኸ። «የማከርን የመሰለ ቅልጥፍና ዐይቼም አላውቅ!»

የማርሴሉስ ጓደኛም÷ «ለቅልጥፍናው ምን ወደር አለው። ዕድሜውን ሙሉ ከመዋጋት በቀር ሌላ ምን ሥራ አለው ብለህ ነው?» ሲል መለሰለት።

ሠራተኞች የነብሩን እሬሳ ተሸክመው ሄዱ። ወዲያው የብረት መዝጊያ ሲከፈት ተሰማ። አንድ ጐፈር አንበሳ ብቅ አለ። በአደባባዩ ላይ ወዲህና ወዲያ እየተንጎማለለ ተመልንቾቹን በአድናቆት ይመለከት ጀመር። አንበሳው በቁመቱም ሆነ በግርማው የሚያስፈራ ነበር። ከሁለት ነብሮች ጋር እንኳ ቢጋጠም በአንድ አፍታ ጭጭ ሊያደርጋቸው የሚችል ነበር። በአንበሳው ዓይን ማከርን ሲመለከቱት ሕፃን ይመስላል ለማለት ይቻላል» አንበሳው ምግብ ከየ ብዙ ቀናት  አልፈዋል። ዳሩ ግን እንደ ነብሩ የቊጣ መንፈስ አልታየበትም። መሽሎኪያ ቀዳዳ በመፈለግ እንድ ጊዜ ያን ክብ አደባባይ እያነፈነፈ ከዞረ በኋላ ጐርጡን በመረዳት ወደ አደባባዩ መካከል ሄዶ ቆመ። ከዚያም አፍንጫውን መሬት ላይ ተክሎ ቢያገሳ ጽኑ የሆነው ሕንፃ እስከ መሠረቱ ድረስ የተንቃነቀ መሰለ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የማይበገረው ማክር ዝም ብሎ ቆሞ ይመለከት ነበር። ጦሩን ደህና አድርጎ ጨብጦ ካሁን አሁን ጉብ ይልብኛል በማለት ይጠባበቅ ነበር። በመጨረሻም አንበሳው ፊቱን ወደ ማክር አዞረ። ሁለቱ ዓይን ለዓይን ተፋጠው ቆሙ። ፍንክች የማይለው የማክር አስተያየትም አውሬውን ከልክ ያለፈ እንዲቴጣና ጉፈሩን እንዲቆም አደረገው። ጅራቱን ወደ ኋላ ጋማውን ወደ ላይ ገትሮ እንደ ዘንግ ሊወረወር መሰናዳት ጀመረ። በዚህ ጊዜ የተመልካቾቹ ልብ ስቅል አለ። በናፍቆት ይጠባበቁዋት የነበረችው ቅጽበት ደረሰች።

አንበሳው ተወረወረ። ማክርም ጦሩን እንደ ሰነዘረ ወደ ጐን ውልብ አለ። በዚህ ጊዜ ጦሩ የአንበሳውን የጐድን አጥንት አግኝቶ ኖሮ ከእጁ አምልጦ መሬት ላይ ወደቀ። አንበሳው በመጠኑ ቈስሎ ነበር። ቍስሉ ቍጣውን ከመጠን ያለፈ አደረገው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማክር ምንም ፍንክች አላለም። ባዶ እጁን አንበሳው ፊት ቆሞ ይታይ ነበር። አንበሳውም እየደጋገመ ሊወጣበት ይወረወር ጀመር። ማክርም በብልሃትና በቅልጥፍና ወዲህ ወዲያ እያለ ጦሩ የወደቀበት ስፍራ ሊደርስ ቻለ። ጦሩን እጁ ካገባ በኋላ አንበሳው እንደ ልማዱ ተወርውሮ መጣበት። ማክርም ሰንዝሮ ልቡ ላይ ወጋው። ታላቁም አውሬ ወድቆ ማጓራት ጀመረ። እንደገናም እየተንገዳገደ ተነሥቶ ጥቂት እርምጃዎች ከሄደ በኋላ የመጨረሻ ጩኸት አሰምቶ እዚያው ድፍት ብሎ ቀረ።



ነብሩም ማክርን ዐየው

ሮማውያን የትርእይቱን መለወጥ ስለ ፈለጉ በማክር ፈንታ የባታቪያው ተወላጅ ተተካ:: አንድ አነስተኛ ነብር በአደባባዩ ውስጥ ተለቀቀ:: የባታቪያውም ተወላጅ ያለ አንዳች ችግር ወዲያው ነብሩን ገደለው:: ቀጥሎም አንድ አንበሳ ብቅ አለ:: አንበሳው በቁመት መጠነኛ ነበር:: በቀጣና በመንቆራጠጥ ከፊተኛው የባሰ ነበር:: የባታቪያውን ተወላጅ ከአንበሳ ጋር በመዋጋት ያሳየው ቅልጥፍና ከማክር ያነሰ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር:: ግብ ግብ እንደ ገጠሙ አንበሳው ቈሰለ:: ደሙን እያዝረከረከ ቢወረወር የባታቪያውን ተወላጅ መዳፉ ውስጥ ሊያገባው ቻለ:: በዚያ ሁሉ ተመልካቾች ፊት ሰውነቱን እንደ አሮጌ ጨርቅ ብጭቅጭቅ አድርጎ ጣለው:: በኋላም ማክር መጥቶ አንበሳውን በቀላሉ ገደለው::

ከተመልካቾቹ ለማክር የቀረበው ጭብጨባ በማስተጋባት ላይ እያለ አንድ ሰው ወደ አደባባዩ ውስጥ ገባ:: እርሱም ቀደም ብሎ ቈስሎ የነበረው የሞሬታኒያው ተወላጅ ነበር:: እየተንገዳገደና ደሙን እያዝረከረከ ማክር ወዳለበት ቀረበ:: እንዲሞት የተፈረበደት መሆኑ በሁሉ ዘንድ ታውቆ ነበር:: ራሱም ዐውቆት ኖሮ ማክር አጠገብ እንደ ደረሰ ጦሩን መሬት ላይ ጥሎ ተስፋ በመቍረጥ እንዲህ ሲል ጮኸ፤ «ወዲያ ግደለኝና ከጭንቀት ዐሳርፈኝ!»

ተመልካቾች ሁሉ ከአሁን አሁን ወግቶ ጣለው በማለት ዓይኖቻቸውን አፍጥጠው ሲመለከቱ ማክርም ጦሩን ወዲያ አሽቀንጥሮ ጥሎ ዝም ብሎ ቆመ:: ተመልካቾቹ ዓይናቸውን ማመን አቃታቸው:: የበለጠ መገረም የያዛቸው ማክር እጆቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ ወደ ቄሣሩ ፊት ዞሮ የሚከተሉትን ቃላት በተናገረ ጊዜ ነው:: «ታላቁ ቄሣር ሆይ! እኔ የክርስትናን እምነት ተቀብያለሁ:: ከእንግዲህ ወዲህ ከእንስሳት ጋር በስተቀር በሰው ላይ እጆቼን ላላነሣ ቍርጥ ውሳኔ አድርጌአለሁ:: ከመግደል ይልቅ መሞት ይሻለኛል::»

የሕዝቡ ማጉረምረም አደባባዩን ሞላው:: ማርሴሉስም÷ «ምን ማለቱ ነው? ክርስቲያን ነኝ? ከመቼ ወዲህ?» ሲል ጓደኛውን ጠየቀው::

ሉኩሉስም እንዲህ ሲል መለሰለት፡- «እነዚህ ክርስቲያኖች እየተባሉ ፍጥረቶች እመኖሪያው ድረስ ይመጣሉ ማለትን ሰምቼ ነበር:: አስጸያፊ የሆነ ማኅበራቸው ውስጥ ሳይገባ አይቀርም:: ክርስቲያኖች የሚባሉት ሁሉ አስከፊ ፍጥረቶች ናቸው:: ማክርም እንደ እንዳቸው ሳይሆን አልቀረም::»

«ከመዋጋት መሞትን ይመርጣል ታዲያ?»

«ክርስትና የተባለ ዕብደት የያዘው ሁሉ እንደዚሁ ነው።»

ተመልካቾቹ መንቈራጠጥ ጀመሩ። በመደነቅ ፊንታ ንዴት ያዛቸው። አንድ ተራ ተዋጊ እንዲህ አድርጎ ሊደፍራቸው መቻሉ ቊጣቸውን እያጋለው ሄደ። ሠራተኞች ከዚህም ከዚያም ብቅ ብቅ አሉ። ዳሩ ግን ትርእይቱ እንዲቀጥል በመወሰኑ ሁሉም ወደ መጡበት ተመለሱ። ማክር መዋጋት እምቢ ካለ÷ የእምቢተኝነት ቅጣቱን እንዲቀበል ተወሰነ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማክር ምንም የፍርሃት መንፈስ አላሳየም። ባዶ እጁን በአንድ ጡጫ ብቻ እንኳ ከምድር ጋር ሊያደባልቅ ወደሚችለው የሞሪታኒያው ተወላጅ ተጠጋ። የሞሪታኒያው ተወላጅ ዓይኖቹ ደም ለበሱ። መደነቅ÷ ደስታና የድል ስሜት ይዘው ያንገላቱት ጀመር። ጦሩን ከወደቀበት አንሥቶ ማክርን ልቡ ላይ ወጋው።

‹‹ጌታ ኢየሱስ ሆይ÷ ነፍሴን ተቀበል!›› እነዚህ ቃላት በደም ተውጠው ቀሩ። የማክርም ነፍስ ከሰማዕታት ሠራዊት ጋር ለመቀላቀል ወደ ሰማይ ዐረገች።

ይህን ድርጊት ይመለከት የነበረው ማርሴሉስም ጓደኛውን ‹‹እንዲህ ያሉ ትርእይቶች አዘውትረው ይፈጸማሉን?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹ክርስቲያኖች አደባባዩ ውስጥ እንዲገቡ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ የሚፈጸመው ይህንኑ የመሰለ ትርእይት ነው። አያሌ ከሚሆኑ አውሬዎች ጋር ተዋጉ ቢሉአቸው በደስታ ይዋጋሉ። ወጣት ልጃገረዶች እንኳ ከአንበሳም ሆነ ከነብር ጋር ለመግጠም ምንም አይፈሩም። በሰው ላይ ግን እጃቸውን ስንዝር አያደርጉም። ማክርን የመሰለ ተዋጊ መቸም አይገኝም። ክርስቲያን በመሆን የሞኝነት ሥራ ሠራ። እስከዚህም ያደረሰው የሕዝቡ መቀየም ነው።››

ማርሴሉስም ‹‹ለአንድ ተራ ተዋጊ እንዲህ ያለ ድፍረት ሊሰጥ የቻለው እንዴት ያለ እምነት ቢሆን ይሆን?›› አለ።

‹‹አይዞህ የእምነቱን ምሥጢር ወደ ፊት እያወቅኸው ትሄዳለህ።››

‹‹እንዴት?››

‹‹ያልሰማው መጣ! እነዚህን ክርስቲያኖች ካሉበት ስፍራ እያደነክ እንድትይዝ ተሹመህ የለም እንዴ? አብዛኛዎቹ የተሸሸጉት ካታኮምብ በተባለው የምድር ውስጥ ለውስጥ ዋሻ ውስጥ ነው። አንዳቸውን ሳያስቀሩ ተከታትሎ መያዝ ያሻል።››

‹‹በዛሬ ቀን ብቻ የተቃጠሉት ሃምሳዎቹ እነሰው ነው ሌሎቹ እንዲያዙ የሚፈለገው?››

‹‹ባለፈው ሳምንት መቶ የሚሆኑ አንገታቸው እንደ ተቀላ አልሰማህም? ገና ምኑ ተይዞ! ከተማውን የሞሉት እነርሱ ብቻ ናቸው። ቄሣሩ የቀድሞው እምነት የጥንት ስፍራውን እንዲያዝ ወስኖአል።››

‹‹የአገራችን መቅሠፍቶች ስለ ሆኑ ድራሻቸው እንዲጠፋ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንንም ወደ ፊት ትረዳዋለህ።››

ማርሴሉስ የጓደኛውን ንግግር በትሕትና ካዳመጠ በኋላ እንዲህ አለ፡- ‹‹እንደምታውቀው በሮም ውስጥ ብዙ ጊዜ አልቆየሁም። ክርስቲያኖች የሚባሉት ሰዎችም የሚያምኑት በምን እንደሆን አጣርቼ ዐላወቅሁም። እስከ አሁን ስለ እነርሱ የሰማሁት ወንጀለኞችና አገር አጥፊዎች መሆናቸውን ብቻ ነው። አንተ እንደምትለው ከሆነ በሚገባ ሳውቃቸው ዕድል ይገጥመኝ ይሆናል።››

ወዲያው አንድ ዐዲስ ትርእይት በመጀመሩ የሁለቱ ጓደኞች ንግግር ተቋረጠ።

አንድ በዕድሜው የገፋ ሽማግሌ አደባባዩ ውስጥ ገባ። እርሱም ሰውነቱ በእርጅና የጉበጠ÷ ጸጉሩ ጥጥ የመሰለ ነበር። የእርሱ መታየት በተመልካቾች ዘንድ የንቀትና የማሾፍ ወካታን ፈጠረ። አዛውንትነቱ ምንም ሊያሳፍራቸው አልቻለም። ሣቃቸውና ጩኸታቸው አደባባዩን ሞላው።

በዚህ ጊዜ ሽማግሌው እጆቹን አንሥቶ ጥቂት ቃላትን ሊተነፍስ ሞከረ።

ማርሴሉስ÷ ‹‹ማን የሚባለው ነው?››

ሉኩሉስ ‹‹እስክንድር የተባለው የእነዚያ ርኵሶች መምህር ነው። እምነቱን እንዲተው ቢያስፈራሩትም አልበገር ብሎ እስከዛሬ ቆይቶአል።››

‹‹ዝም በሉ እባካችሁ! ሊናገር ነው።››

ሽማግሌውም እጆቹን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ‹‹ሮማውያን! እኔ ክርስቲያን ነኝ። አምላኬ ለእኔ ሲል ሞቶአል÷ እኔም ለአምላኬ ስል ሕይወቴን በደስታ አሳልፌ እሰጣለሁ።››

የሽማግሌው ቃላት በሕዝቡ ውካታና ጩኸት ተውጠው ቀሩ። ወዲያውም ሦስት ነብሮች እየገሰገሱ ወደ እርሱ መጡ። እጆቹን ጭብጥ አድርጎ በጸሎት ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አቀና። አውሬዎቹም ወዲያው በሚጭቀው ጣሉት።

የአውሬዎቹ ቊጥር እየበዛ ሄደ። ወዲህ ወዲያ እየተሯሯጡ መተራመስ ጀመሩ።

በመጨረሻም እርስ በርሳቸው መፋጀትን ያዙ፤ ትርእይቱም የሚያሠቅቅ ሆነ።

በአውሬው ትርምስ ውስጥ በብዛት የሚቄጠሩ እሥረኞች ተቀላቀሉ። አብዛኞቹ ወጣት ልጃገረዶች ነበሩ። እነዚህም የሮማውያንን የደም ጥማት እንዲያረኩ የተፈረደባቸው ነበሩ። ትርእይቱ የርኅራኄ ስሜቱ የተሟጠጠበትን ሰው እንኳ የሚዘገንን ነበር። ርኅራኄና ሐዘን በዚያን ወራት በሮም ውስጥ ስፍራ አልነበራቸውም። እነዚያ ወጣት ልጃገረዶች በዚህ በሚያሠቅቅ አኳኋን ከሞት ጋር ዓይን ለዓይን እንዲተያዩ ስለ ተፈረደባቸው መፍራታቸው አልቀረም።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ድፍረታቸው ከሞት በላይ አደረጋቸው። አውሬዎቹ ሊናጠቁአቸው በቀረቡ ጊዜ እጅ ለእጅ በመያያዝ ጽኑ የሆነ የእምነት ሰንሰለት ፈጠሩ።

ዓይኖቻቸውን ወደ ሰማይ አቅንተው ጣዕም ባለውና ወደ አርያም ሊያስተጋባ በሚችል ዜማ የሚከተሉትን ቃላት ዘመሩ።

‹‹ለወደደን
ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን
ለአባቱም
ነገሥታትና ካህናት ላደረገን
ለእርሱ
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ
ክብርና ኃይል ይሁን
ሃሌ ሉያ! አሜን።››

አንድ በአንድ ድምፃቸው በደም በመበከል በጭንቀት ገዘም ተሰኘ። የጣሩም ጩኸት ከምስጋናው መዝሙር ጋር ተዋሐደ። የእነዚህም የተዋቡ ሰማዕታት የጀግንነት መዝሙር በሰማይ ካሉት ጻድቃን ውዳሴ ጋር ተቀላቀለ።

# የቄሣር የመኮንኖች ሰፈር

ማርሴሉስ የጋዶስ ተወላጅ ነበር። አስተዳደጉ በሮማ ጦር ሠራዊት ሥነ ሥርዓት የታነፀ ነበር። በአፍሪቃ÷ በሶሪያ÷ በብሪታንያ እየተዘዋወረ እንዲያገለግል በተደረገበት ጊዜ ሁሉ በጦር ሜዳ ላይ ካሳየው ጀግንነት ሌላ ከሥራ ጓደኞቹ ጋር የነበረው ኅብረትና አብሮ የመኖር ዘዴ በጣም አስመስጋኝ ነበር። ያሳየው የሥራው ችሎታ በማዕረግ ላይ ማዕረግ÷ በክብር ላይ ክብር እየጨመረ እንዲሄድ አደረገው። የአንድ ታላቅ መልእክት አድራሽ ሆኖ ወደ ሮም ከመጣ በኋላ ባሳየው ችሎታ ቄሣሩ በመደሰቱ ከክብር መኰንኖቹ መካከል አንድ ከፍተኛ ስፍራ ይዞ እንዲያገለግል ሾመው።

ሉኩሉስ ከኢጣልያ ይቅርና ከሮም ወጥቶ ዐያውቅም። ከጥንታውያን የሮም መኳንንት በመወለዱ በሀብትም በክብርም የደረጀ ነበር።

ሉኩሉስ በማርሴሉስ ድፍረትና ግልጽነት በመማረኩ ሁለቱ መኰንኖች የቅርብ ጓደኞች ሆኑ። ሉኩሉስ የሮምን መውጪያና መግቢያ ደኅና አድርጎ ያውቅ ስለነበር ማርሴሉስን አገር በማስለመድ በጣም ይረዳው ነበር።

ማርሴሉስ ኮሎሴዩም ወደ ተባለው የትርኢት አደባባይ ሄዶ ባለፈው ምእራፍ የተዘረዘረውን እልቂት ያየው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። የቄሣር መኰንኖች ሰፈር የተመሠረተው ከሮም ቅጥር አጠገብ ነበር። ሰፈሩም አንድ ልዩ በሆነ አጥር የተከበበ ነበረ። የወታደሮቹ መኖሪያ እንደ ዋሻ በግድግዳው ውስጥ በተቦረቦሩት ክፍሎች ውስጥ ነበር። መኮንኖቹ በቍጥር የበዙ፤ በከተማይቱም ውስጥ የነበራቸው አቋም ከፍ ያለ በመሆኑ ለብዙ ዘመናት የመንግሥቱን አስተዳደር የመቈጣጠሩን ሥልጣን በእጃቸው አግብተው ነበር። በቄሣር መኰንኖች ውስጥ ሥልጣን ማግኘት ከፍ ያለ ግምት የሚጣልበት ክብር በመሆኑ የማርሴሉስ የወደፊት ዕድሉ በጽኑ መሠረት ላይ እንደ ቆመ የሚቈጠር ሆነ።

በማግሥቱ ማለዳ ሉኩሉስ ወደ ማርሴሉስ መኖሪያ ክፍል ሄዶ ነበኘው። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላም ባለፈው ቀን ስላዩት ትርኢት መነጋገር ጀመሩ።

ማርሴሉስ ቀበል አደረገና ‹‹ትናንት ባየናቸው ትርኢቶች ፍጹም አልተደሰትኩም፤ ይህ የፈሪ ተግባር ነው›› አለ። ‹‹ሁለት

ጀግኖች በሥርዓት ሲዋጉ ማየት ያስደስተኛል። ትናንት በኮሎሲዩም ውስጥ ያየነው እልቂት ግን ፍጹም አስጸያፊ ነበር። ሽማግሌዎችና ሕፃናትስ ለአውሬዎች እንዲጣሉ የሚደረገው ለምንድነው?››

‹‹ክርስቲያኖች በመሆናቸው ይህን የመሰለ ፍርድ እንዲፈጸምባቸው የሚወስነው ሕጉ ነው።››

‹‹ሁልጊዜ የምሰማው ይህንኑ መልስ ነው። ክርስቲያኖች ምን አደረጉ? በተዘዋወርኩባቸው አገሮች ሁሉ ክርስቲያኖችን ዐይቻለሁ። ማንኛውንም ዓይነት ሁከት ሲያስነሡ ግን ዐይቼ ዐላውቅም።››

‹‹እባክህ ዝም በለኝ፤ የሰው ሙጣጮች ናቸው።››

‹‹ሁሉም ስለ እነርሱ የሚያወራው ይህንኑ ነው። ክፉ ነገር ለመሥራታቸው ምን መረጃ ይገኝባቸው ይሆን?››

‹‹መረጃ! ስለ እነርሱ ደግሞ ምን መረጃ ያስፈልጋል? የመንግሥትን ሕግና እምነት ለመቃወም የሚያሴሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። የእኛን አስተዳደር ክልብ የሚቃወሙ ለመሆናቸው የተገኘው ዋናው መረጃ ለአማልክቶቻችን መሥዋዕት ከማቅረብ ይልቅ ሞትን መምረጣቸው ነው። ከዚያ ከተሰቀለው አይሁዳዊ በስተቀር ሌላ ንጉሥ ዐያውቁም። እርሱንም ከሞተበት ተነሥቶአል እያሉ ያወራሉ። በእኛም ላይ ያላቸውን ጥላቻ ከሞት በኋላ ለዘለዓለም በገሃነም ትሠቃያላችሁ በሚለው ስብከታቸው ይገልጣሉ።››

‹‹የምትለው ሁሉ እውነት ሊሆን ይችላል። እኔ ግን በበኩሌ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም። ስለ ክርስቲያኖች የማውቀው ነገር የተወሰነ ነው።››

‹‹ከተማይቱን ያጣበቡት እነርሱ ብቻ ናቸው። ከእነርሱ ነጻ የሆነ የግዛታችን አንድ ክፍል አይገኝም። አንድ ነገር ልብ አድርግ፤ ብዙዎቹን በሐዘን ላይ የጣለው የመንግሥታችን መድከም፤ የክፋትና ያለመታዘዝ መብዛት፤ የድንበራችን እየተቀነሰ መሄድ፤ ይህ ሁሉ ክርስቲያኖች ሲበዙ እየገነነ የሚሄድ ነገር ነው። ይህን መዓት የሚያመጡብን እነርሱ ካልሆኑ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል?››

‹‹ይህን የምትለውን መዓት እንዴት አድርገው አመጡብን ለማለት ይቻላል?››

‹‹አስጸያፊ በሆነው ትምህርታቸውና ሥራቸው ነዋ! ጦርነት አይገባም፤ ወታደሮች የጥፋት መሣሪያዎች ናቸው። እስከዚህ ድረስ ያደረሰን የገነነውን ሃይማኖታችንን መርገማቸው ነው። ነዋሪዎቹን አማልክቶቻችንን የተረገሙ ሰይጣናት ናቸው እያሉ ያስተምራሉ።

በትምህርታቸውም አማካይነት ግብረ ገብነት የተባለ ነገር ፈጽሞ እንዲጠፋ ለማድረግ ይጣጣራሉ። በምሥጢር የሚፈጽሙአቸው ተግባሮች እጅግ የሚያሠቅቁ ናቸው።

‹‹ከራሳቸው ወገኖች በስተቀር ምሥጢራቸውን ዘልቆ የሚያውቅ የለም። አንዳንድ ጊዜ ግን አጉል የሆነ ንግግራቸውና የረከሰ መዝሙሮቻቸውን እንሰማለን።››

‹‹አሁን የዘረዘርካቸው ነገሮች ዝም ብለው የሚታለፉ አይደሉም። ያልከው ሁሉ እውነት ከሆነ ተገቢውን ቅጣት መቀጠል አለባቸው። ባልሳሳት ክርስቲያኖቹ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳይቀላቀሉ በምሥጢር ይኖራሉ። ስለ እነርሱ የምናውቀው ነገር የተወሰነ ነው ብለሃል። እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ። ትላንት እንደዚያ ባለ አሠቃቂ መንገድ ያለቁት ሰዎች ክርስቲያኖች ይሠራሉ እየተባሉ የሚታሙትን ወንጀል የሠሩ ይመስልሃል? ትናንት ያየነው ሽበታም ሰውዬ ዕድሜውን በኃጢአት ያሳለፈ ይመስልሃል? እነዚያስ ቆነጃጅት የዘመሩት መዝሙር ርኩሰት ያለበት ነው?

‹‹ለእርሱ ለወደደን

ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን።››

ማርሴሉስም መዝሙሩን ዝቅ ባለ ድምፅ አዜመ።

ሉኩሉስም፣ ‹‹እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም አዝኜላቸዋለሁ።››

ማርሴሉስም ‹‹ሮማዊ ወታደር ባልሆን ኖሮ አለቅስላቸው ነበር። እስቲ ጉዳዩን በሚገባ አስተውለው። አንተ ስለ እነዚህ ክርስቲያኖች ያወራህልኝ ነገር ሁሉ ሁኔታቸውን ከማያውቁ ሰዎች የመነጨ ነው። ክርስቲያኖች ነውረኞችና የሰው ሙጣጮች ናቸው ብለኸኛል። በየጊዜው የሕይወትን መሠረት በሚያናውጥ መሪር ሞት ፊት ምርጫ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ትናንት ተረድቻለሁ። ድፍረታቸውና አሟሟታቸው የሚያስደንቅ ነበር። ሮም በረጅም ታሪክዋ ውስጥ ትናንት ያየነውን የመሰለ ጀግንነት ልታሳየኝ አትችልም። ወታደሮችን ይጠላሉ ትለኛለህ። ዳሩ ግን አሟሟታቸው የጀግንነት ነበር። አገራቸውን የሚከዱ ናቸው ትለኛለህ። ዳሩ ግን ከአገራቸው ሕግ አንዲቱን ነቁጥ አልተላለፉም። ርኩሶች ናቸው ትለኛለህ፥ ዳሩ ግን የትናንቱን ቆነጃጅት የመሰለ ንጽሕና ያላቸው በምድር ላይ የሚገኙ አይመስለኝም።››

‹‹ዋና ደጋፊያቸው ሆነህ የለም እንዴ?››

‹‹እንደርሱ አይደለም ወዳጄ ሉኩሉስ፥ እኔ የምመኘው እውነቱን ለማወቅ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ስለ እነዚህ ሰዎች እሰማው የነበረው

ልክ አንተ የነገርኸኝን የመሰለ ወሬ ነው። ትናንት ያየሁት ትርእይት ግን ይህ ወሬ እውነት ሊሆን አይችልም የሚል ስሜት በውስጤ ፈጥሮብኛል። አንተ ነገሩን በማብራራት እንድትነግረኝ ብጠይቅህ የወሬ ወሬ ከማውራት አላለፍክም። ካልክስ ባየኋቸው ክፍለ ዓለማት ሁሉ ክርስቲያኖች የሰላማዊነትና የታማኝነት ዝና እንዳላቸው ይታወሰኛል። ሁከት አንሺዎች፥ ብጥብጥ ፈጣሪዎች እየተባሉ የሚታሙት በከንቱ ነው። ሠሩ የሚባሉትንም ወንጀል ማስረጃ አቅርቦ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ያለ አይመስለኝም። ታዲያ እንደዚህ ያሉት ሰዎች ሞት ይገባቸዋል?››

‹‹ቄሣር ያለ በቂ ምክንያት እንዲጠቁ ያደርጋል ብለህ ነው?››

‹‹በክፋት መንፈስ የሚመሩትን አማካሪዎቹን መንገድ ተከትሎ እንደሆንስ?››

‹‹ዐሳቡ ሁሉ ከራሱ የመነጨ ለመሆኑ ጥርጥር አይግባህ።››

‹‹መቼም እስካሁን የሞቱት ቍጥር የበዛ ነው።››

‹‹አዎን፥ በሺህ የሚቈጠሩ ሳያልቁ አይቀርም። ዳሩ ግን ገና ያልተነኩ ብዙዎች አሉ። እነዚህን አድነን ለማጥፋት ሞክረን አቅቶናል። በነገራችን ላይ አንድ ብርቱ ጕዳይ ዘነጋሁ። ከቄሣር ዘንድ ብርቱ የሆነ መልእክት አምጥቼልሃለሁ።››

ሉኩሉስ ከትጥቁ ውስጥ የብራና ጥቅል አውጥቶ ለማርሴሉስ ሰጠው። እርሱም ተቀብሎ በጥንቃቄ ያነበው ጀመር።

ደብዳቤው የማዕረግ ዕድገት ያገኘ መሆኑንና ክርስቲያኖችን ከተሸሸጉበት ካታኮምብ ከተባለው ዋሻ ውስጥ እየፈለገ እንዲይዝና እንዲያቀርብ የታዘዘ መሆኑን ይገልጽ ነበር።

ማርሴሉስ ፊቱን ቅጭም አድርጎ ደብዳቤውን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ጠቅልሎ አስቀመጠው።

‹‹ምነው የደስታ መልክ ዐይታይብህ?›

‹‹እንደ እውነቱ ከሆነ ይህን ያሁኑን ሥራዬን በፍጹም አልወደድኩትም። እኔ ወታደር ነኝ። ሕፃናትና ሽማግሌዎችን ለገዳይ አሳልፌ መስጠት ተግባሬ አልነበረም። መታዘዝ የወታደርነት ግዴታዬ ስለ ሆነ ሌላ ምንም ሳያደርገው የምችለው ነገር የለም። ፈቃድህ ቢሆን ካታኮምብ ስለ ተባለው ስፍራ አስረዳኝ።››

‹‹ካታኮምብ የተባለው ስፍራ መጠኑና ርዝመቱ ይህ ነው የማይባል ከከተማይቱ ሥር የተቆፈረ የምድር ውስጥ ዋሻ ነው።

ስደት ሲነሣባቸው ክርስቲኖች ወደ እዚያ ይሸሻሉ። የሞቱባቸውንም የሚቀብሩት እዚያው ውስጥ ነው። እዚያ ከገቡ መንግሥት በምንም ዓይነት መንገድ ተቈጣጥሮ ሊደርስባቸው አይችልም።››

‹‹ካታኮምብ የተባለውን ዋሻ የቆፈረው ማን ነው?››

‹‹እገሌ ነው የቆፈረው ብሎ ለማስረዳት የማቻል አይመስለኝም። ዋሻው ከተቆፈረ ብዙ ዘመናት አልፎታል። እንደሚመስለኝ ዋሻዎቹ መጀመሪያ መቆፈር የተጀመሩት ለከተማይቱ መሥሪያ የሚያገለግል አሸዋ ለማግኘት ተብሎ ነው።

‹‹ዛሬም ቢሆን ሠራተኞች አሸዋ የሚያወጡት ከዚያው ውስጥ ነው። እያደር እያደር አሸዋ ፈላጊ እየበዛ በመሄዱ ዛሬ ከዋሻዎቹ ርዝመትና ብዛት የተነሣ ከተማችን የቆመችው የንብ እንጀራ በመሰለ መሠረት ላይ ነው።››

‹‹ለመሆኑ የታወቀ መግቢያ አለው?››

‹‹መግቢያዎቹ ቍጥር ስፍር የላቸውም። እኛንም የቸገረን ይኸው ነው። መግቢያዎቹ ጥቂቶች ቢሆኑ ኖሮ አድብተን ለመያዝ ይቻል ነበር። ከየትኛው አቅጣጫ ፍለጋችንን መጀመር እንደምንችል ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ሆኖብናል።››

‹‹በጣም የተጠረጠረ ስፍራ አለ?››

‹‹አዎን ቪያ አፒያ እንቲካ የተባለውን ጎዳና ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ተከታትሎ ከተሄደ በኋላ ሴሲሊያ ሜቴላ መቃብር ዘንድ ይደረሳል። ከዚያም አንድ ክብ የሆነ የሕንፃ ቁንጮ ይታያል። እዚያም ብዙ ጊዜ ሬሳ ተገኝቷል። የተገኙትም ሬሳዎች ክርስቲያኖች ዘመዶቻቸውን ከትርእይቱ አደባባይ ለቀብር ያመጡአቸው ናቸው እየተባለ ይወራል። ዘበኞቹ ተከታትለው ሲደርሱባቸው ሬሳውን እየጣሉ ይሸሻሉ። ይህም ሆኖ ዱካቸውን ለመከተል በፍጹም አልቻልንም። ካታኮምቡ ጎብሩ የበዛ በመሆኑ እዚያው ውስጥ ከሚኖሩት ሰዎች እርዳታ ሳያገኝ መውጪያ መግቢያውን ለማወቅ የቻለ ሰው የለም።››

‹‹እዚያ ውስጥ የሚኖሩት ያልካቸው እነ ማንን ነው?››

‹‹ለቤት ሠሪዎች አሸዋ የሚያቀርቡትን ቆፋሪዎች ማለቴ ነው። አሁን ሁሉም ክርስቲያኖች ሆነዋል። ዋና ሥራዬ ብለው የያዙት ለሞቱት ክርስቲያኖች የመቃብር ስፍራ በዋሻዎቹ ግድግዳ ውስጥ መፈልፈልን ነው። እነዚህ ቆፋሪዎች ዕድሜያቸውን የሚያሳልፉት በዚያው ውስጥ ከመሆኑም በላይ በነዚያ በተወሳሰቡት ዋሻዎች ውስጥ ሰውን የመምራት ችሎታ ያላቸው እነርሱ ብቻ ናቸው።››

‹‹ካታኮምብ ውስጥ ገብተህ ታውቃለህን?››

‹‹አዎን፤ ከረጅም ጊዜ በፊት አንድ ቆፋሪ እየመራ ዐሳይቶኝ ነበር። ከውስጡ ብዙ ጊዜ ልቆይ አልቻልኩም። በሕይወቴ እንደ እርሱ ያለ አሠቃቂና አስፈሪ ስፍራ ዐይቼ ዐላውቅም።››

‹‹ከዚህ ቀደም የካታኮምብን ዝና እንዲሁ የወሬ ወሬ እሰማ ነበር። እስከ አሁን ስፍራው በሚገባ እንዲጠና አለመደረጉ የሚያስገርም ነው። እነዚህ ቆፋሪዎች ወታደሮችን እየመሩ እተፈለገበት ስፍራ ሊያደርሱ አይችሉም?››

‹‹በፍጹም! ይኸማ ክርስቲያኖችን አሳልፎ መስጠት ይባላል።››

‹‹የሞከረ ሰው አለ?››

‹‹አዎን ከቆፋሪዎቹ ጥቂቶቹ መኰንኖችን ለመምራት ፈቃደኞች መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ ራሳቸው እስኪዞር ድረስ ሲያንከራትቱአቸው ይውላሉ። በመጨረሻም መኰንኖቹ የያዙት መብራት ይጠፋና እስከ መደንገጥ ይደርሳሉ። በኋላም መርተው እንዲያወጡአቸው ይለምናሉ። ከዚያም ቆፋሪዎቹ መኰንኖቹን በመደለል እዚህ ውስጥ ክርስቲያኖች የሉም፤ ያሉትም ከዚህ ውስጥ ሸሽተዋል በማለት ፍለጋው እተጀመረበት አድርሰው ይሸኙአቸዋል።››

‹‹ክርስቲያኖችን እስኪያገኝ ድረስ ቆርጦ ፍለጋውን የቀጠለ የለም?››

‹‹ክርስቲያኖቹን እስኪያገኙ ድረስ ጨክነው ፍለጋቸውን የሚቀጥሉትን በአንድ በተወሰነ አካባቢ ውስጥ ሲያዞሩ ያከርሙአቸዋል።››

‹‹ክርስቲያኖች ያሉበትን ስፍራ የሚጠቁም ቆፋሪ እስከ ዛሬ አንድም አልተገኘም?››

‹‹አልፎ አልፎ ይገኛል። ዳሩ ግን ክርስቲያኖች አንድ ትንሽ የአደጋ ምልክት ሲሰሙ በሚያውቁት ሥርቻ ውስጥ እየገቡ ይሠወራሉ።››

‹‹እንዲህ ከሆነማ እንዴት አድርጎ ሊቀናኝ ይችላል?››

‹‹እንጃልህ! የተጣለብህ ኃላፊነት ግን ከባድ ነው። ይህም የሆነው ድፍረትህና ብልህነትህ ተባብረው እንዲሳካልህ ይረዱሃል በማለት ነው። ይህን ትእዛዝ ከግቡ ለማድረስ ከቻልክ እንጀራ ወጣልህ ማለት ነው። እኔም የማውቀውን ያህል ስለ ስፍራው አስረድቼሃለሁ። በተረፈ አንድ ቆፋሪ ጠጋ ብትል በበለጠ ሊያስረዳህ ይችላል። በል እንግዲህ ይቅናህ።››

ሎኩሉስ እነዚህን ቃላት ተናግሮ ወደ ስፍራው ተመለሰ።

ማርሴሉስም በበኩሉ ራሱን ወደ ምድር አቀርቅሮ በዐሳብ ባሕር ውስጥ ገብቶ ይዋኝ ጀመር። በዐሳቡ ውስጥ ጣልቃ እየገባ ያ ሞት የሚሸነፍበትን መንገድ የሚያውጀው ጣፋጭ ዜማ ትዝ ይለው ነበር።

‹‹ለእርሱ ለወደደን
ከኃጢአታችንም
በደሙ ላነጻን።››

# የአፒያ አንቲካ ጎዳና

‹‹ያዘነ ሰልፈኛ መስለው በአፒያ አንቲካ ጎዳና ግራና ቀኝ የተሰለፉት መቃብሮች የኃያላን አፅም ጠባቂዎች ናቸው፡፡››

ማርሴሉስ ያስመዘግየት የታዘዘውን ለመፈጸም ተነሣ፡፡ ወታደር ሳያስከትል ምርመራውን ቀጠለ፡፡ ከመኮንኖች ሰፈር ተነሥቶ አፒያ አንቲካ በተባለው ጎዳና በኩል ግራ ቀኙን እየቃኘ የስለላ መልክ ያለውን ሽርሽሩን ጀመረ፡፡

ይህ ስመ ጥር ጉዳና በግራ በቀኙ በማዕረግ በተጠበቁ መቃብሮች የታጠረ ነበር፡፡ ከመንገዱ ራቅ ብሎ የሚያማምሩ ቤቶች ተደርድረው ይታያሉ፡፡

ከነዚህም ራቅ ብሎ የሚታየው የባላገሩ ሰፈር ነው፡፡ ከከተማይቱ ቅጥር ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ከሄደ በኋላ ወደ አንድ ክብ ሕንፃ ደረሰ፡፡ ሕንፃው በአራት ማዕዘን መልክ በተቀረፁ ታላላቅ ደንጊያዎች እጅግ ውብ በሆነ አኳኋን የተሠራ ነበር፡፡ ሕንፃው ጽኑ ሆኖ የተሠራ በመሆኑ በዘመናት ርዝመት ሳይበገር ግርማውንና ውበቱን ሳይቀንስ ኖሮአል፡፡ ማርሴሉስም ለጥቂት ጊዜ ቆም ብሎ ወደ ኋላው ተመለከተ፡፡ የሮም ከተማ በሩቅ ቆሞ ለሚመለከታት እንግዳ የምታበረክታቸው ብዙ ውበት ያላቸው ታሪካዊ ቅርሶች አሏት፡፡ ከሁሉ ይበልጥ የሚደንቀው ግራና ቀኝ የተሰለፉት መቃብሮች ናቸው፡፡ እነዚህ መቃብሮች የሮም ታላላቆች፤ የመኳንንትዋና የጥንታውያን ጀግኖችዋ ማረፊያ ስፍራ ነበሩ፡፡ ለመታሰቢያ በተቀረፁላቸው ደንጊያዎች ላይ የተጻፉት ቃላት በሕይወታቸው ሳሉ የነበራቸውን ምድራዊ ክብርና ገናናነት ወዳልታወቀው ሕይወት ሲሻገሩ የነበራቸውን የተስፋ ጭላንጭል ይገልጹ ነበር፡፡ እነዚህን መቃብሮች ብዙ ጠቢባን ያጌጡአቸውና ትውልድም ፈርሰው እንዳይረሱ የተንከባከባቸው ነበሩ፡፡

ማርሴሉስ በዚያ ቆሞ ከመቃብር በታች የዋሉትን የሮምን ኃያላንና ታሪካዊ ስሞች ዝክረ ነገር ሲያስላስል አንድ ሊቅ እንዲህ ሲል የተናገረው ትዝ አለው፡፡

- በፓርታ ካፒና በኩል አልፈህ የካላቲኒስን÷ የሲፒዮስን÷ የእነ ሰርቪልንና የእነሜቴሲን መቃብሮች ስትመለከት በዚያ ውስጥ ያረፉት ሰዎች ደስተኞች አይደሉም የሚያሰኝ ስሜት ያድርብሃልን?

ታላቋ መናገሻ ከወዲህም ከወዲያም የድንበርዋን ቅርንጫፍ

እያስፋች በመሄድዋ ከቀድሞው ወሰንዋ ውጭ የተሠሩት የመኖሪያ ቤቶች ብዙ ነበሩ። ከዚህ የተነሣ የከተማይቱ ወሰን የት እንደሚያልቅና የገጠሩ ድንበር የት እንደሚጀምር ለማወቅ አስቸጋሪ ነበረ።

ከሩቅ የሚተመው የከተማይቱ ድምፅ ተሰማው። ከወዲህ ወዲያ የሚርመሰመሱት ሠረገሎች ታዩት። የሕዝቡ ኮቴ ጆሮውን ነበኘው። ሐውልቶችና መቅደሶች፥ የሚያንጸባርቀው ቤተ መንግሥት፥ አያሌ ጉልላቶችና ታሪካዊ ዓምዶች ስፍራ ስፍራቸውን ይዘው ዐየ። ከዚህ ሁሉ ከፍ ብሎ የካፒቶሊን ኮረብታ የጁፒቴርን መቅደስ እንደ ዘውድ ቁንጮው ላይ ደፍቶ ይታይ ነበር። ዳሩ ግን ውብ ከሆነችውና የሕይወት ምልክት ከሚታይባት የሕያዋን መኖሪያ ከሆነችው መዲና ይልቅ የዝምታው ግርማ የሚያሸብረው የሙታን ሰፈር ያስደንቅ ነበር።

ማርሴሉስ በቅመበት ምድር ዙሪያ ዘመናት ያፈሩአቸው የሮም መሐንዲሶች የሥራ ውጤቶች በግራም በቀኝም ተሰልፈው ነበር። የሮም ኃያላን ሐውልቶች የብዙ ዘመናት ግርማቸውን እንደ ተጎናጸፉ ቆመዋል።

የሮም የጀግኖችዋ፥ የጠቢባኗ፥ የዝናዋና የብልጽግናዋ ዜና በነዚህ ሐውልቶች ላይ ተቀርፆ ሲነበብ የብዙ ዘመን ትዝታን ይቀሰቅስ ነበር። በዘመኑ የነበረው አረማዊ እምነት ዱካ በታሪክ ጎዳና ላይ በግልጽ ይታይ ነበር። ይህም ሃይማኖት በሚዳዊ ሥርዓቱ በውበትና በክብር ያጌጠ ቢሆንም፥ ለአማኞቹ መንፈሳዊ ቅርስ ሊያተርፍ አልቻለም። በሞቱት መታሰቢያ ደንጊያዎች ላይ የሚነበቡት ጽሑፎች የእምነትን ነገር ፈጽመው አያነሡም። ሟቾቹም፥ ሥጋዊ ኑሮንና የሕይወትን ደስታ የተቋደሱ መሆናቸውን ከመግለጽ ሌላ፥ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት የነበራቸውን ተስፋ የሚጠቁም አልነበረም።

ማርሴሉስ በዚያ በመቃብሮች ሰልፍ መካከል ቁሞ ከዐሳቡ ጋር ሲወጣና ሲወርድ እንደ ገና የሊቁ ቃል ትዝ አለው፦

- እዚህ ውስጥ ያረፉት ሰዎች ደስተኞች አይደሉም የሚል ስሜት ያድርብሃልን?

- እነዚህ እያደንኩ እንድይዛቸው የታዘዝኩት ክርስቲያኖች በጠቅላላው የፍልስፍና ትምህርቶች ውስጥ የማይገኘውን ምሥጢር የደረሱበት ይመስለኛል። የሞትን ፍርሃት ከማሸነፋቸውም ሌላ በደስታ መሞትን ያውቃሉ። በዕድሜ ላነሱትም ሆነ በጉልበት ለደከሙት ይህን የመሰለ ብርታት የሚሰጣቸው ምን ይሆን? የመዝሙራቸው ትርጉምስ ምንድን ነው? የእኔ እምነት በሕይወት እስካለሁ ድረስ ተደሳች

ያደርገኛል፤ የእነርሱ ግን ሞትን በጀግንነትና በመዝሙር እንዲጋፈጡ ይረዳቸዋል፡፡

ማርሴሉስ እዚያ እቆመበት ሆኖ በነዚህ ዐሳቦች ይንገላታ ጀመር፡፡ እነዚህን ክርስቲያኖች በእንዴት ያለ አኳኋን ፈልጎ ያግኛቸው? ብዙ ሰዎች በአጠገቡ ይወጡ ይወርዱ ነበር፡፡ የእርዳታ እጃቸውን ሊያቀብሉት የሚችሉ በመካከላቸው ያሉ አልመሰለውም፡፡ ታላላቅ ሕንፃዎች÷ ቅጥሮች÷ መቃብሮችና መቅደሶች ከበውት ነበር፡፡ ወደ አሰበበት ካታኮምብ ወደ ተባሉት ዋሻዎች የሚያደርስ ምልክት ምንም ሳይታየው ቀረ፡፡ በመጨረሻ የሚያደርገው ነገር ጥፍት አለበት፡፡

ጎዳናውን ተከትሎ ግራና ቀኝ የሚያያቸውን ቤቶች እየቃኘ በአጠገቡ የሚያልፉትን ሰዎች እየመረመረ ጉዞውን በዝግታ ቀጠለ፡፡ ዳሩ ግን ያለፈባቸው ስፍራዎችም ሆኑ ያያቸው ሰዎች እርሱ ሊደርስበት ከሚፈልገው ሥፍራ ጋር ምንም ግንኙነት ያላቸው መስለው ዐልታዩትም፡፡ ፀሐይዋ ተዘቀዘቀች፡፡ ቀኑም እየመሸ ሄደ፡፡ የማርሴሉስም ፍለጋ ምንም ፍሬ ሳያፈራ ቀረ፡፡

ካታኮምብ የተባለው ዋሻ ብዙ መግቢያዎች እንዳሉት በማስታወስ ተስፋ ሳይቈርጥ ፀሐይዋ እስክትጠልቅ ድረስ ፍለጋውን ለመቀጠል ወሰነ፡፡ ማርሴሉስ ብዙ ጊዜ ወጣ ወረደ፡፡ በአካባቢው የሚገኙትን አቅጣጫዎች ሁሉ አዳረሰ፡፡ በአንዱ መንገድ ብዙ ጊዜ ተመላለሰበት፡፡

ፀሐይዋ የአድማሱን ዘርፍ ነካች፡፡ ለዓይን ሊጨልም ሆነ፡፡ የማርሴሉስም ድካም በመጨረሻው የተፈለገበትን ፍሬ አበረከተ፡፡ አንድ ልጅ አስከትሎ የሚሄድ አንድ ሰውዬ ውልብ ሲል ታየው፡፡ ሰውዬው የለበሰው ልብስ ድሪቶ ከመሆኑም በላይ የአፈርና የእሸዋ ምልክት ይታይበት ነበር፡፡ ፊቱ ብዙ ጊዜ በእሥር ቤት ውስጥ እንደ ከረመ ሰው ፊት የገረጣ ነበር፡፡ ሁኔታው ሁሉ የወጣቱን መኰንን ጥርጣሬ ቀሰቀሰበት፡፡

ማርሴሉስ ወደ ሰውዬው ጠጋ አለና እጁን ከትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ‹‹እሸዋ ቆፋሪ ነህ? በል ተከተለኝ!›› አለው፡፡ ሰውዬው ቀና ብሎ ቢያይ የሚያነጋግረው በማዕረግ ልብስ የተዘናከተ መኰንን መሆኑን ተረዳ፡፡ አስተያየቱ አስፈራው፡፡ ከእጁም አምልጦ ተፈተለከ፡፡ ወዲያው የገባበት ጠፋ፤ ማርሴሉስ ሊከተለው ቢል ፍለጋው ጠፋበት፡፡

ዳሩ ግን ማርሴሉስ ባዶ እጁን አልቀረም፡፡ ሰውዬውን ተከትሎት የነበረውን ልጅ ‹‹በል አንተ ተከተለኝ›› አለው፡፡

ልጁም የማርሴሉስ አንጀት ቡጭቡጭ እስኪል ድረስ በእግሩ ላይ

ድፍት ብሎ ልመናውን አወረደው። ››ለእናቱ ስትል ማረኝ! እኔን ይዞህ የሄድክ እንደ ሆነ ጉዞሉ ይገድላታል።››

‹‹አይዞህ ምንም አላደርግህም።››

እንደዚህ ብሎ ከወጪ ወራጁ ራቅ ለማለት ልጁን እንደ ያዘ ከመንገድ ወጣ አለ።

ማርሴሉስም÷ ‹‹በል እንግዲህ እውነትዋን አውጣ። ማን ትባላለህ?›› ሲል ጥያቄውን ጀመረ።

ልጁም፤ ‹‹ስሜ ፖሊዮ ነው›› ሲል መልስ ሰጠ።

‹‹የት ትኖራለህ?››

‹‹ሮም።››

‹‹እዚህ ምን ትሠራለህ?››

‹‹ተልኬ ነው የመጣሁት።››

‹‹አብሮህ የነበረው ሰውዬ ማን ይባላል?››

‹‹አሸዋ ቆፋሪ ነው።››

‹‹ከእርሱ ጋር ምን ::ደርግ ነበር?››

‹‹ዕቃ ተሸክሞልኝ ነበር።››

‹‹ዕቃው ውስጥ ምን ነበረ?››

‹‹የሚበላ ነገር።››

‹‹ለማን ነበር የምትወስደው?››

‹‹እዚህ ሰፈር ለሚኖር አንድ ችግረኛ።››

‹‹የት ነው የሚኖረው?››

‹‹እዚህ ቅርብ ነው።››

‹‹ስማ አንተ ልጅ! እውነትዋን እንድታወጣ እፈልጋለሁ። ካታኮምብ ስለ ተባለው ስፍራ የምታውቀው ነገር አለ?››

‹‹ሰዎች ሲያወሩ ብቻ ነው የሰማሁት።››

‹‹እዚያ ውስጥ ገብተህ ታውቃለህ?››

‹‹አዎን÷ ጥቂቶቹ ውስጥ።››

‹‹እዚያ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል የምታውቃቸው አሉ?››

‹‹አንዳንድ የማውቃቸው ሰዎች እዚያ ይኖራሉ። አሸዋ የሚያወጡ ናቸው።››

‹‹ከሰውዬው ጋራ ወደዚያ ነበረ የምትሄደው?››

ልጁም ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ‹‹እኔ እዚያ ውስጥ ምን ሥራ አለኝ?›› አለ።

‹‹ሥራስ ነበረህ። ከሰውዬው ጋር ወደ ካታኮምቡ መሄድህ ነበር!››



ማርሴሉስና ፖሊዮ

‹‹ስማ አንተ ልጅ እውነትዋን እንድታወጣ እፈልጋለሁ።››

‹‹ወደዚያ እንዳይደረስ በሕግ የተከለከለበት ስፍራ ምን አደርግ እሄዳለሁ።››

ማርሴሉስም፥ ‹‹በል እንግዲህ እንደምታየው ቀኑ መሽቶአል። እዚያ ማዶ ወዳለው መቅደስ ሄጄ ጸሎት አደርሳለሁና ተከተለኝ›› አለው።

ልጁም ጥቂት ካመነታ በኋላ፤ ‹‹ቸኩያለሁ›› አለ።

‹‹ከእንግዲህ ወዲያ እሥረኛዬ ነህ። እኔ ደግሞ ጸሎቴን ላስተጓጉል አልችልም፤ ይልቁንም ተከተለኝና ጸሎቴን ሳደርስ ትረዳኛለህ።››

ልጁም በድፍረት፤ ‹‹አላደርገውም›› አለ።

‹‹ለምን?››

‹‹ክርስቲያን ነኝ።››

‹‹ክርስቲያን መሆንህን ሳትነግረኝ ዐውቄዋለሁ። በካታኮምቡ ውስጥ ዘመዶች አሉህ። ተልከህ የነበረውም ወደዚያ ነበር። ችግረኛ

ሰው የምትላቸው በዚያ ውስጥ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ነው። የምትወስደው ስንቅም ለእነርሱ ነበር።››

ልጁም ራሱን ወደ ምድር አቀርቅሮ አንዲት ቃል አልተነፍስ አለ።

‹‹አሁን የካታኮምቡን መግቢያ እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ።››

‹‹እባክህን ጌታዬ እንዲያው ምሕረት አድርግልኝ እንጂ ወደዚያ እንድወስድህ አትጠይቀኝ። ወዳጆቼን አሳልፌ ለመስጠት አልችልም።››

‹‹ከብዙዎቹ መግቢያዎች መካከል አንዱን ማሳየት ወዳጆችህን አሳልፎ እንደ መስጠት ሊቈጠርብህ አይችልም። እንዲያው ለመሆኑ ዘበኞቻችን መግቢያ መውጫያውን የማያውቁት ይመስልሃል?››

ልጁም ጥቂት ጊዜ ካሰበ በኋላ መርቶ ሊወስደው ያለውን ፈቃደኛነት ገለጸ። ማርሴሉስም እጁን ይዞ ተከተለው።

ልጁ አፒያ አንቲካ የተባለውን ጎዳና አቋርጦ ወደ ቀኝ ከታጠፈ በኋላ አንድ ደሳሳ ቤት ውስጥ ይዞት ገባ። ወደ ምድር ቤት ውስጥ ከገቡ በኋላ አንድ በር ከፍቶ በእጁ እያመለከተ ያውልህ አለው። ማርሴሉስም በትእዛዝ መልክ ወደ ዋሻው ውስጥ ለመግባት እፈልጋለሁ አለው።

‹‹እንዴት አድርገህ ብቻህን ለመግባት ትደፍራለህ?››

‹‹ክርስቲያኖች የሰውን ነፍስ አናጠፋም ይላሉ። እንዲህ ከሆነ ምን የሚያስፈራኝ ነገር አለ? ዝም ብለህ ምራኝ!››

‹‹ለመብራት የሚሆን ችቦ የለኝም።››

‹‹መብራት እኔ አለኝ፤ ዝም ብለህ ምራ!››

‹‹አልችልም!››

‹‹እምቢ ማለትህ ነው?››

ልጁም? ‹‹አዎን እምቢ ማለቴ ነው። ዘመዶቼና ወዳጆቼ ያሉት እዚያ ውስጥ ነው። አንተን መርቼ እዚያ ከማድረስ የሞት ሞት ብሞት ይሻለኛል›› አለ።

‹‹ለመሆኑ ደፋር ነህ። ሞት ምን እንደ ሆነ ዐታውቅ ይሆናል።››

‹‹ሞት ምን እንደ ሆነ የማላውቅ እኔ ነኝ? ለመሆኑ ክርስቲያን የሆነ ሞትን የሚፈራ ይመስልሃል? ብዙዎች ወዳጆቼ በጭንቀት ሲሞቱ ዐይቻለሁ። ሲቀበሩም በቀብራቸው ላይ ተገኝቻለሁ። ፍጹም ወደዚያ ስፍራ አልመራህም። ብትፈልግ እሥር ቤት ውሰደኝ።››

‹‹ወደ እሥር ቤት የወሰድኩህ እንደ ሆነ ዘመዶችህ ምን ይላሉ ለመሆኑ እናት አለህ?››

ልጁም የእናቱ ነገር ሲነሣ ስቅ ስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡

‹‹በለቅሶህ የእናትህን መኖር ተረድቼአለሁ፡፡ ከእናትህ ጋር እንድትገናኝ ምራና ውሰደኝ፡፡››

‹‹አሳልፌ ለመስጠት በፍጹም አልችልም፡፡ ቀድሚ መሞት ይሻለናል፡፡ ውሰድና የፈለግኸውን አድርገኝ፡፡››

ማርሴሉስም፤ ‹‹ክፉ ነገር ባስብ ኖሮ ብቻዬን የምመጣ ይመስልሃለን?›› አለው፡፡

‹‹የቄሣር መኮንን የተጠሉትን ክርስቲያኖች ሊያጠፉ እንጂ ሌላ ምን ሊያደርግ ይመጣል?››

‹‹ስማ አንተ ልጅ፤ እኔ የመጣሁት ክፉ ነገር አስቤ አይደለም፡፡ መርተህ ክርስቲያኖች ያሉበት ዘንድ ብታደርሰኝ ክፉ ነገር እንደማላደርስባቸው እምልልሃለሁ፡፡ እዚያ ከገባሁ በኋላ የእነርሱ እሥረኛ ነኝ ማለት ነው፡፡ የፈለጉትን ነገር ሊያደርሱብኝ ይችላሉ፡፡››

‹‹አሳልፌ አልሰጣቸውም ብለህ ትምላለህ?››

‹‹ዘለዓለማዊ የሆኑት የቄሣር አማልክት ያጥፉኝ›› ሲል ማርሴሉስ መሐላውን ደረደረ፡፡

‹‹እንግዲያው በጸጥታ ተከተለኝ፡፡ መብራትም አያስፈልገንም፡፡››

ልጁም ማርሴሉስን ከኋላ አስከትሎ ዋሻው ውስጥ ጥልቅ አለ፡፡

## ካታኮምቡ ውስጥ

ጉዞአቸው ድቅድቅ ካለው ጨለማ ውስጥ አደረሳቸው፡፡ መተሳሰፊያው መንገድ እየሰፋ ሄደ፡፡ በመጨረሻም አዘቅዝቆ ወደሚወርድ አንድ ደረጃ ደረሱ፡፡ ማርሴሉስም የልጁን ጨርቅ ሙጥኝ ብሎ እንደ ያዘ ተከተለው፡፤ ስፍረራው ፍርሃትን የሚቀሰቅስ ነበር፡፡ ማርሴሉስም በገዛ ፈቃዱ መሰሎቹ የሮም ባለሥልጣኖች በምድር ገጽ ላይ እንዳይኖሩ አባረው አሠቃቂ ወደ ሆነው የምድር ማኅፀን ውስጥ እንዲገቡ ወደ አደረጉአቸው ሰዎች ይገሰግስ ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች ማርሴሉስን የሚቈጥሩት እንደ አጥፊቸው መሆኑ ጥርጥር አልነበረውም፡፡ ዳሩ ግን የእነዚህን ሰዎች ደግነትና ትሕትና ከሩቅ የተመለከተ በመሆኑ ክፉ ነገር ይደርስብኛል የሚል ሥጋት አላደረበትም፡፡ በዚያ ዓይን ቢወጋ በማይታይበት ጨለማ ውስጥ፤ ዘወርዋራነቱ ራስ በሚያዞረው መንገድ ይመራው የነበረው ወጣት ልጅ እንኳን የፈለገውን ጉዳት ሊያደርስበት ይችል ነበር፡፡ ይህም ስሜት አላሠጋውም፡፡ ማርሴሉስን እስከዚህ ድረስ ገፋፍቶ ያደረሰው የክርስቲያኖችን ምሥጢር በበለጠ የማወቅ ጉጉት ነበር፡፡

ቀደም ብሎ በመሐላው እንደ ገለጸውም ሁሉ ይህንን ጉብኝቱን ክርስቲያኖች ለማጥፊያ መሣሪያ ሊያደርገው በፍጹም አላሰበም። ጥቂት ጊዜ ተሽቈልቊለው ከወረዱ በኋላ የሚረግጡት መንገድ እየቀና መሄድ ጀመረ። ወዲውም የምድጃው እሳት ጭል ጭል እያለ ወደሚነድበት በብረት መዝጊያ ወደ ተዘጋ አንድ ክፍል ደረሱ። የልጁ የዚያን ዘወርዋራ ስፍራ ማወቅ በጣም የሚያስደንቅ ነበር። ልጁም እደረሰበት ክፍል ውስጥ ገብቶ ወለሉ ላይ ካሉት ችቦዎች አንዱን አበራና ጕዞአቸውን ቀጠሉ።

የመቃብር ስፍራ ከሌሎች ስፍራዎች ሁሉ የተለየ ስሜት አለው። የቦታው መክበድ ወይም የአፈሩ ሽታ ብቻ ሳይሆን ለስፍራው አስፈሪ የሆነ ግርማ የሚሰጠው ይህ ነው የማይባል ነገር አለው። በሰዎች አእምሮና አካል ላይ የሚያርፈው ምናልባት የሚቆቹ ጥላ ይሆን? በካታኮምቡ ውስጥ ሲገቡ የሚሰማው ስሜት ይህን የመሰለ ነው። የስፍራው ቅዝቃዜና ርጥበት በቀጥታ ከሞት ዓለም የመጣ ይመስላል። እዚያ ውስጥ የገባ ሁሉ ምሥጢራዊ የሆነው የሞት ኃይል ምን ያህል እንደሚዘገንን ሳይሰማው አይወጣም። ወጣቱ ፖሊዮ መንገዱን በመምራት ማርሴሉስም በመከተል ጕዞአቸውን ቀጠሉ። እዚያ አሠቃቂ የሆነ ስፍራ ውስጥ የፀሐይ ጮራ ወይም የቀን ብርሃን ገብቶበት ዐያውቅም። ከዚህ የተነሣ ጨለማው የሚጋፋና ለመዳሰስ እንኳ የሚቻል ይመስላል። የችቦው ጭላንጭል ከጥቂት እርምጃዎች በላይ ጨለማውን ሊያስወግደው አይችልም ነበር።

ይከተሉት የነበረው መንገድ በጣም ዘወርዋራና ብዙ ቅርንጫፍ መንገዶች ያሉት ነበር። ፖሊዮም ድንገት ቆም አለና ለማርሴሉስ አንድ ጎድጓዳ ስፍራ ዐሳየው። እርሱም ጐምበስ ብሎ ቢመለከት መጨረሻው የማይታይ አዘቅት መስሎ ታየው።

‹‹ወዴት የሚያደርስ ነው?››

‹‹ወደ ታች።››

‹‹ከሄድንባቸው ሌላ ወደ ታች የሚያወርዱ መንገዶች አሉ?››

‹‹ብዙዎች አሉ! አንድ ጊዜ እነዚህኑ መንገዶች ይዤ እስከ ሦስት ፎቆች ወደ ታች ወርጃለሁ። እሸዋ ቆፋሪዎቹማ በጣም ወደ ታች እንወርዳለን ይላሉ።››

የመንገዱ ዘወርዋራነት እየባሰበት ሄደ። ማርሴሉስም ግራ ገባው። ጕዞአቸውን ከጀመሩ አንሥቶ የሄደበት ርቀት አንድ ወይም ዐሥር ኪሎ ሜትር መሆኑን ሊለይ አይችልም ነበር።

ዐ/ሥር ኪሎ ሜትር መሆኑን ሊለይ አይችልም ነበር።

እያደር እያደር ግን የተጨነቀው ዐሳቡ እየሰከነ መሄድ ጀመረ። ግራ የገባውም አእምሮው በሌሎች ነገሮች ተጠመደ። በሚያልፋባቸው ስፍራዎች ግራና ቀኝ እየተዘዋወረ ምርመራውን ቀጠለ። በዋሻዎቹ ግራና ቀኝ ባሉት ግድግዳዎች ውስጥ ተፈልፍለው እንደ መደብ የተሠሩ ብዙ ስፍራዎች ይታዩ ነበር። እያንዳንዱ መደብ አጠገብ ጽሑፍ ያለበት ትንሽ ስሌዳ ተሰቅሎአል።

በስሌዳዎቹ ላይ የተቀረፁት ጽሑፎች ስፍራዎቹ የክርስቲያኖች መቃብሮች መሆናቸውን ይገልጹ ነበር። ማርሴሉስም ቆም ብሎ ጽሑፎቹን ለማንበብ ጊዜ ያጠረው ቢሆንም፥ በሚያልፋበት ጊዜ ዓይኖቹ እንዲህ በሚሉት ቃላት ላይ ያርፍ ነበር።

- ሐኖሪያ በሰላም ዐረፈች።

- ፋውስታ በሰላም።

ባያቸው ስሌዳዎች ላይ ሁሉ ‹‹ሰላም›› የተባለው ቃል ተቀርፆበት ተመለከተ።

- ይህን በመሰለው አሠቃቂ ስፍራ ውስጥ ሆነው ሞትን ከመናቅ የማይመለሱት እነዚህ ክርስቲያኖች እንዴት የሚያስገርሙ ሰዎች ናቸው?

ዓይኖቹ ስፍራውን እየተላመዱት ሄዱ። የመንገዱ ግራና ቀኝ መጥበብ ጀመረ። የዋሻው ጣሪያ ራሳቸውን ነካ። በመጨረሻም አጎንብሰው በዝግታ መሄድ ግድ ሆነባቸው። የዋሻው ግድግዳ የመጀመሪያዎቹ አሸዋ አውጭዎች እንደ ቆፈሩት የተተወ ወጣ ገብ ነበር። በምድር ውስጥ ሊበቅሉ የሚችሉ ዕፅዋት መሬቱን ከማልበሳቸው የተነሣ ለስፍራው ልዩ የሆነ ቅዝቃዜና ርጥበት ሰጥተውታል። ከችቦው የሚወጣው ጢስ አነስተኛ ከሆነው አየር ጋር ሲቀላቀል ሳንባዎችን እፍን ያደርግ ነበር።

ከመቶ በላይ የሆኑ ዘወርዋራ መንገዶችን አለፉ። አያሌዎች ቅርንጫፍ መንገዶች ወደየአቅጣጫው ሲሰራጩ ይታዩ ነበር።

ማርሴሉስ የመንገዱን ውስብስብነት በመረዳቱ ማምለጫ በሌለው አኳኋን ከላይኛው ዓለም የተለየ መሆኑን ተረዳ። ነፍሱ በዚያ ወጣት ልጅ እጅ ውስጥ መሆንዋን ተገነዘበ።

‹‹ለመሆኑ እዚህ ውስጥ ከገቡ በኋላ መንገዳቸውን የሚስቱ አሉ?››

‹‹አዎን፤ ብዙዎች ይስታሉ።፡››

‹‹መጨረሻቸውስ ምን ይሆናል?››

‹‹አንዳንድ ጊዜ የሚያውቁት ሰው እስኪያገኙ ድረስ ዝም ብለው ይዞራሉ። አንዳንድ ጊዜ የደረሱበት ሳይታወቅ ጠፍተው ይቀራሉ። በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቻችን መንገድን ደኅና አድርገን ስለምናውቀው ልንሳሳት አንችልም። መንገዱ ቢጠፋብንም ዞረን ወደ አንድ ምልክት ወዳለው ስፍራ ለመድረስ እንችላለን።››

ማርሴሉስን የታናናሽ መቃብሮች በብዛት መታየት በጣም አስደነቀው። የሕፃናት መቃብሮች መሆናቸውንም ከፖሊዮ ጠይቆ ተረዳ። ይህም አንድ ልዩ የሆነ ስሜት ፈጠረበት።

- ሕፃናት ንጹሖቹ? ምንም ክፉ ነገር ሲሠሩ የማይችሉት? እዚህ ምን ያደርጉ ገቡ? መቃብራቸው ላይ የፀሐይ ጮራ በሚያርፍበትና አበባዎች በሚፈኩበት ስፍራ ምነው ቢቀበሩ? የቡቃያነት ዘመናቸውን ያሳለፉት በእነዚህ በጨለመባቸው መንገዶች ውስጥ ወዲያ ወዲያ በማለት ይሆን? ስደትና መከራን በመሸሽ ወዲህ የገቡትን ሰዎች መከራ ተካፋይ ሆነው ይሆን? ዕድሜያቸው በለጋነቱ እንዲቀጭ ነውር የሌለው መንፈሳቸው ከሥጋቸው እንዲለይ ያደረገው የዚህ አሠቃቂ ስፍራ መርዘኛ አየር ይሆን?

ማርሴሉስ÷ ‹‹ጉዞአችንን ከጀመርን ብዙ ጊዜ ሆኖናል። ልንደርስ ነው?››

ፖሊዮ÷ ‹‹አዎን÷ እንግዲህ ምንም አልቀረን።››

ማርሴሉስም ክርስቲያኖችን ከእንደዚህ ያለው ስፍራ ውስጥ አድኖ ለመያዝ መሞከር ድካምን ብቻ የሚያተርፍ ከንቱ ልፋት መሆኑን ተረዳ። አንድ የጦር ሠራዊት ቢገባበት ክርስቲያኖች ያሉበት አቅራቢያ እንኳ ለመድረስ አይችልም። ከመንገዱ ርዝመትና ከዘወርዋራነቱ የተነሣ የገቡት ሁሉ ዕድሜያቸውን እንደሚፈጁት የታወቀ ነው።

ማርሴሉስ በድንገት ከሩቅ ድምፅ ሰማ። ድምፁም ይህ ነው የማይባል ዜማ ያለው ነበር። ከፊታቸው የተዘረጋውን ረጅም መንገድ አቋርጦ ሰማያዊ በሆነ ስልቱ ንቁ የሆነውን ጆሮውን ጎበኘው።

ጉዞአቸውንም እንደ ቀጠሉ የብርሃን ጮራውን በጨለማው ውስጥ ፍንጥቅጥቅ ሲያደርግ ይታያቸው ነበር። ድምፁ እየቀረበ ሄደ። አንዳንድ ጊዜ የዘማሪዎችን ዜማ÷ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የጸሎተኞችን ልመና ይመስል ነበር። አንድ መታጠፊያ መንገድ ላይ ደረሱ። ግሩም የሆነ ትርኢይት ፊታቸው ላይ ድቅን አለ። ፖሊዮም ማርሴሉስን ‹‹ቁም!›› ብሎ አዘዘውና የያዘውን ችቦ አጠፋ። ማርሴሉስም በመታዘዝ

ካለበት ቁሞ ከፊቱ ያለውን ነገር በመገረም ትክ ብሎ ይመለከት ጀመር። ማርሴሉስን የታየው አንድ በጣም አነስተኛ ክፍል ነበር። በክፍሉም ውስጥ ከሕፃናትና ከሴቶች ጋር መቶ የሚሆኑ ሰዎች በመጣበብ ተቀምጠው ነበር። በክፍሉም በአንደኛው ማዕዘን አንድ ጠረጴዛ ይታያል። ከጠረጴዛው በስተኋላ አንድ በዕድሜ ገፋ ያለ ሰው ቆሞ ነበር። እርሱም የስብሰባው መሪ ይመስላል። በስፍራው ውስጥ ጭል ጭል የሚል የጧፍ ብርሃን ይታይበታል። ይህም አነሥተኛ የብርሃን ጭላንጭል ለተሰበሰቡት ሰዎች አስፈሪ የሆነ መልክ ሰጥቶአቸዋል። ጠቅላላው የሰዎቹ መልክ ማርሴሉስ የተገናኘውን አሽዋ ቆፋሪ የመሰለ በሥጋት የገረጣና የከሳ ነበር። ዳሩ ግን በዚያ ተሰብስበው ሲታዩ ምንም የሐዘን÷ የጭንቀትና የተስፋ መቍረጥ ምልክት በገጻቸው ላይ ዐይታይባቸውም። ወደ ላይ ያሻቀበው አስተያየታቸው ተስፋን÷ ደስታንና ድል አድራጊነትን ያበሥር ነበር። ማርሴሉስ ባየው ሁሉ ተነካ። ከዚህ ቀደም በመጠኑ ላየውና ለሰማው ከእርሱ ሥውር ለሆነው የክርስቲኖች ጀግንነት ተስፋና ሰላም ማረጋገጫውን አገኘ። ማርሴሉስ እቀመበት ስፍራ ሆኖ ሲያዳምጥ በስብሰባው ላይ የነበሩት በኅብረት የሚከተሉትን ቃላት ሲያዜሙ ሰማ፡-

‹‹ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ÷
ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው
የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ÷
መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው።
ጌታ ሆይ÷
የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው?
አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና
የጽድቅህም ሥራ ስለ ተገለጠ
አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ
በፊትህም ይሰግዳሉ።››

ከመዝሙሩ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ ሆነ። የስብሰባው መሪ ተነሥቶ ከአንድ ጥቅል ብራና አነበበ። የንባቡ ቃላት ለማርሴሉስ ፍጹም እንግዳ ነገር ሆነበት። ብንባቡ የተሰማው ቃል ስለ ነፍስ ሕያውነትና ከሞት በኋላ ስላለው ዘላለማዊ ሕይወት የሚያስረዳ ነበር። በስብሰባው ላይ የነበሩት የሚነበበውን ቃል ግሩም በሆነ እርጋታ ያዳምጡ ነበር። የስብሰባው መሪ ባነበበው ቃል ምክንያት የተሰማውን ደስታ ከልብ

ገለጠ፡፡ ተሰብሳቢዎቹም አሜን በማለት የደስታውና የተስፋው ተካፋዮች መሆናቸውን አሰሙ፡፡

ምንም እንኳ ማርሴሉስ የተነበቡትን ቃላት ምሥጢር ለመረዳት ባይችልም ስሜቱ ልቡን ነካው፡፡ ‹‹ሞት ሆይ÷ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ÷ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው፤ የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡›› እነዚህ ቃላት ዐዳዲስ የሆኑ ዐሳቦች የያዘ አንድ ዐዲስ ዓለም ከፈቱለት፡፡ ኃጢአት÷ ሞትና ክርስቶስ የተባሉት በመንቃት ላይ የነበረችውን ነፍሱን በዐሳብ እንድትባክን አደረጓት፡፡ የክርስቲያኖችን ምሥጢር ለማወቅ የነበረው ፍላጎት እየተጋጋለ መሄዱን ቀጠለ፡፡



የስብሰባው መሪ ፊቱን ወደ ሰማይ አቅንቶ እጆቹን ዘርግቶ ከልብ የሆነ ጸሎት አደረሰ፡፡ ሁሉን ቻይ ለሆነውና ለማይታየው አምላክ ኃጢአቱንና ምስቁልናውን አስታወቀ፡፡ በክርስቶስ ምክንያት ስለ ተገኘውም የኃጢአት ስርየት ምስጋናውን አቀረበ፡፡ መንፈስ ቅዱስ የማኅበሩን አባሎች ሁሉ እንዲቀድስ ልመናውን አሰማ፡፡ ጭንቀታቸውን በመዘርዘር ከችግራቸው የሚወጡበት ረድኤት እንዲደርስላቸው በሕይወት ሳሉ በእምነት እንዲራመዱና የሞታቸውም ጊዜ ሲደርስ እንዲጸኑ÷ በኢየሱስ ስም ምክንያት ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት ምእመናን ቍጥር እየበዛ እንዲሄድ ያለውን የጋለ ምኞት አስታወቀ፡፡

ቀጥሎም የሚከተሉት ቃላት ተዘመሩ፡-

‹‹እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን
በሰዎች መካከል ነው
ከእነርሱም ጋር ያድራል፤
እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ
እግዚአብሔር አምላክም ከእነርሱ ጋር ሆኖ
አምላካቸው ይሆናል፤
እንባዎችን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል
ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም
ሐዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ
ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም።
የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና
በረከትና ክብር ጥበብም
ምስጋና ውዳሴም ኃይልም ብርታትም
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ
ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን።››

በስብሰባው ላይ የነበሩት ሰዎች መበታተን ጀመሩ። ወዲያው ፖሊዮ ማርሴሉስን አስከትሎ ከስብሰባው ክፍል ውስጥ ገባ። የሚያንጸባርቀውን የመኰንን ልብሱን በማየታቸው በስብሰባው ላይ የነበሩት ሁሉ ክልክ ያለፈ ደነገጡ። በየስርቻው ውስጥ ገብተው ለማምለጥ ሲሞክሩ ማርሴሉስ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አላቸው።

‹‹ክርስቲያኖች ሆይ! አትፍሩ÷ እኔ የመጣሁት ብቻዬን ነው። አሁን የምገኘውም እጃችሁ ውስጥ ነው።››

ይህን ቃል በመስማታቸው ፈጋ እንደ ማለት ብለው አትኩረው ይመለከቱት ጀመር። የስብሰባው መሪ ወደ ማርሴሉስ ጠጋ ብሎ በሚገባ ተመለከተው።

‹‹ማን ትባላለህ? በምድር ላይ ማረፊያ እንዲሆነን ይህ ስፍራ ቢቀረን ከዚህም ልታጠፋን መጣህ?››

‹‹ክፉ ነገር ያደርግብናል ብላችሁ አትጠርጥሩኝ። እንደምታዩት የመጣሁት አንድ ራሴን ነው። በእጃችሁ ውስጥ ገብቻለሁ። እንደ ፈቃዳችሁ ልታደርጉኝ ትችላላችሁ።››

‹‹የቄሣር መኰንን ከእኛ የሚፈልገው ምን ነገር አለ? ወንጀለኛ

ሕይወትህ በአደጋ ውስጥ ነው?››

‹‹አይደለም። እኔ አንድ ታላቅ ሥልጣን ያለኝ የቄሣር መኰንን ነኝ። ዕድሜዬን በሙሉ እውነትን በመፈለግ ላይ እገኛለሁ። ክርስቲያን ስለምትባሉት ሰዎች ብዙ ነገር ሰምቻለሁ። ጊዜው የስደት በመሆኑ በሮም ውስጥ ከእናንተ ወገኖች ጋር ተገናኝቶ መነጋገር በጣም አዳጋች ሆኖ አገኘሁት።››

ሽማግሌው ተሰብስበው የነበሩትን ክርስቲያኖች ወደ የቦታቸው እንዲሄዱ አመለከታቸው። በተረጋጋ መንፈስ ሁሉም ወደ ስፍራቸው ተሰራጩ። ሽማግሌው ከዐዲሱ እንግዳ ጋር ንግግሩን በመቀጠል ላይ ሳለ አንዲት ፊቷ የገረጣ ሴት ወደ ፖሊዮ መጥታ እጁን ለቀም አደረገችው።

‹‹ምነው እስካሁን ቆየህ ልጄ?››

‹‹ይኸ መኮንን ነው ይዞ ያዘገየኝ።››

‹‹እንኳን ደኅና መጣህልኝ ብቻ። ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?››

‹‹ደኅና ሰው ሳይሆን አይቀርም። ምሥጢሩን ሁሉ ሲነግረን አልሰማሽም?››

ሽማግሌውም ሴትዮዋን፡-

‹‹ሴሲሊያ÷ ‹‹እስቲ ጥቂት ጊዜ እዚህ ቆዪ እላት።››

ሴቲቱም ከጥቂቶች ሰዎች ጋር መሪያቸው አጠገብ ቆመች። ሖኖሪዮስም ንግግሩን በመቀጠል ማርሴሉስን እንዲህ አለው፡-

‹‹ስሜ ሖኖሪዮስ ይባላል። የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በሽምግልና ሥራ አገለግላለሁ። ሳይህ ደኅና ሰው ትመስለኛለህ። ከእኛ የምትፈልገው ነገር እንዳለ አስረዳን።››

‹‹እኔም ማርሴሉስ እባላለሁ። በቄሣር ሠራዊት ውስጥ በመኰንንነት አገለግላለሁ።››

ሽማግሌውም እጁን እያጨበጨበ÷ ‹‹ወየው ጠፋን!›› የሚል ተስፋ የመቍረጥ ድምፅ አሰማ። አጠገቡ የቆሙትም በፍርሃት ማርሴሉስን ትክ ብለው ይመለከቱት ጀመር።

ሴሲሊያም እያለቀሰች፡- ‹‹ምነው ፖሊዮ! አሳልፈህ ትሰጠን?›› አለችው።

# የክርስቲያን ምሥጢር

‹‹እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ አምላክ በሥጋ ተገለጠ...፡፡››

ወጣቱ መኰንን ስሙ በሰዎቹ ዘንድ የፈጠረውን ድንጋጤ በማየቱ እጅግ ተደነቀ፡፡

‹‹ለምን በፍርሃት ትንቀጠቀጣላችሁ? ይህ ሁሉ ድንጋጤ በእኔ ምክንያት ነው?››

ሖኖሪዮስም ከድንጋጤው ፋታ ሳያገኝ እንዲህ አለ፤ ‹‹ምንም እንኳ ወደዚህ ስፍራ እንድንሰደድ ብንገደድም ከከተማይቱ ጋር የዘወትር ግንኙነት አለን፡፡ እኛን ፈልጎ ለመያዝና ለማሳደድ ብርቱ የሆነ ጥረት ማድረግ እንደ ተጀመረ ሰምተናል፡፡ ይህንንም ተግባር እንዲፈጽም የተሾመው ማርሴሉስ የተባለው የቄሣር መኰንን መሆኑን ተረድተናል፡፡ የጠላቶቻችን አውራ የሆንከው ይኸው በመካከላችን ትገኛለህ፡፡ ታዲያ ፍርሃትና ድንጋጤ ይብዛብን? እንዲያው ለመሆኑ ልታጠፋን እዚህ ድረስ ለምን መጣህ?››

ማርሴሉስም÷ ‹‹ምንም እንኳ የጠላቶቻችሁ አውራ ብሆንም እኔን ለመፍራት ምንም ምክንያት የላችሁም›› ሲል ተናገረ፡፡

‹‹አሁን ያለሁት ከሥልጣናችሁ ሥር ነው፡፡ እዚህ ልታስቀሩኝ ብትሹ የማመልጥበት መንገድ የለኝም፡፡ ልትገሉኝም ብትፈልጉ እንዴት አድርጌ ነፍሴን ማዳን እችላለሁ? እንደምታዩት በመካከላችሁ መውጫና መግቢያ የሌለው ሆኛለሁ፡፡ አሁን ያለሁበት ሁኔታ ብቻ እኔን መፍራት የሌለባችሁ መሆኑን ሊያረጋግጥላችሁ ይችላል፡፡››

ሖኖሪዮስም ረጋ ባለ አኳኋን እንዲህ አለ፦

‹‹እርግጥ ነው፤ አሁን ያልከው ሁሉ እውነት ነው፡፡ እኛ ካልረዳንህ በቀር ወደ መጣህበት ስፍራ መመለስ አትችልም፡፡››

‹‹እንግዲያውስ የምነግራችሁን ነገር አድምጡኝ፡፡ እንደምታዩኝ የሮም ወታደር ነኝ፡፡ ትውልዴም በእስፓኝ አገር ነው፡፡ አስተዳደጌ በሥርዓትና በግብረ ገብነት የታነፀ በመሆኑ ከሕፃንነቴ ጀምሮ አማልክትን መፍራትና የሚፈለግብኝን ግዴታ መፈጸም ተምሬአለሁ፡፡ ብዙ አገሮችን ተዘዋውሬ ዐይቻለሁ፡፡ እስከ ዛሬ አብዛኛውን ጊዜዬን ያሳለፍኩት በወታደርነት አገልግሎት ላይ ነው፡፡ ዳሩ ግን እስከ ዛሬ ስኖር የእምነትን ነገር ችላ ብዬ ዐላውቅም፡፡ ትርፍ ጊዜዬን የማሳልፈው የግሪክና የሮምን ፍልስፍና በማጥናት ነው፡፡ ይህም ጥናቱ እታመንባቸው

የነበሩትን ከራሴ እንኳ የማይሻሉትን አማልክታችንን እርግፍ አድርጎ ወደ መተው አድርሶኛል፡፡››

‹‹ከፕላቶና ከሲሴሮ የአንድ ከፍተኛ አምላክን መኖርና ለእርሱም መታዘዝ እንዳለብኝ ተረድቼአለሁ፡፡ ይህንን አምላክ በሚገባ ላውቀው የምችለው እንዴት አድርጌ ነው? ፈላስፎች ከሞት በኂላ ያለውን ሕይወት ድንቅ በሆነ ቃላት ያስረዳሉ፡፡ እንደ እኔ ያለ ተራ ሰው ግን ምሥጢሩን ሊደርስበት አይችልም፡፡ ከልብ የምመኘው የዚህን ሁሉ ምሥጢር አጣርቼ ለማወቅ ነው፡፡

‹‹በየጊዜው የምጠይቃቸው ካህናታችን ምንም ነገር ሊያስረዱኝ አልቻሉም፡፡ እነርሱ ሲፈጽሙ የሚታዩት ራሳቸው እንኳ የማያምኑባቸውን አሮጌ ወጎችና ሥርዓቶችን ነው፡፡ የጥንቱ እምነት ሙት ሆኖአል፡፡ ሰዎችም ስለ እርሱ ግድ የላቸውም፡፡

‹‹በተዘዋወርኩባቸው አገሮች ሁሉ የክርስቲያኖችን ወሬ ሰምቻለሁ፡፡ የምኖረው በወታደሮች ሰፈር በመሆኑ ከእነርሱ ጋር ተገናኝቶ የመነጋገር ዕድል እስከ ዛሬ ደረስ አላጋጣመኝም፡፡ እኔም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሁኔታቸውን ለመረዳት ሆን ብዬ አልተነሣሁም፡፡

‹‹ስለ ክርስቲያኖች የሰማሁት የግብረ ገብነት እጦት÷ ነውር የሆነ ርኲሰት÷ አጥፊ የሆነ ትምህርት ወሬ ብዙ ነው፡፡ እኔም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሰማሁትን ወሬ ሁሉ እንደ እውነት አድርጌ እቈጥር ነበር፡፡

‹‹በቅርብ ቀን ኮሎሲዩም እተባለው የስፖርት አደባባይ ውስጥ ገብቼ ነበር፡፡ እዚያ ውስጥ ሳለሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ክርስቲያኖች ጥቂት መረዳት ጀመርኩ፡፡ ማከር የተባለው ፍርሃት ምን እንደ ሆነ የማያውቀው ተዋጊ ስሕተት መስሎ የታየውን ነገር ከማድረግ ይልቅ ሕይወትን አሳልፎ መስጠትን እንደ መረጠ ዐየሁ፡፡ ከዚህ ሁሉ ይልቅ÷ አንድ በዕድሜ የገፋ ሽማግሌ የሞትን ወንዝ በደስታና በፈግግታ ሲሻገር ዐየሁ፡፡ ወጣቶች ልጃገረዶች የድል መዝሙር በመዘመር ራሳቸውን ለአውሬዎች ሲሰጡ የዓይን ምስክር ነበርኩ፡፡

‹‹ለእርሱ ለወደደን
ከኃጢአታችንም
በደሙ ላጠበን፡፡››

የማርሴሉስ ንግግር በአድማጮቹ ዘንድ ልዩ ልዩ የሆነ ስሜትን ፈጠረ፡፡ ዓይኖቻቸው በናፍቆትና በደስታ በሩ፡፡ የማከርን ስም ባነሣ ጊዜ ሁሉም ምሥጢር ባለው ፈገግታ ተጠቃቀሱ፡፡ ስለ ሽማግሌው ሞት

ሲያወራ ሖኖሪዮስ ወደ ምድር አቀረቀረ። ስለ ወጣቶቹ ልጃገረዶች ሲናገር የሁሉም ዓይኖች በእንባ ረጠቡ።

‹‹በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞት ሲሸነፍ ዐየሁ። በጦር ሜዳ ላይ ማንኛውም ወታደር ከእኔ ጭምር በቈራጥነት መሞት ወታደር የሆነ ሁሉ ግዴታ ነው። ዳሩ ግን ሲሞቱ ያየኋቸው ክርስቲያኖች በመሞታቸው ሲደሰቱ ነው።

‹‹ከእነርሱ ውስጥ አንድም ወታደር አልነበረም። ያንን አስደናቂ ቈራጥነትን ካሳዩት መካከል አብዛኞቹ ወጣቶች ነበሩ።

‹‹ከዚያን ቀን ወዲህ በዐሳቤ ውስጥ ሌላ ነገር አልገባም፤ የወደዳችሁ ማን ነው? ከኃጢአታችሁ የሚያጥባችሁስ ማን ነው? ያን የመሰለ ከፍተኛ ድፍረትና ተስፋ በውስጣችሁ እንዲነግሥ ያደረገስ ማን ነው? እንዲህ ደጋግሮ እንድትጸኑ የሚያደርጋችሁስ ምንድን ነው? ከጥቂት ጊዜ በፊትስ ትጸልዩ የነበረው ለማን ነበር? እንደምታውቀት የበታቾቼን ልኬ እንዳጠፋችሁ ተሹሜአለሁ። መጀመሪያ ግን ስለ እናንተ በሚገባ ለማወቅ ምኞቴ ነው። የታላቁን አምላክ ስም ጠርቼ ይህ የአሁኑ ጉብኝቴ ክፉ ነገር ሊያስከትልባችሁ እንደማይችል እምልላችኋለሁ፡፡ እንግዲህ የክርስትና ምሥጢር ምን እንደ ሆነ አስረዱኝ።››

ሖኖሪዮስም የሚከተሉትን ቃላት ለማርሴሉስ ተናገረ፡-

‹‹አሁን የተናገርከው ሁሉ ከቅን ልብ የመነጨ እውነተኛ ቃል ነው። በንግግርህም የሰላና የጠላትነት ምኞት እንደሌለህና ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ልብህ ይመኘው የነበረውን የእውነት ነገር እንድትረዳ ወደዚህ ስፍራ የመራህ መንፈስ ቅዱስ ራሱ መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ። ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ ከበር እንዲመለስ አይደረግም። ስለዚህ ልትደሰት ይገባል።

‹‹እዚህ ውስጥ ያየኻቸው ወንዶች ሆኑ ሴቶች ንብረታቸውን÷ ወዳጆቻቸውን÷ የነበራቸውን ክብርና ሀብት÷ እርግፍ አድርገው ትተው ለክርስቶስ ሲሉ በረሃብና በፍርሃት÷ በጭንቀት ለመኖር የመረጡ ናቸው። ሕይወታቸውን እንኳ ከምንም አይቈጥሯትም። ማንኛውንም ነገር ለእርሱ ለወደደን መሥዋዕት አድርገዋል።

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ ይህንን ሁሉ ለማድረግ የሚያስችል ከፍተኛ ሥልጣን ሳይኖር አይቀርም ያልከው እውነት ነው። ይህንን ሁሉ

ለማድረግ ያደረሰን የጭፈና እምነት ወይም ማታለል ወይም ከነፈሰው ጋራ የመንፈስ ፍላጎት አይደለም። ይህንን ሁሉ ለማድረግ የሚገፋፋን ስለ እውነት ያለን ዕውቀትና ሕያው የሆነውን አምላክ ከልብ ስለምናፈቅር ነው።

‹‹ዕድሜህን ሙሉ ትፈልገው የነበረው እንደ ብርቅ የሆነ መዝገብ ነው፤ ይህንንም በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ከፍ ያለ ዋጋ ያለውን መዝገብ ጠቅላላው ዓለም እንኳ ሊሰጥ አይችልም። ሕይወታችን ይህን በመሰለው አሠቃቂ ስፍራ ውስጥ እንዲወሰን ቢገደድም እንኳ ደስታ ተለይቶን ዐያውቅም። የሞታችን ጊዜ ሲደርስ በድል አድራጊነት ወደ በጎው ዓለም እንሻገራለን።

‹‹ስለ ከፍተኛው አምላክ በሚገባ ለማወቅ እፈልጋለሁ ብለሃል። ይህ ከፍተኛ የምትለው አምላክ በእኛ እምነት÷ በክርስቶስ አማካይነት ራሱን ለሰዎች ገልጾአል።

‹‹እርሱ ለታላቅነቱና ለሥልጣኑ ብቻ ሳይሆን ለፍቅሩና ለምሕረቱ ወሰን የሌለው አምላክ ነው። ሃይማኖታችንም ወደ እርሱ እንድንጠጋ ስለሚያደርገን እርሱ ከልብ የሆነ ወዳጃችን÷ መሪያችን÷ መጽናኛችን÷ ተስፋችን÷ ፈጣሪያችን፤ ተበዝያችንና የአሁንም ሆነ የዘለዓለም አዳኛችን ነው።

‹‹ስለ ዘላለም ሕይወት የማወቅ ፍላጎትህን ገልጸህልኛል። ቅዱሳት መጻሕፍታችን ስለዚህ ጉዳይ በሰፊው ያስረዳሉ። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ምድራዊውን ኑሮአችንን አምላክን በማገልገል ያሳለፍን እንደ ሆነ የዘለዓለም ብዕዕና ባለበት በመንግሥተ ሰማያት ከእርሱ ጋር አብረን እንደምንኖር ያስረዱናል። በምድራዊው ሕይወታችን አምላካችንን የምናስደስትበትን መንገድ በማስረዳት ከዚህ ሕይወት በኋላ እንዴት አድርገን እንደምንወድሰው ያሳዩናል። ምእመናን የሆኑ ሁሉ ሞትን እንደ መቅሠፍት አይመለከቱትም። ሞት ከዚህ ዓለም ወደ ዘለአለም ሕይወት የሚያሸጋግር ድልድይ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍታችን ያስረዱናል።

‹‹በዚህ ዓለም ጭንቀት ውስጥ ከመኖር ይልቅ የወደደንና ራሱን ስለ እኛ የሰጠው ወደ አለበት መሻገር የተሻለ ነው።››

ማርሲሉስም እንባውን እያፈሰሰ እንዲህ አለ፦

‹‹የምትለው ሁሉ ልቤን ነክቶታል፡፡ እባክህ ጨምረህ አስረዳኝ፡፡ እስከ ዛሬም ስናፍቀው የነበረውንና ከፍተኛውን አምላክ እንዲገልጽልኝ እለምነው የነበረው ይኸንኑ ነበር፡፡ ልቤ ሲመኘው የነበረው ምሥጢር ሁሉ በእጅህ ውስጥ መኖሩ ይሰማኛል፡፡ ሞቱም ሽረቱም የሚለየው ዛሬ በመሆኑ ነገ ዛሬ ሳትል ማንኛውንም ነገር ግልጽ አድርገህ እንድትነግረኝ እለምንሃለሁ፡፡ በእውነት ይህንን ሁሉ ነገር እውነተኛው አምላክ ለሰዎች ሁሉ መግለጹን እስከ ዛሬ ሳላውቅ እኖር ነበር ማለት ነው?››

ይህን ሁሉ ቆመው ይሰሙ የነበሩ ክርስቲያኖች ዓይኖች የደስታ እንባ አዘሉ፡፡ ሖኖሪዮስም የምስጋናና የደስተታ ድምፅ አሰማ፡፡ አንድ የብራና ጥቅል በጥንቃቄ አውጥቶ እንዲህ አለ፤ ‹‹ወጣቱ መኰንን ሆይ÷ ለሰዎች ሰላምና ደስታ ሊሰጥ የሚችለው አምላካዊ ቃል እዚህ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ለነፍሳችን የሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ በዚህ ውስጥ ተጽፎአል፡፡ እነዚህ ቅዱስ የሆኑ አምላካዊ ቃላት የትም ስፍራ ሊገኝ የማይችለውን ምሥጢር ሁሉ ያስተምራሉ፡፡ ይህም ጽሑፍ ተመርምሮና ተጠልቶ የማያልቅ የእውነት ውቅያኖስ ነው፡፡

ሖኖሪዮስም መጽሐፉን ገልጦ የኢየሱስን ታሪክ ለማርሴሉስ ማስረዳት ጀመረ፡፡ በዔድን ገነት ውስጥ በተሰጠው ተስፋ መሠረት አንድ የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጥ መምጣቱን ለማወጅ በየጊዜው ተነሥተው ስለነበሩት አያሌ ነብያት የእግዚአብሔርን ምሥጢር ጠባቂ ለመሆን ስለ ተመረጡት እስራኤላውያን÷ በዘመኑ ሁሉ ስለ ተፈጸሙት አምላካዊ ተአምራት በዝርዝሩ አስረዳው፡፡ ስለ ኢየሱስ ከድንግል መወለድ÷ ስለ ሕፃንነቱ÷ ለመጀመሪያ ጊዜ በገሀድ ስለ መገለጡ÷ ስለ ተአምራቱና÷ ስለ ትምህርቱ ከማስረጃ ጋር አነበበለት፡፡

ከዚያ ቀጥሎ ክርስቶስ በሰዎች እጅ የደረሰበትን ውርደት÷ አልፎ መሰጠቱንና ወደ ፍርድ ሸንጎ መቅረቡን ነገረው፡፡ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የደረሰበትን መሪር ሞት ታሪክ አነበበለት፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ማርሴሉስ በተደቆሰ ልብ ታሪኩን ያዳምጥ ነበር፡፡ በሰማው ሁሉ ልቡ ተነካ፡፡ አእምሮውም እየበራለት ሄደ፡፡ ከሰው ኃጢአት ጋር ግንኙነት የሌለው የእግዚአብሔር ቅድስና አጥፊን ያለ ቅጣት የማያልፈው ትክክለኛነቱ÷ ብዙ ነገር ለማለፍ የሚችለው ትዕግሥቱ÷ ለሰዎች ሁሉ ከገነብት አበሳ የሚወጡበትን መውጫያ መንገድ ማዘጋጀቱ÷ አንድ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስከ መስጠት ያደረሰው ግሩም የሆነ ፍቅሩ÷

በፍቅሩም ምክንያት ራሱን ለሰዎች ደኅንነት መሥዋዕት አድርጎ መስጠቱ÷ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ክርስቲያናዊ ምሥጢራት ለማርሴሉስ እየተብራሩለት ሄዱ።

ሖኖሪዮስ በመጨረሻ ክርስቶስ የተሰማውን ‹‹አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውኸኝ›› የሚለውን ቃል ‹‹ተፈጸመ›› ከሚለው የድል ድምፅ ጋር ባነበበለት ጊዜ ማርሴሉስ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ሖኖሪዮስም እንባ ባቀረሩ ዓይኖቹ ቀና ብሎ ቢመለከት ጉበዙ መኰንን አቀርቅሮ እንባውን ሲያፈስ ዐየው። እየተንሰቀሰቀም ‹‹በቃኝ! በቃኝ! ጥቂት ጊዜ ስለ እርሱ ስለ ክርስቶስ የማስብበትን ጊዜ ስጠኝ›› አለ።

‹‹ለእርሱ ለወደደን

ከኃጢአታችንም

በደሙ ላነጻን።››

ማርሴሉስም ፊቱን በእጆቹ ላይ ድፍት አድርጎ÷ ሖኖሪዮስም ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አቅንቶ ጸለዩ። ሁለቱም ብቻቸውን ነበሩ። አብረዋቸው የነበሩት ሁሉ አንድ ላይ ወደ ስፍራቸው ተሰማርተው ነበር። የአንድ አነስተኛ ጧፍ የብርሃን ጭላንጭል ይታይ ነበር። ሁለቱም አንዳች ቃል ሳይተነፍሱ ብዙ ጊዜ አለፈ።

ማርሴሉስ ራሱን አቅንቶ÷ ‹‹ቅዱሱን ከገደሉት ሰዎች እንደ አንዱ መሆኔ ተሰምቶኛል። ከዚያ ከሕይወት ቃል ጨምረህ አንብብልኝ። ሞት ሽረቱ የሚታወቀው በእርሱ ነው›› አለ።

ሖኖሪዮስም ስለ ጌታ ስቅለት÷ ስለ ቀብሩ÷ በሦስተኛው ቀን ከሞት ስለ መነሣቱ÷ በአብ ቀኝ ለመቀመጥ ወደ ሰማይ ስለ ማረጉ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ላይ መውረድ መንፈስ ቅዱስም የምእመናንን ልብ መቀደሱ በማድረግ ከእነርሱ ጋር ዘወትር አብሮ ስለ መኖሩ÷ ለክርስቶስ ክብር ከኃጢአታቸው በንስሐ ለሚመለሱ ሁሉ ክርስቶስን በመግለጥ ስለሚፈጽመው ግሩም ስለ ሆነው ሥራው አነበበለት። ሖኖሪዮስም ንባቡን በዚህ ላይ አላቆመም፤ የማርሴሉስ ነፍስ ሰላምን የምትቀዳጅበትን መንገድ በማብራራት ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ‹‹ወደ እኔ ኑ›› ሲል ያቀረበላቸውን ጥሪ÷ እርሱን እንደ ግል መድኃኒታቸው ለሚቀበሉ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ የተሰጣቸው መሆኑን አስረዳው።

ስለ ዐዲሱ ልደት፥ ስለ ዐዲሱ ሕይወት፥ ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት፥ ስለ ሰጠው ተስፋ አነበበለት።

ማርሴሉስም ይህን ሁሉ ከሰማ በኋላ እንዲህ አለ፡- ‹‹ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ በእውነት ከሰማይ የወረደ ድምፅ ነው። የሰማሁት ሁሉ ልቤን ነክቶታል። በዚህም የዘለዓለም እውነት መሆኑን ተረድቻለሁ። ይህን የተነበበልኝን ደኅንነት የግል ገንዘቤ ለማድረግ እንዴት እችላለሁ? ዓይኖቼ ሁሉ ጠርተዋል። ራሴን ለማወቅ ችያለሁ፡ ከዚህ ቀደም ራሴን እንደ ጻድቅ እቆጥር ነበር። አሁን በተገለጸልኝ ብርሃን ራሴን እንደ ጻድቅ እቈጥር ነበር። አሁን በተገለጸልኝ ብርሃን ራሴን ስመረምረው በቅዱሱ ፊት ጕስቋላ ኃጢአተኛ መሆኔን ተገንዝቤአለሁ። በትቢያ ውስጥ ከመንከባለል በቀር በቅዱሱ ፊት መቆም የማይገባኝ ኃጢአተኛና ወንጀለኛ ነኝ። እንዴት መዳን እችላለሁ?››

‹‹ክርስቶስ ኢየሱስ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው።››

‹‹እንዴት አድርጌ ልቀበለው እችላለሁ?››

‹‹እኛ የምናውጀው የእውነት ቃል በአፍህ በልብህም ቀርቦልሃል። ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ። ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፥ በአፉም መስክሮ ይድናል።››

‹‹ማድረግ የሚገባኝ ምንም ነገር የለምን?››

‹‹ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘለዓለም ሕይወት ነው።››

‹‹ማቅረብ የሚገባኝ መሥዋዕት የለም?››

‹‹እርሱ ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘለዓለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። ስለዚህ ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ስለ እነርሱም ሊማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል።

ማርሴሉስም፤ ‹‹የሚገባኝ ከሆነ ቃሉን አስተምረኝ፥ ወደ እርሱም አሁኑኑ ምራኝ›› አለ።

በዚያ እነስተኛ የብርሃን ጭላንጭል በሚታይበት፥ በዚያ ፍጹም የሆነ ጸጥታ በነገሠበት ክፍል ውስጥ ሖኖሪዮስ ለጸሎት ተንበረከከ። ማርሴሉስም አጠገቡ ድፍት አለ።

ሖኖሪዮስ ጸሎቱን በሚያደርስበት ጊዜ ማርሴሉስ ነፍሱ መንግሥተ ሰማያት ደርሳ ከጌታ ጋር ግንኙነት የምታደርግ መሆኑ ተሰማው። ከሖኖሪዮስ አንደበት የሚመነጩትን ቃላት እንደ ራሱ ቃላት አድርጎ ቈጠራቸው። በሖኖሪዮስ አፍ ጭንቀቱን በሚገባ ለጌታ የሚያመለክት መሆኑ ተሰማው። በመጨረሻም የእርሱ ፍላጎት እየበረታ ሄደ።

እውነተኛ እምነት በልቡ ውስጥ ሥር መስደድ ጀመረ። አንደበቱም ተፈታ። የልቡንም ጭንቀት፥ ‹‹ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ፤ አለማመኔንም እርዳ›› በሚሉት ቃላት ገለጠ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛ ሰው የሆነ ክርስቶስ መሆኑን ተረዳ። ኢየሱስ በሚቀጥሉት መስመሮች የተናገራቸውን ቃላት የእምነቱ መልሕቅ አደረገ። ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ? ቃሌን የሚሰማ በላከኝም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፥ ወደ ፍርድ አይደርስም፥ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ። እኔም ለበጎቼ የዘለዓለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ። ለዘላለም አይጠፉም፥ ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም።››

እዚያው በተንበረከኩበት ላይ እንዳሉ አያሌ ሰዓቶች አለፉ። ከሞት ወደ ሕይወት በምትሻገር ነፍስ ውስጥ የሚፈጸመውን ተአምር ማን ለመግለጥ ይችላል? ፀሐይዋ በላይ ባለው ምድር ላይ ብርሃን ሰጪ ጮራዋን ስትፈነጥቅ የማርሴሉስም ነፍስ በሰማያዊ ብርሃን ውስጥ ገብታ ትደሰት ነበር። ሲናፍቀው የነበረውን ሁሉ አገኘ። የኃጢአት ሸክም ቀለለት። በኢየሱስም ምክንያት በሚሰጠው የእግዚአብሔር ሰላም ልቡ ተሞላ።

የክርስትናን ምሥጢር የግል ገንዘቡ ለማድረግ ቻለ። በፈቃዱም የክርስቶስ ባሪያ መሆንን መረጠ። በክርስቶስ ወንድሞቹና እኅቶቹ ከሆኑ ጋር በኅብረት የሚከተሉትን ቃላት ሊዘምር ቻለ።

‹‹ለእርሱ ለወደደን
ከኃጢአታችንም
በደሙ ላነጻን
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ
ክብርና ኃይል ይሁን።››

# የምስክሮች ብዛት

‹‹እነዚህ ሁሉ በእምነት የሞቱ ናቸው፡፡››

ማርሴሉስ በበለጠ ስለ ክርስቲያኖች ማወቅ ጀመረ፡፡ ጥቂት ጊዜ ዕረፍት ካደረገ በኋላ በሖኖሪዮስ መሪነት ክርስቲያኖች የሚኖሩባቸውን ስፍራዎች ሁናቴ እየተዘዋወረ ተመለከተ፡፡

ማርሴሉስ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያ በስብሰባው ክፍል ያያቸው ሰዎች በካታኮምቡ ውስጥ ከሚኖሩት ጋር ሲያመዛዝናቸው ቊጥራቸው አነስተኛ እንደ ሆነ ተረዳ፡፡

የጉብኝት ጊዜውን በቀጠለበት መጠን በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሆነው አገኛቸው፡፡ ክርስቲያኖቹም በየስፍራው በማኅበር ከተማይቱ ጋር የሚገናኙበት ልዩ መንገድ ነበረው፡፡

ማርሴሉስ ከሖኖሪዮስ ጋር ያደረገው ጉዞ ረጅም ነበር፡፡ በየስፍራው ባያቸው ክርስቲያኖች ብዛት ተደነቀ፡፡ ምንም እንኳ የክርስቲያኖችን ብዛት ከዚህ ቀደም የተረዳው ቢሆንም÷ ይህን ያህል ታላቅ ሠራዊት በካታኮምቡ ውስጥ የመኖርን ዕድል ይመርጣል ብሎ ዐላሰበም ነበር፡፡ በሕይወት ባሉት ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በሞቱትም ዜና ዐሳቡ ተማረከ፡፡ ባለፈባቸው ስፍራዎች ሁሉ በሚገኙት መቃብሮች ላይ የተቀረፁትን ቃላት አነበበ፡፡ በዚያ ውስጥ ያረፉት ሁሉ ጠንካራ እምነትና ከፍ ያለ ዓላማ ያለው ተስፋ እንደ ነበራቸው ተረዳ፡፡ ማርሴሉስ በመቃብሮች ላይ የተቀረፁትን ቃላት ማንበብ ያስደስቱት ጀመር፡፡ ሖኖሪዮስም የእያንዳንዳንዱን ሰማዕት ታሪክ በማብራራት ይገልጽለት ነበር፡፡ ሖኖሪዮስ ቆም ብሎ አንድ የእውነት ምስክር እዚያ አርፎአል ሲል አመለከተ፡፡

ማርሴሉስም ሖኖሪዮስ ወደ አመለከተበት አቅጣጫ ዞሮ የሚከተሉትን ቃላት አነበበ፡፡

- ፕሪሚቲዮስ በሰላም፡፡ ብዙ ሥቃይ ተቀብሎ የሞተ ጽኑ ሰማዕት፡፡ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር፡፡ ሚስቱም ይህን ተገቢው የሆነውን መታሰቢያ አቆመችለት፡፡

ሖኖሪዮስ÷ «እነዚህ ሰዎች ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በእንዴት ያለ አኳኋን መሞት እንደሚገባው ያስተምሩናል፡፡ ያውልህ እልፍ ብሎ

የሚገኘው መቃብር የፕሪሚቲዮስን ዓይነት ሥቃይ ደርሶበት የሞተ ሰማዕት ነው።»

- ጳውሎስ ለዘለዓለም በብዕና ለመኖር ከዚህ ዓለም በሥቃይ ተለየ።

ሖኖሪዮስ÷ ‹‹እዚህ ደግሞ የአንዲት ሴት ወይዘሮ መቃብር ይታያል። የእርስዋ አሟሟት ክርስቶስ ደነሞች ለሆኑ ተከታዮቹ እንኳ በጭንቀት ጊዜ ለሚሰጠው ብርታት ምስክር ነው።

- ክሌሜንቲያ በሥቃይ ሞተች÷ ትነሣለች።

‹‹አንድ ምእመን ሞትን እንዲቀምስ ሲደረግ ነፍሱ ወዲያው ከሥጋው ተለይታ ከጌታ ጋር ትሆናለች። ምእመናን ሁሉ የሚጠባበቁት ታላቅ ተስፋ በማንኛውም ጊዜ ሊፈጸም የሚችለውን የጌታን ዳግመኛ መምጣት ነው። ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታችንን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን። እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።

‹‹ይህ የምታየው ደግሞ ኮንስታንስ የተባለው ወንድማችን ማረፊያ ስፍራ ነው። ሁለት ጊዜ የሞት ፍርድ ቢፈረድበትም ሁለት ጊዜ በእምነቱ ጸንቶ ተገኘ። መጀመሪያ ጊዜ በመርዝ እንዲሞት ተደረገ። መርዙ አልጎዳህ ቢለው በሰይፍ ተገደለ።››

- ለኮንስታንስ ሰይፍ እንዲያቀዳጀው የታቀደውን አክሊል መርዝ ሊሰጠው አቃተው።

በእንደዚህ ያለ አኳኋን በግራም በቀኝም የሚታዩትን የመታሰቢያ ጽሑፎች እያነበቡ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ማርሴሉስ በብዛት የሚቈጠሩትን የቅዱሳን ስሞች በማንበብ ልዩ የሆነ ስሜት አደረበት።

ባጠቃላይ÷ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በቅርብ እንደ መረመረ ያህል ተሰማው። ሰማዕታት የፈጸሙት ገድል እንደ እሳት በሚያውለበልቡ ቃላት በፊቱ ተመዝግበው ታዩት። በብዙዎቹ መቃብሮች ላይ የተሣሉት ሥዕሎች በተመልካች ዘንድ ከፍ ያለ የሐዘን ስሜት የሚቀሰቅሱ ነበሩ። የዶሮ ጭረት በሚመስሉ ፊደሎች ተጽፈው በብዙዎቹ መታሰቢያዎች ላይ የሚነበበው ዐሳብ አለመሳካት÷ ወንጌል ለድሆችና በዚህ ዓለም ላይ ዝቀተኞች ለሆኑ ሁሉ ብርቅ መዝገብ እንደ ነበረች በግልጽ ያስረዳ ነበር። ‹‹ከእናንተ ውስጥ ብዙዎች ጥበበኞች የሆኑ÷ ብዙዎች ኃይለኞች የሆኑ አልተጠሩም። ዳሩ ግን ለድሆች

ወንጌል ይሰበካል፡፡›› በአብዛኛዎቹ መቃብሮች ላይ አንድ ላይ የተጣመሩ ሁለት የዕርዕ ፊደሎች ይታዩባቸው ነበር። የእነዚህም ሁለት ፊደሎች ትርጉም 'ክርስቶስ ጌታ' የሚል ነበር፡፡

አንዳንዶቹ ምልክቶች በዘንባባ ቅጠል አጊጠው ይታያሉ። የዘንባባ ቅጠል በቅዱስ ዙፋን ዙሪያ የመቆም ዕድል የሚሰጣቸው ቅዱሳን በእጃቸው የሚይዙት የድልና የዘላለማዊነት ምልክት ነው። በሌሎች መቃብሮች ላይ ደግሞ ልዩ ልዩ የሆኑ ምልክቶች ይታዩባቸዋል፡፡

ማርሴሉስ ወደ አንድ መርከብ ሥዕል እያመለከተ÷ ‹‹ይህ ደግሞ ምንድ ነው?›› ሲል ጠየቀ፡፡

‹‹የመርከቡ ሥዕል የሚያመለክተው የቅዱሳን ነፍስ ከዚህ ምድር ወደ ሰማያዊው ዕረፍት መጓዟን ነው፡፡››

‹‹የዓሣ ሥዕል ሁልጊዜ ያጋጥመኛል÷ ትርጉሙ ምን ይሆን?››

‹‹ይህ የምታየው የዓሣ ሥዕል ጥልቅ የሆነ ምሥጢር አለው፡፡ ‹‹ዓሣ›› የተባለው ስም የሚጻፍባቸው አምስቱ የዕርዕ ፊደሎች (ΙΧΘΥΣ) የምዕመናንን ክብርና ተስፋ የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ አምስት የዕርዕ ፊደሎች ወደ አማርኛ ሲመለሱ፤ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኅን፤ የእግዚአብሔር ልጅ›› የሚል ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

‹‹አንድ መርከብና የአንድ የባሕር ውስጥ አውሬ አብረው ተሥለው ይታዩኛል፡፡ የዚህ ትርጉምስ ምንድን ነው?››

‹‹ይህ ሥዕል በጥንት ዘመን የኖረ ዮናስ የተባለ የእግዚአብሔር ነቢይ ምሳሌ ነው፡፡ እንደሚመስለኝ ስለ እርሱ ታሪክ ገና አልሰማህም፡፡››

ሖኖሪዮስ ለማርሴሉስ የነብዩን የዮናስን ታሪክ ገለጸለት። የዮናስ ከዓሣ ሆድ ውስጥ ለመውጣት መቻል፤ የክርስቶስ ከመቃብር ማኅፀን ውስጥ በድል አድራጊነት የመውጣቱ ትንቢት እንደ ነበር አስረዳው፡፡

‹‹የተስፋዎች ሁሉ መሠረት የሆነው የትንሣኤ ተስፋ ታላቅ መጽናናትን ይሰጣል፡፡ ይህንም ተስፋ እንዳንዘነጋ የሚያስታውሱን አያሌ ምልክቶች አሉን፡፡ ያች የወይራ ቀንበጥ ይዛ ወደ ኖኅ መርከብ የተመለሰችው ርግብ ሥዕልም ትንሣኤን የሚያሳስበን ነው፡፡››

ይህንንም ብሎ የሥዕሉን ምሥጢር እንዲረዳው የጥፋትን ውኃ ታሪክ ተረከለት፡፡

‹‹ከምልክቶች ሁሉ ይልቅ የትንሣኤ ተስፋችንን ብርቱ የሚያደርገው የዓልአዛር ትንሣኤ ሥዕል ነው፡፡

‹‹እዚህ የምታየው የመልሕት ሥዕል ደግሞ የተስፋ ምልክት

ነው። ምእመን የሆነ ሁሉ በዚህ ዓለም ማዕበል ሌት ተቀን ቢንገላታም ወደ ሰማያዊ ቤቱ ለመድረስ ከመታገል መቦዘን የለበትም።

‹‹ወዲያ ደግሞ የአንድ አውራ ዶሮ ሥዕል ይታያል፤ እርሱ የትጋት ምልክት ነው። ጌታችን ትጉና ጸልዩ ያለውን ያሳስበናል። የአንድ ጠቦት ሥዕል ያውልህ። እርሱ ደግሞ የንጽሕናና የርኅራኄ ምልክት ነው። ከዚህም በቀር ኃጢአታችንን የተሸከመውን፥ በመሥዋዕትነቱ የዘለዓለም ሕይወት ያገኘንበትን የእግዚአብሔርን በግ ያሳስበናል። እንደ ገና አንድ የርግብ ሥዕል ያውልህ። ርግብ ጠቦትን ትመስላለች። እርስዋም የንጽሕና ምልክት ናት፤ በአፏዋ የያዘችው የወይራ ቀንበጥ ደግሞ ሰላምን ያበሥራል።

‹‹እዚያ ደግሞ ሁለት ፊደሎች ይታያሉ። እነርሱም አልፋ ኦሜጋ የሚባሉት ሁለቱ፡ የመጀመሪያና የመጨረሻ የዕርዕ ፊደሎች ናቸው። ጌታችን አንድ ጊዜ እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ ያለውን ያስታውሰናል።

‹‹እዚህ አንድ ዘውድ ይታያል። እርሱም ጻድቅ ጌታ የሚሰጠን የማይጠፋው ዘውድ ምሳሌ ነው። እነዚህ በየስፍራው የምታያቸው ምልክቶች ሁሉ በሰማይ የሚጠብቀንን ብዕዕና የሚያሳስቡን ከመሆናቸውም በላይ የዚህን ዓለም ጭንቀት በመርሳት በእምነት የዘለዓለማዊውን ክብር ብርሃን እንድናይ ያደርጉናል።

ማርሴሉስ፥ ‹‹ይህስ ምናልባት ከእኔ የወደፊት ድል ጋር የሚስማማ ሳይሆን አይቀርም። ቃሉ ትንቢት ይመስላል። እርሱ ጽናቱን ይስጠኝ እንጂ እኔም ወደ ፊት የክርስቶስ ምስክር የምንሆንበት ጊዜ ይደርስ ይሆናል።››

- ማርስ ወጣት የጦር መኰንን በአድሪያን ዘመነ መንግሥት ደሙን ለክርስቶስ ሲል አፍስሶ በሰላም ሞተ። ወዳጆቹ በሐዘንና በፍርሃት ይህንን መታሰቢያ አቆሙለት።

ሖኖሪዮስ፤ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ። ይህንን መጽናናት የሚሰጠን ክርስቶስ ራሱ ነው። በአንድ በኩል ከክፉ እንድንጠነቀቅ ሲመክረን፥ በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ ራሱ ረድኤታችን እንደሚሆን ያረጋግጥልናል። በእርሱም ለድካማችን ሁሉ በቂ የሆነ ጸጋ እናገኛለን።››

ማርሴሉስም፥ ‹‹የዚህ ወጣ መኰንን አርአያ መከተል የልቤ ምኞት ነው። እንደ እርሱ ደሜ ስለ ክርስቶስ የሚፈስበትን ዕለት በተስፋ እጠባበቃለሁ። እንደ እርሱ የታመነ ለመሆን ያብቃኝ። ታላላቅ ከተባሉት ኃያላ መካከል በክብር ከመቀበር ይልቅ በወንድሞቼ መካከል

በእንደዚህ ያለ አኳኋን ማረፍን እመርጣሁ።

ሁለቱም አንድ ላይ ፕዞአቸውን ቀጠሉ።

ማርሴሉስ ‹‹በእውነቱ የክርስቲያን ሞት ሞት አይባልም። ክርስቲያን ለሆነ ሞት ጭንቀት የሌለበት የተቀደሰ እንቅልፍ ነው። በሞት ጊዜ የምእመናን ነፍስ ከጌታ ጋር ለመሆን የመጨረሻውን ትንሣኤ ትጠባበቃለች። ከዚህ የተነሣ የምእመን ሞት ድልንና ዘላለማዊውን ዕረፍት ያሳስባል።

- የአልፒስ ማረፊያ ስፍራ።
- ሁቲኩስ እዚህ ዐርፎአል።
- አሌሉስ በክርስቶስ አንቀላፋ።
- ማራቲሪያ በሰላም።
- ቪዳሊያ በክርስቶስ ሰላም።
- መልካሙ ኒሴፎሩስ በዕረፍት ስፍራ።

አላይ የተጠቀሱትን የመታሰቢያ ቃሎች እያነበቡ ከተጓዙ በኋላ ሖኖሪዮስ ማርሴሉስን እንዲህ አለው፡- ‹‹በአንዳንዶቹ መቃብሮች ላይ የተቀረፁት የመታሰቢያ ቃሎች የሚቹን ጠባይ የሚገልጹ ናቸው። እስቲ ይህን ተመልከት።››

- ማክሲሙስ 23 ዓመት ኖረ፤ የሁሉ ወዳጅ።
- ጥቅምት 5 ቀን ቦርጎኒዮስ በክርስቶስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ሁሉ ወዳጁ።

‹‹እነዚህ ደግሞ የሚቹቹን ምድራዊ ኑሮ ሁኔታ የሚገልጡ የመታሰቢያ ቃሎች ናቸው።››

- ካሲሊዮስ ለባለቤቱ ለካሲሊያ ፕላሲንዳ ለመልካም መታሰቢያዋ። ያለ አንዳች ጠብ ዐሥር ዓመት አብረን ኖርን። በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ።

- የአማልክት ሁሉ ጌታ በሆነው በክርስቶስ ስም ቪታሊስ በነሐሴ ወር ቀዳሚ ዕለት በሃያ አምስት ዓመት ከስምንት ወር ዕድሜዋ ሀርፋ በዚህ ስፍራ ተቀበረች። ከባልዋ ጋር ዐሥር ዓመት ከሠላሳ ቀናት አብራ ኖረች። በክርስቶስ መጀመሪያውና መጨረሻው።

ማርሴሉስ፥ ‹‹ይህ ደግሞ አንድ አባት ለልጁ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ነው።››

ሎሬንስ፥ ለውድ ልጁ ለሰቨሩስ።

- ጥር ሰባት ቀን በመላእክት ታጅቦ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ሖኖሪዮስ፤ ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት አንድ ምእመን ከመንፈስ ቅዱስ ዐዲስ ጠባይ ይቀበላል፡፡ ይህም ዐዲስ ጠባይ የእግዚአብሔርና የፍቅሩ ተካፋይ ያደርገዋል፡፡ አሁን እንዳየኸው ምእመን የሆነ ሁሉ ለወዳጆቹ ከፍ ያለ የፍቅር ስሜት የሚያሳየው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ አንድ ምእመን ከአሮጌው አዳም ዝንባሌ ነፃ ሊሆን ባይችልም እንኳ ራሱን ለማሻሻል ውስጣዊ ኃይል አያጥረውም፡፡››

በጉብኝታቸው ዘመድ ለዘመዱ ወዳጅ ለወዳጁ የሚያሳያቸውን የጋለ የፍቅር መታሰቢያዎች በእያንዳንዱ መቃብር ላይ ተመዝግበው አነበቡ፡፡

ብዙ ምእመናን አንድ ላይ ወደ ተቀበሩበት ስፍራ እንደ ደረሱ ሖኖሪዮስ ማርሴሉስን እንዲህ አለው፡- ‹‹አንዳንድ ጊዜ ሁለት ሦስት ሰዎች በአንድ መቃብር ውስጥ ይቀበራሉ፡፡ ስደት በበዛበት ዘመን ደግሞ በብዙ የሚቈጠሩ ምእመናን በአንድ ጕድጓድ ውስጥ እንዲያርፉ ይደረጋል፡፡ በዚያን ጊዜ ለእያንዳንዱ ምእመን የሚገባውን የቀብር ሥርዓት መፈጸም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ እልፍ ብሎ የምታየው ስማቸው ያልታወቀ የብዙ ሰማዕታት መቃብር ነው፡፡ ስማቸው ባይታወቅም መታሰቢያቸው ብፁዕ ሆኖ ይኖራል፡፡››

የሚከተሉት የመታሰቢያ ቃላት በመቃብሩ ላይ ይነበቡ ነበር፡፡

- ማርሴላ ከአምስት መቶ ሰማዕታት ጋር ያረፈበት መቃብር፡፡

ሖኖሪዮስ፤ ‹‹እንዳየኸው ይህ ሁሉ ውድ የሆኑት የክርስቲያን ወንድሞቻችን ማረፊያ ነው፡፡ ስማቸው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሲነሣ ይኖራል፡፡

‹‹በልደት በዓልም ዕለት በመቃብሮቹ ዙሪያ ተሰብስበን የፍቅር በዓል እናደርጋለን፡፡ በዚህ በዓል ላይ እገሌ ትልቅ ነው እገሌ ወራዳ ነው ማለት የለም፡፡ የወገንና የቋንቋ ልዩነት ሁሉ ለኅብረታችን መሰናክል ሊሆን አይችልም፤ በክርስቶስ ሁላችን ወንድማማቾች ነን፡፡

‹‹ክርስቶስ እኛን እንደ ወደደን እኛም እርስ በርሳችን መዋደድ አለብን፡፡››

ማርሴሉስ በካታኮምቡ ውስጥ ባደረገው ጕብኝት ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ያላቸው ፍቅር በቃል ብቻ ሳይሆን በግብር ሲገለጥ በቅርብ ለመመልከት ቻለ፡፡ በደረሰበት ስፍራ ሁሉ የሚያገኛቸው ሰዎች ድሃ÷ ባለ ጠጋ ወጣት÷ ሽማግሌ ሳይባባሉ በኅብረትና በፍቅር አብረው ሲኖሩ ዐየ፡፡

ከዚህ ቀደም የክርስቲያኖች ጠር የነበሩት አሳዳጆች ክርስቲያን ሆነው ከክርስቲያኖች ጋር ተቀብረው ይታያሉ፡፡ የኦሬት ሕግ ቀንበር

የወረደለት አይሁዳዊ ካህን ከዚህ ቀደም ይጸየፋቸው ከነበሩት አረማውያን ጋር ጐን ለጐን ይሄድ ነበር፡፡ ወንጌልን እንደ ስንፍና ይገምተው የነበረው ዕርዓዊ፥ ጥልቅ ምሥጢሩን በመገንዘቡ በንቀት ዓይን ይመለከቷቸው የነበሩትን ክርስቲያኖች የእምነት ወንድሞቹ አድርጓቸው ይታያል፡፡ ራሱን መውደድና ለገዛ ጥቅም መሽቀዳደም ኵራትና ምቀኝነትን እንዲሁም ወራዳ የሆኑት ሰብአዊ ዝንባሌዎች ሁሉ ለክርስቲያናዊው ፍቅር ስፍራቸውን ለቀው ይታዩ ነበር፡፡ የክርስቶስ እምነት የምእመንን ልብ በሙላቱ ከመውረሱም በላይ በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች የመንፈስ ግለት በሌላ ስፍራ አምሳያ የማይገኝለት ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ዓይነተኛ ምክንያት ማንንም ሳይለይ ያጠቃ የነበረው ስደት ከምድራዊ ብልጥግና፥ ከዓለም ፈተናና ከጥቅም ፍላጎት ገላግሎ በክርስቶስ ፍቅር እንዲተሳሰሩና የደረሰባቸውን መከራ በኅብረት እንዲቀበሉ ስላደረጋቸው ነው፡፡



ማርሲሉስና ሖኖሪዮስ ካታኮምቡ ውስጥ

‹‹ይህ ምታየው ደግሞ ኮንስታንስ የተባለው ወንድማችን ማረፊያ ነው፡፡››

ሖኖሪዮስም ለወጣቱ መኰንን የእውነተኛውን አምልኮ ምሥጢር እንዲህ ሲል አስረዳው፡-

‹‹የእውነተኛው አምላክ አምልኮ ስሑት ከሆኑት አምልኮዎች ሁሉ የተለየ ነው። አንድ አሕዛብ ለጣዖታት ወደ ተሠሩት መቅደሶች በመሄድ ቅድስና በሌለው ካህን አማካይነት ኃጢአት ሊያስተሰርዩ የማይችሉትን መሥዋዕቶች ዕለት ዕለት ለባዕዳን አማልክት ያቀርባል። ለእኛ ግን ነውር ያልተገኘበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለዘለዓለም በቂ የሆነ መሥዋዕት አድርጎ አንድ ጊዜ ለሁሉ አቅርቦአል።››

‹‹በክርስቶስ የሚታመኑ ምእመናን ሁሉ ቅዱስና ታላቅ በሆነው የካህናት አለቃ በኩል ወደ እግዚአብሔር የጸጋ ዙፋን ፊት ለመቅረብ ይችላሉ። ምክንያቱም በክርስቶስ እያንዳንዱ ምእመን የመንግሥትና የክህነት ወገን ሆኖአል። ስለዚህ አሳዳጆቻችን ከአብያተ ክርስቲያናችን እንድንሰደድ ቢያደርጉንም እንኳ አምልኮአችን በልዩ ስፍራና ጊዜ ሊወሰን አይችልም። ሰማያት የእግዚአብሔር ዙፋን ናቸው፥ መላው ዓለምም መቅደሱ ነው። ልጆቹ የሆኑ ባሉበት ስፍራና በተመቻቸው ጊዜ ስሙን ሊጠሩ ይችላሉ፥ እርሱም ይሰማቸዋል።››

ማርሴሉስ በካታኮምቡ ውስጥ ለውስጥ ያደረገው ጕዞ ረጅም በመሆኑ የወሰደው ጊዜ ያንኑ ያህል ነበር። ምንም እንኳ የክርስቲያኖችን ምሥጢር ለመረዳት የነበረው ጕጕት ከፍ ያለ ቢሆንም ባየው ነገር ሁሉ ከመጠን ያለፈ አድናቆት አደረበት። ይሁን እንጂ፥ በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች ዜና ገሚሱ እንኳ አልተነገረውም ነበር። ያደረገው ጕዞም ከጠቅላላው የካታኮምቡ ርዝመት ጋር ሲያመዛዝኑት በአነስተኛነት የሚገመት ነበር። የዋሻዎቹ ከፍታ በአንዳንድ ስፍራዎች እስከ ስምንት ጫማ በሌሎች ስፍራዎች ደግሞ እስከ ዐሥርና እስከ ዐሥራ አምስት ጫማ ይደርሳል። የዋሻው ከፍታ ምቹ በሆነበት ቦታ የስብሰባ ክፍሎች፥ እንደ ልብ መላወሻና መኖሪያ ስፍራዎች ተሠርተዋል። በአንዳንድ የመሰብሰቢያ ክፍሎች ጣራ የብርሃን ጭላንጭል የሚያስገባ ቀዳዳ ይታይባቸዋል። እነዚህንም ስፍራዎች ክርስቲያኖች ለመናፈስ ያዘወትሩዋቸዋል። በቀዳዳው የሚገባው የብርሃን ጮራ የኑሮአቸውን አሠቃቂነት በመጠኑ በመቀነስ ጤናማውን አየር እንዲቀምሱ ያደርጋቸው ነበር።

ማርሴሉስ ባንዳንድ ስፍራዎች በሥርዓት ተለስና የቆመ ዓምድ በማየቱ ምሥጢሩን ለመረዳት ሖኖሪዮስን ጠየቀ። ሖኖሪዮስም እንዲህ ሲል አስረዳው። ‹‹ይህ ለብቻው ተለይቶ የሚታየው ነገር የአንድ

ሮማዊ መቃብር ነው። ቀሻዎቹ ሲቆፈሩ÷ ቆፋሪዎችን አንዳንድ ጊዜ የሮማውያን ስም ያለበት መቃብር ያጋጥማቸዋል። በዚህ ጊዜ መቃብሩን እንዳለ ትተው ዙሪያውን ከቆፈሩት የሮማውያንን መቃብሮች ለማፍረስ በመፍራት ሳይሆን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በሕይወቱም ሆነ በሞቱ ጊዜ ከእነርሱ መካከል ውጡ÷ የተለያችሁም ሁኑ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ማክበር እንዳለት በመገንዘብ ነው።››

ማርሴሉስ÷ ‹‹ስደትና መከራ ክርስቲያኖችን መውጫ መግቢያ አሳጥቶአቸዋል። የእግዚአብሔር ወገኖች እንደዚህ ተበትነው የሚኖሩት÷ ጠላቶቻቸውም እንዲ ያሠቃዩዋቸው የሚፈቀድላቸው እስከ መቼ ድረስ ነው?››

ሖኖሪዮስ÷ ‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ ይህ የአሁኑ ጥያቄህ የሁላችንንም ልብ የሚያስጨንቅ ጥያቄ ነው። ዳሩ ግን እምነታችን ይህ ደረሰብን ብሎ ማንጎራጎርን አይፈቀድልንም። ከዚህ በቀር የጌታ ረድኤት እስካሁን ተሳይቶን ዐያውቅም።

‹‹ከዚህ ቀደም ክርስቲያኖች መከራ ሳይደርስባቸው በሰላም ያሳለፉት ጊዜ መኖሩን እናስታውሳለን። አልፎ አልፎ የአሁኑን የመሰለ ስደት ይነሣና አያሌ ምእመናን በግፍ ያልቃሉ። የሆነ ሆኖ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ታጥቀው የተነሡት ኃያላን ሁሉ ዐሳባቸውን ከግቡ ሳያደርሱ አልፈዋል።

‹‹እስካሁን የደረሰብን ስደትና መከራ የምእመናንን ልብ ከማንጻቱም በላይ እምነታቸውን ጽኑ አድርጎታል። ጌታችን በመሆኑ ከምንችለው በላይ አንዳች ነገር እንዲ ደርስብን አይፈቅድም።

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ ስለዚህ መትጋትና መጸለይ አለብን። ይህ ሁሉ መከራና ስደት ታላቁ የጌታ ቀን መቃረቡን የሚያሳስበን ነው።››

ማርሴሉስና ሖኖሪዮስ በእንደዚህ ያለ አኳኋን እየተወያዩ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ማርሴሉስም ስለ አንዱ አምላክ ምሥጢር÷ በምእመናን ሕይወት ስለ ደረሱት ነገሮች ሁሉ የሚበቃውን ያህል ሊረዳ ቻለ። የፍቅራቸው÷ የንጽሕናቸው÷ የጽናታቸውና የእምነታቸው እውነተኛነት በልቡ ውስጥ ሥር ሰደደ።

በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የተረዳው ነገር የክርስቲያኖችን ዕጣ ለመምረጥ ያለውን ፍላጎት እያጠነከረው ሄደ። በገዛ ፈቃዱም በአብ

በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም ተጠመቀ።

በማግሥቱ የጌታ ዕለት እሑድ ስለ ነበር በጌታ ማዕድ ዙሪያ ከምእመናን ጋር ተቀመጠ። ያንን ቅዱስና የጌታ የሞቱ መታሰቢያ የሆነውን ሥርዓት በአንድ ልብ ሲፈጽሙ፥ ዳግመኛ መምጣቱን ተስፋ ያደርጉ ነበር። ሖኖሪዮስ ለጌታ መታሰቢያ የሚሆነውን ጸሎት አደረሰ።

ማርሴሉስም ለመጀመሪያ ጊዜ ኅብስቱንና ወይኑን በመቀበል ጌታ ሥጋውን የቆረሰውና ደሙን ያፈሰሰው ለደኅንነቱ መሆኑን ተገነዘበ።

መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ወደየስፍራቸው ተበታተኑ።

# የእምነት ጽናት

‹‹በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር›› እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡››

ወጣቱ መኰንን ከሰፈሩ ከተለየ አራት ቀናት አለፉ፡፡ በነዚህም ቀናት ውስጥ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ሊቀስም ቻለ፡፡ የኀበኛቸው ክርስቲያኖች÷ ሞት ሽረታቸውን ሳያውቁ በጭንቀት ውስጥ ይዋልሉ ነበር፡፡ ዳሩ ግን የወጣቱ መኰንን ድካም መልካም ፍሬን አፈራለት፡፡ ዕድሜውን ሙሉ ይመኘው የነበረውን የእውነት ምሥጢር ሊረዳ ቻለ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወለደ፡፡

ይህ በሕይወቱ የተፈጸመው መለወጥ አንድ ቊርጠኛ ውሳኔ ለማድረግ አስቻለው፡፡

በአንድ በኩል ዝና÷ ክብርና ብልጽግና በራቸውን ከፍተው መመለሱን ይጠባበቁ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ድህነት÷ ችግርና ስደት አለንልህ ይሉት ነበር፡፡ ወጣቱ መኰንን በቀረበለት ምርጫ አላመነታም፡፡ ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ‹‹ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን›› መረጠ፡፡

ወደ ጦር ሠፈሩ ተመልሶ ከተላከበት ስፍራ መመለሱን ለአለቃው አስታወቀ፡፡ ከክርስቲያኖች ጋር መሰንበቱንና የተላከበትን ግዳጅ ለመፈጸም የማይችል መሆኑን በመግለጽ በዚህ ምክንያት የሚሰጠውን ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ለአለቃው አስረዳ፡፡ አለቃው ጄኔራልም በቀጥታ ወደ ክፍሉ እንዲሄድ በጥብቅ ትእዛዝ ሰጠው፡፡

ወደ ክፍሉ ገብቶ የሚደርስበትን ነገር ሁሉ በማሰላሰል ላይ ሳለ ወዳጁ ሉኩሉስ በድንገት ከተፍ አለ፡፡ ሉኩሉስ ለጓደኛው ለማርሴሉስ የፍቅር ሰላምታ ሲያቀርብለት በገጹ ላይ የሥጋት ምልክት ይታይበት ነበር፡፡

‹‹ጄኔራሉ አስጠርቶኝ ለአንተ አንድ መልእክት እንድነግርህ አዘኛል፡፡ አስቀድሜ ሳውቀው የምፈልገው ይህ ያደረግኸው ነገር ምን እንደ ሆነ ነው፡፡››

ማርሴሉስም አንዳች ነገር ሳይሠውር ከሄደበት ቀን ጀምሮ የደረሰበትን ነገር ሁሉ ለሉኩሉስ ገለጸለት፡፡ ሁኔታው ሁሉ የመንፈስ

ቅዱስ ሥራ ለልቡ ጽናትን የሰጠው መሆኑ በጉልህ ይታይ ነበር። በሚከተለውም አኳኋን ከአለቃው ጄኔራል ጋር ያደረገውን የቀይታ ንግግር ነገረው፡-

‹‹ወደ ጄኔራሉ ስገባ የወሰድኩት የውሳኔ እርምጃ የሚያስከትለውን መዘዝ በመገንዘብ ነው። ያደረግሁት ሁሉ እንደ ከዳተኛ የሚያስቈጥረኝ መሆኑን ዐውቃለሁ። ለዚህ ዓይነት ወንጀል ከሞት በስተቀር ሌላ ቅጣት የማይወሰን መሆኑን አልዘነጋሁትም። የሆነ ሆኖ የዚያን ጊዜ አንዳች ሌላ ነገር ለማድረግ ኃይል አልነበረኝም።

‹‹ጄኔራሉ ያደረገልኝ አቀባበል ልባዊ ነበር። ይህንንም ያደረገው ከተሳካበት ስፍራ ቀንቶኝ የተመለስኩ መስሎት ነው። እኔም ከክርስቲያኖች ጋር መሰንበቴንና ከእነርሱም ጋር ያሳለፍኩት ጊዜ ከዚህ ቀደም ስለ ክርስቲያኖች የነበረኝን አስተያየት ፈጽሞ የለወጠው መሆኑን ገለጥኩለት። ከዚህ ቀደም ክርስቲያኖች ሞት የሚገባቸው የአገራችን ጠላቶች ይመስሉኝ እንደ ነበርና ከዚህ ጉብኝቱ በኋላ ግን በሥርዓት የሚኖሩ የአገራቸውና የመንግሥታቸው ቅን አገልጋዮች መሆናቸውን መረዳቴን አልሸሸግሁትም። ይህን በመሰሉ ንጹሐን ሰዎች ላይ ሰይፌን ከማንሣት ይልቅ ከሥልጣኔ መውረድና የሚደርስብኝን ቅጣት መቀበል የተሻለ መሆኑን አስረድቼዋለሁ።››

ሉኩሉስም÷ ‹‹የአንድ ወታደር የግል ስሜት ግዴታውን ከመፈጸም ሊያግደው አይችልም›› አለው።

ማርሴሉስም፤ ‹‹ለፈጣሪዬ መፈጸም የሚገባኝ ግዴታ ለሰዎች መፈጸም ካለብኝ ግዴታ የበለጠ ሆኖ አግኝቼዋለሁ›› ሲል መለሰለት።

‹‹የክርስቲያኖች ፍቅር ዓይንህን ሳያሳውረው የቀረ አይመስለኝም። ይህ የፈጸምከው ተግባር ከፍ ያለ የከዳተኝነት ወንጀል መሆኑ ዐይታይህም?››

‹‹አዎን÷ ይህንኑ በመረዳት የሠራሁት ወንጀል የሚያስከትለውን ቅጣት ለመቀበል የተዘጋጀሁ መሆኔን አልሠወርኩመም። ጄኔራሉም በቊጣ ቃል በቀጥታ ወደ መኖሪያህ ሂድ÷ እኔም የምሰጠውን ውሳኔ አስታውቅሃለሁ!›› ብሎ አዝዞኛል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚደርስብኝን ሁሉ ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ አለሁ።››

ሉኩሉስ የማርሴሉስን ቃል በጸጥታ አደመጠ። ሁኔታው ሁሉ

ስለ ወዳጁ የወደ ፊት ዕድል ጥልቅ የሆነ ሥጋት ያደረበት መሆኑን ይገልጥ ነበር።

ሉኩሉስም ሐዘን በተሞላበት አኳኋን እንዲህ አለ፡- ‹‹መቼም ይህ አድራጎትህ የሚያስከትለውን ቅጣት ደኅና አድርገህ ታውቃለህ። የሮም ሥነ ሥርዓት በቀላሉ የሚታለፍ ነገር አይደለም። መንግሥት ክርስቲያኖችን በተመለከተ ጥብቅ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ መወሰኑ ጉዳዩን ከልክ ያለፈ አክርሮታል። በአሁኑ አኳኋንህ የቀጠልህ እንደ ሆነ ውድቀትህ የተቃረበ መሆኑ አይጠረጠርም።››

‹‹ወደዚህ ውሳኔ ያደረሱኝን ምክንያቶች ሁሉ ገለፁልሃለሁ።››

‹‹ማርሲሉስ ሆይ÷ ቀጥተኛ የሆነውን ዝንባሌህን ዐውቃለሁ። አእምሮህ በቀጥተኛው መሥመር መመራትን ይፈቅዳል። ስለ ፍልስፍና ትምህርት ያለህን ልባዊ ግምት የማውቀው ነው።

‹‹እንደ ቀድሞው ይኸው ቢበቃህ ምን አለበት? በአንድ በተሰቀለ አይሁዳዊ ትምህርት ይህን ያህል ልብህ መነካቱ አይገባኝም።››

‹‹የጠቀስከው የፍልስፍና ትምህርት እስከዚህ ድረስ በቂ ሆኖ አላገኘሁትም። ወዲህ ለምትንገላታው ነፍሳችን የምታርፍበት ቋሚ ነገር የማይገኝበት መሆኑን አንተው ራስህ ታውቃለህ። ክርስትና ግን በእግዚአብሔር በራሱ የተገለጠ÷ በሞቱና በትንሣኤው የተረጋገጠ እውነተኛ እምነት ነው።››

‹‹የክርስቲያንን እምነት ትምህርት ምንም ሳታስቀር አስረድተኸኛል። ስለዚህ እምነት ያለህ ግምት÷ ይህ እምነት መልካም ሳይሆን አይቀርም የሚለውን ዐሳብ ሊያሳድርብኝ ጥቂት ቀርቶታል። የዚህ እምነት ተከታዮች ሁሉ እንደ አንተ ከሆኑ ለዓለማችን ታላቅ በረከት መሆናቸው አይጠረጠርም። ዳሩ ግን የእኔ አመጣጥ ስለ እምነት ለመከራከር አይደለም። እኔ የመጣሁት ስለ ራስህ ጉዳይ ነው።

‹‹ውድ ወዳጄ ሆይ÷ ክብርህ ሥልጣንህ÷ ዝናህ÷ መላው ሕይወትህ በአደጋ ላይ ተንጠልጥሎአል። ያደረግኸው ነገር ምን እንደ ሆነ ልብ አድርገህ አመዛዝነው። አንድ ታላቅ ጉዳይ እንድትፈጽም ተላክህ። የላከህም ባለ ሥልጣን ካንተ ይጠብቅ የነበረው ትእዛዙ ከፍጻሜ የሚደርስበትን መንገድ የሚከፍቱ ዜናዎች ይዘህ እንድትመጣ ነበር÷ ይህን በማድረግ ፈንታ ለስለላ ወደ ተላክህበት የጠላት ሰፈር

መከዳትህንና ከፍጹም ልብህ እንደ እነርሱ መሆንህን ለጄኔራሉ ገለጽክለት፡፡ እስከነ አካቱውም ወታደርነትህን በመዘንጋት በእነርሱ ላይ መግረያዬን አላነሣም አልክ፡፡ ወታደር የሆነ ሁሉ የሚዋጋውን ጠላት የመምረጥ መብት ቢኖረው÷ ሥነ ሥርዓት ባላስፈለገም ነበር፡፡ ወታደር ማድረግ ያለበት የተጣለበትን ግዴታ መፈጸም ብቻ ነው÷ እውነት አይደለም?››

‹‹እውነት ነው ሉኩሉስ፡፡››

‹‹ዋናው ጥያቄ በፍልስፍናና በክርስትና እምነት መካከል ምርጫ እንድታደርግ አይደለም፡፡ የቀረበልህ ምርጫ ክርስቲያን ትሆናለህ ወይስ ወታደር? የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የክርስትና እምነትና ወታደርነትን አጣምሮ መያዝ አይቻልም፡፡ ከሁለት አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል፡፡

‹‹ጉዳዩ በዚህ ብቻ የሚወሰን ቢሆን መልካም በሆነ ነበር፤ የክርስትና እምነት እመርጣለሁ ያልክ እንደ ሆነ የዕጣቸው ተካፋይ መሆን አለብህ፡፡ ስለ አንተ ተብሎ ልዩነት የማይደረግ መሆኑን መገንዘብ አለብህ፡፡ ወታደር ለመሆን የመረጥክ እንደ ሆነ ክርስቲያኖችን መቋቋም አለብህ፡፡››

‹‹ጉዳዩ አንተ እንደምትለው መሆኑን አልዘነጋሁትም፡፡››

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ የፈጸምከውን ከፍ ያለ ወንጀል ለመርሳት የተዘጋጁ የልብ ወዳጆች እንዳሉህ አትዘንጋ፡፡ ከተፈጥሮህ ያገኘኸውን ቆጥተኛነት የማውቅ በመሆኔ ስለ አንተ ጉዳይ ከጄኔራሉ ጋር ተከራክሬአለሁ፡፡ ጄኔራሉም ሁኔታህን ከመረመረ በኋላ ወታደራዊ ዝንባሌህን ከታላቅ ግምት ላይ ያዋለው መሆኑን አልሠወረም፡፡ በጥቂት ነገሮች የምትስማማ ብትሆን ማንኛውንም ነገር ለመርሳት የተዘጋጀ መሆኑን ገልጦልኛል፡፡

‹‹እኒህ የምስማማባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?››

‹‹እነዚህን ያለፉትን አራት ቀናት እንዳልነበሩ አድርገህ ቁጠራቸው፡፡ የተጣለብህን አደራ በመገንዘብ ወታደሮችህን አስከትለህ ክርስቲያኖችን ለማሠር ተነሣ፡፡››

ማርሴሉስም ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ እንዲህ አለ፡ ‹‹ሉኩሉስ ሆይ÷ እንደምታውቀው ከልብ እወድሃለሁ፤ ጓደኝነታችንም ጽኑ በሆነ

የፍቅር ሰንሰለት በመተማሥር ያለ አንዳች ሳንካ እስከ ዛሬ ቆይቶአል። ለእኔ ለጓደኛህ ያሳየኸውን ፍቅር እስከ መቼም ልረሳው አልችልም። የሆነ ሆኖ ግን በውስጤ አንድ ዐዲስ የሆነ ነገር ተፈጥሮአል። ያም ለአንተ እንግዳ ነገር ሳይሆንብህ አይቀርም። ለእኔ ግን ከዚህ ዓለም ክብርና ሀብት ይበልጥብኛል። ይህም እንደ ብርቅ ነገር አድርጌ የቈጠርኩት የእግዚአብሔርን ፍቅር ነው። ስለ እርሱም ክብርን፥ ሥልጣንንና ሕይወትን እንኳ አሳልፌ ለመስጠት የተዘጋጀሁ ሁኛለሁ። ከዚህ ውሳኔ ስንዝር አልናወጥም። ከእንግዲህ ወዲህ ከክርስቲያኖች እንደ አንዱ ቊጠረኝ።››

ሉኩሉስ አንዳች ነገር ሳይተነፍስ ወዳጁን በሐዘንና በትካዜ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተው። የጓደኛውን የልብ ጽናት በመገንዘብ በምንም ዓይነት መንገድ ዐሳቡን እንዲለውጥ ሊያደርገው አለመቻሉን ተረዳ።

በልዩ ልዩ የክርክር ዘዴ ሊያሳምነው ቢሞክር፥ የተደገሰለትንም ነገር በቃል አሠቃቂነት እያብራራ ቢያስረዳውም ማርሴሉስ ፍንክች አልል አለ። በመጨረሻም ከተቀመጠበት ሐዘን በሞላበት አኳኋን ብድግ ብሎ የሚከተሉትን ቃላት ተናገረ፡-

‹‹ማርሴሉስ ሆይ፥ ይህ አድራጎትህ ምንም ደስ የሚያሰኝ አይደለም። ወደ ጥፋት ስትገሰግስ ትታየኛለህ። መልካሙ ዕድልህ የሰጠህን ክብርና ሥልጣን እምቢ ብለህ የእነዚያን ወራዶች ዕድል መምረጥህ የሚያሳዝን ነው። አጥፊ የሆነ ምርጫን እንድትለውጥ የጓደኝነቴን ያህል መክሬሃለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ ምክሬን ብታቃልል የራስህ ጉዳይ ነው።››

‹‹አሁንም ላስረዳህ የምፈልገው አንድ ነገር አለ። ጄኔራሉ አስፈላጊ የሆነውን ውሳኔ አድርጓል። ከዛሬ ጀምሮ ማዕረግህንና ሥልጣንህን ተገፈሃል። እሥረኛም ነህ። ነገ ፍርድህን እንድትቀበል ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለ ሥልጣኖች ፊት ትቀርባለህ። እስከዚያው ድረስ ብዙ ሰዓቶች መኖራቸውን አትዘንጋ። ከዚህ ውሳኔ ለማምለጥ ብትፈልግ ግን ዕወቅበት። ጊዜ ማባከን አስፈላጊ አይደለም። በተቻለህ መጠን ከዚህ ጥፋ። ከቄሣር በቀል ለመሠወር የምትችልበት ከሰማይ በታች አንድ ስፍራ ብቻ አለ።››

ማርሴሉስም የመጨረሻውን የጓደኛውን ቃል በጸጥታ ካዳመጠ

በኋላ ማዕረጉንና የክብር ልብሱን አንድ ባንድ እያወለቀ አስቀመጠ። ግርማ ሞገስ አጎናጽፎት የነበረውን የመኰንንነት የማዕረግ ልብሱን አወላልቆ አንድ ተራ ሰው በመምሰል ጓደኛው ፊት ቆመ።

‹‹ደኅና ሰንብት ማርሴሉስ! ምናልባት በምድር እንደ ገና እንገናኝ ይሆናል። የቸገረህ እንደ ሆነ ግን እኔ የምገኝበትን ስፍራ ታውቃለህ። ታማኝነቱን የማያጓድል ጓደኛህ መሆኔን አትዘንጋ።››

ሁለቱ ጓደኞች በጋለ ፍቅር በመተቃቀፍ የመጨረሻ ስንብት አደረጉ። ማርሴሉስም ከዚያ ለማምለጥ ጉዞውን ቀጠለ።

ከሰፈሩ ወጥቶ የሕዝብ አደባባይ ወደ ተባለው ስፍራ ደረሰ። በሚያልፍባቸው መንገዶች ግራና ቀኝ አያሌ የሆኑ መቅደሶች፥ ታሪካዊ ዓምዶችና ሐውልቶች ይታያሉ።

የጢጦስ ቅስት፥ በዕንቍና በዕብነ በረድ ያጌጠው የቄሣር ቤተ መንግሥት ግርማና ሞገስ ተጎናጽፈው ቆመዋል። በአንድ በኩል ግዙፍ የሆነው የኮሌሴዩም ግድግዳ፥ እልፍ ብሎ የሰላም መቅደስ በውበትና በግርማ በማሸብረቅ አለን አለን ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ካፒቶሊን የተባለው ኮረብታ ግሩም የሆኑ መቅደሶችን በቁንጮው ላይ ተሸክሞ ኩል ከመሰለው ሰማይ በታች ስፍራውን ይዞአል።

ማርሴሉስ ጉዞውን ወደ ካፒቶሊን ኮረብታ ጫፍ አመራ። ከጫፉም እንደ ደረሰ በዙሪያው የሚገኘውን ውበት ተመለከተ። የካፒቶሊን ኮረብታ ጫፍ በዕብነ በረድ የተነጠፈ አራት ማዕዘን አደባባይ አለው። በግራና በቀኝ ድንቅ የሆኑ መቅደሶች ቆመው ይታያሉ።

በአንድ በኩል ካምፑስ ማርቲዩስ ከሜዲቴራንያን ባሕር ጋር ለመቀላቀል በሚገሰግሰው የቴቤር ወንዝ ተከቦአል። በሌላ በኩል ደግሞ ከተማይቱ ከቀድሞው ወሰኖችዋ አልፋ ተርፋ ከመጠን በላይ ተስፋፍታ ትታያለች።

በከተማው ውስጥ መቅደሶች፥ ዓምዶችና ሐውልቶች በያሉበት ቆመዋል። ከመጠን በላይ የሆኑ ታሪካዊ ቅርሶች ከተማይቱን አጣበዋታል። ፏፏቴዎችም በያሉበት ውሃቸውን ይተፋሉ።

ሰረገሎችና መንኰራኩሮች መንገዱን ሞልተውታል። የሮም

የጦር ሠራዊት ከነትጥቁ ወዲህና ወዲያ ይላል። በጠቅላላው የቁማርኞች መዲና የሆነችው ሮም የሕይወትና የሥራ ትርምስ ወደር የሌለው ነበር። በከተማይቱ አካባቢ በሚገኘው ሜዳ ላይ አያሌ መንደሮች፥ በምቾትና በብልጽግና የተሞሉ ቃላላት አዳራሾች ይታያሉ። በአንድ በኩል የበረዶ አክሊል የደፋው የአፔኒኒ ተራራ አናቱን ወደ ሰማይ አቅንቶአል። በሌላ በኩል ደግሞ ነፋስ ወዲህ ወዲያ የሚያማታው የሜዲቴራኒያን ባሕር ከበረቱ ጋር ትልቅ ትግል ገጥሟል።

ማርሴሉስ ድንገት አንድ ድምፅ ሰማ። ዘወር ብሎ ቢመለከት አንድ ጭርንቁስ የለበሰ ከሲታ ሰውዬ አስፈሪ የሆነ የፍርድ ቃላት ሲናገር ሰማ። አስተያየቱና አኳኋኑ አእምሮው የተናወጠ መሆኑን ያስረዳ ነበር።

‹‹ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች
የአጋንንትም ማደርያ ሆነች
የርኩሳንም መናፍስት መጠጊያ
የርኩሳንና የተጠሉ ወፎች መጠጊያ ሆነች
እግዚአብሔርም ዐመፅዋን ዐሰበ
እርስዋ እንደ ሰጠች መጠን ብድሯን መለሰላት
እንደ ሥራዋ ሁለት ዕጥፍ ደረሰባት
ራስዋን እንደ አከበረችና እንደ ተቀማጠለች
ስለዚህ በአንድ ቀን መቅሠፍቶችዋ ይመጣሉ
ሞት ሐዘን ራብም
በእሳትም ትቃጠላለች
የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና።››

በብዛት የሚቴጠሩ ሰዎች መጥተው ሰውዬውን ከበው ንግግሩን በአድናቆት ሲሰሙ ወታደሮች መጥተው እየገፈተሩ ወሰዱት።

ማርሴሉስ በሀሳቡ፥ ‹‹ራሱ፥ በስደትና በመከራ የተናወጠ ምስኪን ክርስቲያን ሳይሆን አይቀርም›› አለ። ሰውዬውም ያንኑ የፍርድ ቃል እየደጋገመ ሲናገር ብዙ ሰዎች እየተከታተሉ ይሣለቁበት ጀመር። በመፈረሻውም ድምፁ እየራቀ ሄደ። ማርሴሉስም፥ ‹‹ጊዜ ማባከን የለብኝም፤ ተነሥቼ ልገስግስ›› አለ። ተነሥቶም መንገዱን ቀጠለ።

# የካታኮምቡ ውስጥ ኑሮ

‹‹የብርሃን ጭላንጭል የማይደፍረው፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ የሰፈነበት ስፍራ፡፡››

የማርሴሉስ ሽሽት ወደ ካታኮምቡ አደረሰው፡፡ ክርስቲያኖችም በደስታ ተቀበሉት፡፡ ከእሰቶቹ ጋር ተገናኝቶ ስለ ወሰደው እርምጃ በታላቅ ናፍቆት አደመጡት፡፡ ከክርስቲያኖች ጋር መከራን ለመቀበል ውሳኔ በማድረጉ ቢደሰቱም እንኳ በደረሰበት ችግር ምክንያት የተሰማቸውን የርኅራኄ ስሜት አልሸሸጉም፡፡

እንደ ገና ከእምነት ወገኖቹ ጋር በመደባለቅ ስለ ክርስትና እምነት ያለው ዕውቀት ከዕለት ወደ ዕለት እየደረጀ ሄደ፡፡ የካታኮምቡ ውስጥ ኑሮም በብዙ ዓይነት መልኩ ተገለጠለት፡፡

በብዛት በካታኮምቡ ውስጥ ለሚኖሩት ክርስቲያኖች የሚሆን ምግብ የሚመጣው ከከተማይቱ ጋር የዘወትር ግንኙነት በማድረግ ነበር፡፡ የምግቡም ማቀበል ተግባር የሚፈጸመው የሌሊቱን ጨለማ ተገን በማድረግ ነበር፡፡

ይህንም አደገኛ ሥራ የሚያከናውኑት በድፍረታቸው የታወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችና ወጣቶች ልጆች ይህንኑ ተግባር እንዲፈጽሙ ይላኩ ነበር፡፡

ከወጣቶች መካከል ፖሊዮንን የሚያህል ቀልጣፋ የምሥጢር መልእክተኛ አልነበረም፡፡ እጅግ ብዙ በሆነው በሮም ነዋሪ ሕዝብ መካከል ሳይታወቁ ወዲህ ወዲያ ማለት በጣም የሚያስቸግር ነገር አልነበረም፡፡ ከዚህ የተነሣ ክርስቲያኖች በምግብ ረገድ እምብዛም ችግር አልደረሰባቸውም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ግን የተላኩት መልእክተኞች በጠላቶቻቸው እጅ ውስጥ በመግባት ከሄዱበት ስፍራ ሳይመለሱ የሚቀሩ ነበሩ፡፡

ጥልቅ በሆኑት ዋሻዎች ውስጥ በብዛት የሚቴጠሩ ምንጮች በመኖራቸው በውኃ በኩል በካታኮምቡ ውስጥ በሚኖሩት ክርስቲያኖች ላይ ምንም ችግር አልደረሰባቸውም ነበር፡፡ በአውሬዎች የተበጫጨቁትን፥ በእሳት የተቃጠሉትን የክርስቲያኖች አፅም ቅሪት በመሰብሰብ የሚያረገው የጨለማ ውስጥ ፍለጋ ከሁሉ የባሰ አደገኛ

ነበር። ክርስቲያኖች የዘመዶቻቸውንና የወዳጆቻቸውን የተቀደሱ አፅሞችና ቅሬታዎች ከአደጋና ከሞት መንጋጋ አውጥቶ የሚገባቸውን የክብር ዕረፍት እንዲያገኙ ለማድረግ ያሳዩት የነበረው ድፍረትና ልበ ቁራጥነት ወደር የሌለው ነበር። የሰማዕታትን ክብር የሚገልጹ ሥነ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ። አስከሬኖቹም በካታኮምቡ ውስጥ በተፈለፈሉት ዋሻዎች ውስጥ እንዲያርፉ ያደርጋሉ። መቃብሩ ከተሰሰነ በኋላ የሟቹ ስምና የአሟሟቱ ሁኔታ በአንድ ሰሌዳ ላይ ይቀረፃል።

የቀደሙት ክርስቲያኖች የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ ያደርጉ ስለ ነበር የሚጠፋው የማይጠፋውን የሚጎናጸፍበትን፥ አላፊው ሕይወት በዘላለማዊው ሕይወት የሚተካበትን ጊዜ በተስፋ ይጠባበቁ ነበር።

ከዚህ የተነሣ በሰማይ ታላቅ ክብር የሚጠብቀው የሞቱትን ምእመናን ሬሳ የትም ወድቆ እንዳይቀር በማለት ከያለበት እየሰበሰቡ የመጨረሻው የእምቢልታ ድምፅ እስከሚሰማበት ቀን ድረስ ዕረፍትና ጸጥታ እንዲያገኝ በክብር ያስቀምጡት ነበር።

የክርስትና እምነት በተሰበከባቸው ባለፉት ትውልዶች አያሌ አብያተ ክርስቲያናት በሮምና በአካባቢዋ ተመሥርተው የምእመናንም ቍጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየበረከተ ይሄድ እንደ ነበር የሚታወስ ነው። በዚህ ጊዜ ሁሉ ሕይወታቸውን ለእምነታቸው የሠውት ሰማዕታት ሁሉ የሚቀበሩት በካታኮምቡ ውስጥ ነበር። ከዚህ የተነሣ ካታኮምብ በሚል ስም የታወቀው ምድር ማኅፀን ጸጥታ የነገሠበት የሙታን ከተማ ይመስል ነበር። በዚያ ውስጥ ያረፉት ሁሉ በቅጽበት ተለውጠው ጌታን በአየር ላይ የሚገናኙበትን ጊዜ በታላቅ ጸጥታ ይጠባበቁ ነበር።

በካታኮምቡ ውስጥ አልፎ አልፎ ጣራቸው ከፍ ያለና ብዙ ሰዎች ለመያዝ የሚችል ክፍሎች ነበሩ። አብዛኞዎቹ ምቾት አልነበራቸውም። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ክርስቲያኖቹ በብዛት በመሰብሰብ እንደ ልባቸው ለመተንፈስና አንድነታቸውን ለማጽናት ስብሰባዎችን በማድረግ የማይገፋውን የመከራ ጊዜ አብረው ያሳልፉ ነበር።

ክርስቲያኖች ይኖሩበት የነበረው ጊዜ በብዙ ዓይነት መንገድ የከፋ ነበር። ይህንንም በየዕለቱ የሚደርስባቸው ስደትና መከራ ያስረዳል። ሮም ፍርድና ትክክለኛነት የሰፈነበት የማዛት ዘመን እንደ ነበረ የታሪክ ምስክርነት ያረጋግጣል። እያደር እያደር ግን የሮም አገዛዝ

ሁኔታ እየተለወጠ ሄደ። በፍርድና በትክክለኛነት ስፍራ ጭቆናና ሕገ ወጥነት ተተኩ። ሴራ÷ አድማና ክሕደት የሮምን የቀና አገዛዝ ጤና የሚነሡ ጸሮች ሆኑ። ብዙዎቹ ልበ ቀና ሮማውያን የጊዜውን ሁኔታ በመገንዘብ የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ ከዳር ቆመው ከመመልከት በስተቀር ሊፈጽሙት የቻሉት ነገር አልነበረም።

የክርስቶስ የወንጌሉ ብርሃን ለሰዎች የተገለጸው የጊዜው ሁኔታ እንደዚህ ጭልምልም ባለበት ወቅት ነው። የክርስቶስ ወንጌል በሰዎች ልብ ውስጥ ስፍራ ለማግኘት ከብዙ ኃያላን ጠላቶች ጋር መጋደል አስፈለገው። የተከታዮቹም ኑሮ ምቾት አልነበረውም። ከዘመድ÷ ከሀብት÷ ከዝናና ከሕይወት የሚለይ ብርቱ ተጋድሎ ማድረግ ነበረባቸው። የክርስቶስ ተከታዮች እየበረከቱ በሄዱበት መጠን ክፋትም ኃይሉን እያደረጀ መሄድ ጀመረ።

የሮማውያን ኑሮ ከሕግ የወጣ ሆነ መንግሥታቸውም ወደ መውደቅ አዘቅት ይገሰግስ ጀመር።

ከዚህ የተነሣ የክርስትናን እምነት ከምድር ገጽ ለማጥፋት የታቀደው ስደት ተጀመረ። ከቄሣሮች ዘንድ የሚወጣው አዋጅም ክርስቲያኖችን በታላቅ ሥቃይ ላይ የሚጥል ሆነ። ክርስቲያኖች በየዕለቱ በክርስቶስና በሞት መካከል ምርጫ እንዲያደርጉ በመገደዳቸው ከእልቂቱ የተረፉት ከቤታቸው÷ ከዘመዶቻቸውና ከቀን ብርሃን ተለይተው በካታኮምቡ ውስጥ መኖርን መረጡ።

የሮማውያን ልብ ደነደነ። ዓይኖቻቸውም ታወሩ። የሕፃናት ንጽሕና÷ የሴቶች ደካማነት÷ የሽማግሌዎች ሽበት÷ የእምነት ጽናት÷ የፍቅር አሸናፊነት ልባቸውን ሊነካው ሳይችል ቀረ። በመንግሥታቸው ላይ ያንዣበበው የውድቀትና የጥፋት ደመና አልከበዳቸው አለ።

በዚህ ስደትና ጭንቀት በነገሠበት ዘመን ካታኮምብ በሚል ስም በታወቁት ዋሻዎች ውስጥ ባለፉት ትውልዶች ሕይወታቸውን ለእምነታቸው ሲሉ የሠውት ሰማዕታት አርፈው የትንሣኤን ቀን ይጠባበቃሉ። በካታኮምቡ ውስጥ ዘመድ ዘመዱን÷ ልጆች ወላጆቻቸውን÷ ወላጆች ልጆቻቸውን ቀብረዋል። ከአውሬዎች መንጋጋ የተረፉት÷ በእሳት ነበልባል የከሰሉት÷ በመስቀል ላይ የተሠቃዩት የሰማዕታት አፅሞች በዚሁ ስፍራ ውስጥ ቦታ ቦታቸውን ይዘው

ይገኛሉ። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በካታኮምቡ ውስጥ ያረፈ ዘመድ የሌለው አልነበረም። ለክርስቲያኖች ስፍራው የተባረከ÷ አየሩ የተቀደሰ ነበር። በጭንቀታቸው ጊዜ ሁሉ ወደዚህ ስፍራ ይጠጉ የነበረው በዚሁ ምክንያት ነው።

ከዚህም በቀር በጭንቀታቸው ወራት ከእነዚህ የምድር ማኅፀን ከሆኑት ዋሻዎች በስተቀር ሌላ መጠጊያ አልነበራቸውም። የብስ አቋርጠው÷ ባሕር ሰንጥቀው ወደ ሌላ አገር የመሄድ ተስፋቸው አነስተኛ ነበር። የሮም ሥልጣን ያልደረሰበት አገር ባለመኖሩ ጽኑ ከሆነው የፖሊስ ድርጅት አምልጦ፤ ከቍጣዋ ርቆ በሰላም መኖር አስቸጋሪ ነበር። ከከፍተኞች እስከ ተራ ሰዎች ለሮም ሥልጣን አሜን ብለው መገዛት ነበረባቸው። ከሥልጣኑ የወረደ ንጉሥ እንኳ ከሮም በቀል የሚያመልጥበት መውጫ መንገድ አልነበረውም። ቄሣር ኔሮ ከሥልጣኑ በወረደ ጊዜ ከከተማይቱ ወጣ ብሎ ራሱን ከመግደል በስተቀር ሊፈጽመው የቻለ ሌላ ነገር አልነበረም። ኅብሩ በበዛውና በተወሳሰበው የካታኮምቡ ዋሻዎች ውስጥ ግን የሮም ኃይል በጣም የደከመ ነበር። ከዚህ ስፍራ ውስጥ ክርስቲያኖችን እያደኑ ለማውጣት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ ፍሬ ቢስ ሆነው ቀርተዋል።

በስደትና በመከራ ተባረው ወደ ካታኮምቡ ዋሻዎች ውስጥ የገቡት ክርስቲያኖች ቍጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረከተ ሄደ። በቀን እየተሰበሰቡ በመጽናናት÷ በእምነት ወገኖቻቸው የሆኑት ሲሞቱ በመቅበር÷ በሌሊት ደፋሮች መልእክተኞቻቸውን ወሬ እንዲያቀብሏቸው ወይም የሞቱትን የሰማዕታት አፅም እንዲያመጡ በመላክ የጭንቀት ኑሮአቸው በመጠኑ ሥርዓትና መልክ እንዲኖረው ይጥሩ ነበር። በሮም ግዛቶች ውስጥ በየጊዜው በተነሡት ስደቶች ምክንያት የሞቱት የምእመናን ቍጥር ከመጠን ያለፈ ቢሆንም በሮም ከተማ የተጣለው የክርስቲያን መሠረት ብዙ ጉዳት አልደረሰበትም።

በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩት ምእመናን ሕይወት ከውጭው ጉዳት የተጠበቀ ነበር። ዳሩ ግን መጨረሻ በሌለው ጨለማ ውስጥ የሕይወት ጣዕም በምን ይታወቃል? ነፍስን በሚያሠቅቅ ስፍራ ውስጥ የሥጋ ደኅንነት ቢጠበቅ ምን ረብ አለው? የማንኛውም ሰብአዊ አቅዋም በብርሃን እጦት የሚደርስበት ጉድለትና ሳንክ ተዘርዝሮ የሚያልቅ

አይደለም። የአካላት መድከም አእምሮን ያቃውሳል። በእንደዚህ ያለ ስፍራ እንዲኖሩ በተገደዱ ሰዎች ላይ ሐዘን÷ ሥጋት ጥርጣሬና ተስፋ መቍረጥ እንደሚነግሥባቸው የታወቀ ነው። በየአደባባዩ በታላቅ ቁራጥነት ከሞቱትና በእሳት እንዲቃጠሉ ከተደረጉት ሰማዕታት ይልቅ በዚህ አሠቃቂ ዋሻ ውስጥ በእምነት እስከ መጨረሻው መጽናት ከፍ ያለ ብርታትን የሚጠይቅ ነበር። በካታኮምቡ ውስጥ እንዲኖሩ የተገደዱት ክርስቲያን ስደተኞች ሕይወት በቀን ጨለማ ውስጥ የተዋጠ ነበር። በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ ስደትንና መከራን መታገሥ ከታላቅ ጀግንነት የሚቈጠር ነው።

የስፍራው ቅዝቃዜ አጥንት የሚሰብር ነበር። ወለሎቹ÷ ጣራዎቹና ግድግዳዎቹ ለጉዳት በሚሰጥ ርጥበት ተበክለዋል። ሌትና ቀን ከሚበሩት ጧፎች የሚወጣው ጢስ በዙሪያው የሚገኘውን አየር ሰውነትን የሚያፍን መርዝ አድርጎታል። በዚህ ጭንቀት ሁሉ ውስጥ የክርስቲያኖች እምነት ምንም አልተናወጠም። ክርስቲያኖች የታገሡትና የተቋቋሙት የመከራ ማዕበል ሲታይ ለጀግንነታቸው በሮም ታሪክ ውስጥ ተመሳሳይ አይገኝለትም። በሰውነት የጠነከሩት ወይም በኃይል የደረጁት ብቻ ሳይሆኑ÷ ሕፃናትና ሴቶች ሳይቀሩ ለስደቱና ለመከራው አልተበገሩም። ሞትን እንደ ቀላል ነገር በመቍጠር የጭንቀት ኑሮአቸውን በደስታና በተስፋ ያሳልፉ ነበር።

በሚመጣው ዓለም የሚጠብቃቸውን ክብር በመገንዘብና ጥልቅ በሆነው በክርስቶስ ፍቅር በመጽናናት ስለ ነፍሳቸው ደኅንነት ብቻ በማሰብ ወደዚህ አሠቃቂ ስፍራ ውስጥ ገብተው መኖርን መረጡ።

ክርስቲያኖች ለሚኖሩበት ስፍራ ምቾት ለመስጠት በብዙ ደክመዋል። የዋሻዎቹን ግድግዳዎች በኖራ እየቀቡ ሥዕሎችን ይቀርፁባቸው ነበር። እነዚህም ሥዕሎች ለአምልኮ የተደረጉ ሳይሆን ‹‹በእምነት መንግሥታትን ድል የነሡትን÷ ጽድቅ ያደረጉትን÷ የተስፋ ቃል የተቀበሉትን፤ የአንበሶችን አፍ የዘጉትን፤ የእሳትንን ኃይል ያጠፉትን፤ ከሰይፍ ስለት ያመለጡትን÷ በድካማቸው የበረቱትን÷ በጦርነት ኃይለኞች የሆኑትን፤ የባዕድ ጭፍሮችን ያባረሩትን›› ጥንታውያን የእምነት አባቶችን የሚያሳስቡ ነበሩ። የእነርሱም መታሰቢያ ጭንቀታቸውን እያቃለለ አሳዛኝ ለሆነው ኑሮአቸው ትርጉም ይሰጠው ነበር።

ስብሰባ በሚያደርጉባቸው ክፍሎች ውስጥ የሚታዩት ንዋያተ ቅድሳት ብዙ አልነበሩም፡፡ የጌታ ሥጋና ደም የሚፈተትበት (የሚቆረስበት) አንድ መጠነኛ ጠረጴዛ በክፍሉ መካከል ቆሞ ይታይ ነበር፡፡

የክርስትና እምነት ከክፋትና ከክሕደት ጋር ከፍ ያለ ውጊያ አድርጓል፡፡ ከዚህ የተነሣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አንዳንድ ፍጹም ያልሆኑ ባህሎች መታየታቸው የሚያስደንቅ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ከሐዋርያት ዘመን በመጠኑ የተለየ ቢሆንም÷ ምእመናንን ከእውነተኛው እምነትና አካሄድ መሥመር ያዛንፋል ተብሎ የሚያሠጋ ያህል አልነበረም፡፡ ከዚህም በቀር መሠረታውያን የሆኑት የክርስትና ትምህርቶች በምንም ዓይነት መንገድ አልተለወጡም ነበር፡፡ የሰው ኃጢአተኝነት÷ የእግዚአብሔር አብ ምሕረት÷ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ልብ ውስጥ ማደር÷ በክርስቶስ ምክንያት ለሰዎች የተሰጠው ደኅንነት÷ ቅዱስ÷ የሆነው የክርስቶስ ደም የሚሰጠው ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ ጥቅም÷ የክርስቶስ ትንሣኤና ዳግመኛ መምጣቱ÷ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያኒቱ የቆመችባቸው መሠረቶች ነበሩ፡፡

ለነፍሳቸው መልሕቅ ያደረጉትን ሰማያዊ ተስፋ የገናናው የቄሣር መንግሥት ማዕበላዊ ቍጣ ሊያናውጠው አልቻለም፡፡ የተጠጉትንም ጽኑ አምባ ሊያፈርሰው የቻለ ኃይል አልነበረም፡፡

በመከራ ጊዜ የሚያበረታ ጽኑ እምነት ነበራቸው፡፡ እምነታቸውም የተመሠረተው በአብ ቀኝ በተቀመጠው አለት ላይ ነበር፡፡ ከእምነታቸው የበለጠ አንዳች ነገር አልነበራቸውም፡፡ እምነታቸው አሠቃቂ የሆነውን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ በሚገደዱበት ጊዜ የሚተነፍሱት እስትንፋሳቸው ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ከምድር ገጽ የጠፉ በሚመስልበት ጊዜ በተስፋ ዓኖቻቸውን ወደ አርያም እንዲያሻቅቡ የሚያደርጋቸው እምነታቸው ነበር፡፡

ሕይወታቸው ይመራ የነበረው ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የኦሪትና የነቢያት ፍጻሜ ባለው ፍቅር ነበር፡፡ ወገን እየለዩ በእምነት የመጣላት መንፈስ አልነበራቸውም፡፡ የሚቋቋሙት አንድ የጋራ ጠላት

ነበራቸው። የጋራ ፍቅራቸው ወገንንና ማዕርግን ሳይመለከት ሁሉንም እኩል የሚጠቀልል ነበር። ከዚህም የተነሣ ወዳጅ ለወዳጁ ሕይወቱን ለመሠዋት አያመነታም ነበር። ሕይወታቸውን እስከ መሠዋት ብርታት የሰጣቸው በልባቸው ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ነበር።

የደረሰባቸው ስደትና መከራ በዘመኑ ጨለማ ውስጥ የሚያንጸባርቅ የእምነትና የፍቅር ጽናት ሰጣቸው። ሁሉም በእምነታቸው የማይናወጡ ቊርጠኞች ነበሩ። ግብዝና በመካከላቸው ስፍራ አልነበረውም። ብርቱዎች እየደረጁ ደካሞቹ ብርታት እያገኙ ይሄዱ ነበር። ይኖሩበት የነበረው ዘመን ክርስቲያኖች በሆኑት ሕይወት ላይ አደጋን የማያስከትል ቢሆንም እምነታቸውን በይፋ እየገለጡ የሚደርስባቸውን መከራ በደስታ ከመቀበል በስተቀር ወደ ኋላ የማፈግፈግ ስሜት አላሳዩም። በዓለምና በክርስቲያኖች መካከል የማይጣስ ድንበር ነበር። ክርስቲያኖችም ያንን ድንበር አልፈው ከዓለማውያን ጋር የመተባበር ፍላጎት አልታየባቸውም።

ጥቂት ቃላትን መተንፈስ÷ አንዳንድ ድርጊቶችን መፈጸም ከሞት ሊያድናቸው ይችል ነበር። ዳሩ ግን እንደበታቸው ጣዖታትን ማመስገን÷ እጆቻቸውም ለጣዖታቱት ማገልገል አሻፈረኝ በማለቱ ሥቃይንና ሞትን መረጡ። የክርስትና እምነት መሠረታዊ ትምህርት የተቀበሉት በአእምሮአቸው ብቻ ሳይሆን በፍጹም ልባቸው ነበር። ክርስቶስም በነበር የተወሰነ የታሪክ ሰው ብቻ ሳይሆን ትላንት ዛሬና ዘለዓለምም የማይለወጥ መሆኑ በልባቸው ውስጥ እንደሚሰማቸው ጥርጥር አልነበረውም። ክርስቶስ በምድር ላይ ያሳለፈው ሕይወት÷ ሕያውነት ያለው አርአያቸው ነበር። የርኅራኄውንና የትሕትናውን÷ የትዕግሥቱንና የየዋህነቱን ፍለጋ ሆነ ብለው ይከተሉ ነበር።

የአንድን ሰው እምነት በሥራው መስተዋትነት ይመለከታሉ ለክርስቶስ ሞት የሚሰጡት ግምት ከማንኛውም ነገር የላቀ ነበር። ለሰዎች ቤዛ ሆኖ መሞቱን ያለ አንዳች ጥርጥር ያምኑ ነበር። ከሞት ተነሥቶ በአብ ቀኝ በክብር መቀመጡና በሰማይና በምድር ላይ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን በመለኮታዊ ሥልጣን እንደ ተገለጠ እውነት ይታመኑበት ነበር።

ለእምነታቸው ሲሉ መስቀላቸውን በመሸከም በእሳት የተቃጠሉ÷

በደንጊያ የተወገሩ፥ ለአናብስት የተወረወሩ ብዙ ናቸው። በዚህ የክርስቶስ ተከታዮች መሆናቸውን በይፋ ለዓለም ገልጠዋል።

ይህንንም ለመረዳት ብዙ ዘመናት ሙሉ ይኖሩበት የነበረውን የካታኮምቦቹን ሁኔታ መመርመር ይበቃል። ለሙታን እንኳ መቀበሪያ ለመሆን በማይሆነው የጨለማ ዓለም ውስጥ ክብራቸውን፥ ሀብታቸውንና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ደኅና ሁኑ ብለው በታላቅ ልበ ቈራጥነት በሥቃይ መኖርን መረጡ።

እነዚህ የእውነት ምስክሮች በዓለም ላይ ድሆች፥ የተናቁና የተጠሉ ነበሩ። ምሕረትን ለማግኘት ያቀረቡትን አቤቱታ የሚያደምጣቸው ጠፋ። በምሕረት ፈንታ ጭካኔና ሥቃይ የዕለት ድርሻቸው ሆነ። ምድር ማኅፀንዋ ወደ ሆኑት ጥልቅ ዋሻዎች ውስጥ አግብታ ከጭንቀትና ከስደት ፋታ እንዲያገኙ በማድረግ ከወገኖቻቸው ይልቅ ርኅራኄዋን ዐሳይታቸዋለች።

በዚህ ሁሉ መካከል የማርሴሉስ ወደ ክርስትና እምነት መመለስ ድንገተኛ ነገር ነበር። ይህን በመሰለ አኳኋን ከስሕተት ጎዳና ወደ እውነት መሸጋገር በእርሱ ብቻ አልተጀመረም። የአሕዛብን ሥርዓቶችና የፍልስፍናን ትምህርቶች የሞከረ ሰው ቢሆንም፥ አንዳች ረብ ሳያገኝባቸው ቀርቶአል። ከክርስትና እምነት ጋር ያደረገው ግንኙነት ግን የልቡን ፍላጎት አጠቃሎ ሰጠው። ባዶ የነበረችው ነፍሱም በሰላም ተሞላች።

ዓይኖቹ ተከፍተው የጽድቅን ፀሐይ ተመለከቱ። በዚያ ግሩም ብርሃን አማካይነት ብቻ ምሥጢራትን ተረዳ። ስደትና መከራ ከሚቀበሉት የጽድቅ ሠራዊት ጎን ተሰልፎ የሚደርስበትን ሁሉ በደስታ ለመቀበል ቍርጠኛ ውሳኔ አደረገ።

ይህን በመሰለ አኳኋን ወደ ክርስቶስ በንስሐ የሚመለሱ ብዙ ነበሩ። እንደ ማርሴሉስ የአሕዛብ የጭፈና እምነት ያደከማቸው ሰዎች ቍጥር ብዙ ነበር። የክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተሰበከላቸው ጊዜ አሕዛብ እውነትን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም። ያን ጊዜ በታወቀው ዓለም ወንጌል የተዳረሰው በዚሁ መንገድ ነበር።

ማርሴሉስ ዐሳቡን ቈርጦ ከክርስቲያኖች ጋር በካታኮምቡ ውስጥ ለመኖር ከወሰነ በኋላ የተሰፉቸው፥ የፍርሃታቸውና የደስታቸው

ተካፋይ መሆን ጀመረ። እምነታቸውና አለኝታቸው፣ እንዲሁም ዘለዓለማዊ ተስፋቸው ለልቡ መጽናኛ ሆኑት። የእግዚአብሔርንም ቃል ሌትና ቀን በመመርመሩ መንፈሳዊ ሕይወቱ እየበሰለ ሄደ።

በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች ለጸሎትና ለመንፈሳዊ ግንኙነት በቂ ጊዜ ነበራቸው። ከዓለም መውጣት መውረድ የተለዩ በመሆናቸው የነፍሳቸውን ጉዳይ ብቻ ያስቡ ነበር።

የዓለምን ደስታና ፍቅር እርግፍ አድርገው ትተው ነበር። ከአንደበታቸው የሚመነጩት ቃላት እግዚአብሔርን የሚያከብሩና የመንግሥቱን ጉዳይ የሚያጠነክሩ ነበሩ። በእምነት ጸንቶ መኖር÷ በመከራም ጊዜ በቈራጥነት የሞት ሽለቆን መሻገር የሚያስከትለውን ብዕዕና ማውጋት አይሰለቻቸውም ነበር።

የቀድሞዎቹን ሰማዕታት ዜና በማውሳት የራሳቸውን የመጨረሻ የእምነት ፍሬ በናፍቆት ይጠባበቁ ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ÷ የመጨረሻው ጥሪ የሚሰማበትን÷ ሙታን የሚነሡበትን÷ ሕያዋን የሚለወጡበትን በደሙ የተዋጁት የምድር ነገዶች በአየር ላይ ከጌታ ጋር የሚገናኙበትን÷ በክርስቶስ የዙፋን ፍርድ ፊት ቀርበው የታማኝነታቸውን ዋጋ የሚቀበሉበትን ዕለት ተስፋ ያደርጉ ነበር።

ማርሴሉስም በእንደዚህ ያለ አኳኋን የሙታን ብቻ ሳይሆን በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሕያዋን መከማቻ የሆነውን የካታኮምቡን ውስጥ ኑሮ በቅርቡ ሊመለከት ቻለ። በዚያ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች መተፋፈግ ያገረጣቸው÷ መከራ ያደከማቸው ቢሆኑም በሚኖሩበት ጨለማ ውስጥ ያሳዩት የነበረው ደስታና ብሩህ ገጽ በሮም አደባባዮች ከሚታየው የበለጠ ነበር። እርስ በርሳቸው በሞቀ ፍቅር ይዋደዱ ነበር። ዝምድናቸውና መተሳሰባቸው በጽኑ አቋራኝተዋቸው ይታያሉ። የሐዘናቸው እንባ ከሞቱባቸው ሰማዕት ደም ጋር በመቀላቀሉ÷ ቋሚዎቹን ከሟቾቹ ጋር አስተሳስሮአቸዋል። በእነዚህ አሠቃቂ ዋሻዎች ውስጥ እንዲኖሩ የተገደዱት ሁሉ ስደትና መከራን÷ ሐዘንና ጭንቀትን ድል ነሥተዋል። በዚያም ውስጥ በተስፋ÷ በእምነት÷ በፈገግታ ብርሃን የንጋትን ኮከብ ተመልክተዋል። ከሚያዝነውና ከሚያለቅሰው አንደበት የደስታ ቃላት መንጭተዋል።

# ስደትና መከራ

«የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁትን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናናት ያስፈልጋችኋል።»

ስደቱና መከራው እየተፋፋመ ሄደ። ማርሴሉስም በካታኮምቡ ውስጥ ባሳለፋቸው ጥቂት ሳምንቶች ውስጥ አያሌ ሰዎች እየሸሹ መጠጊያ ለማግኘት ወደ ዋሻዎቹ ውስጥ ይገቡ ጀመር። ከዚህ ቀደም ይህን ያህል ሰዎች በካታኮምቡ ውስጥ ተሰብስበው ዐያውቁም። ለወትሮው የሮም ባለ ሥልጣኖች የሚያሳድዱት ከክርስቲያኖች መካከል ቀንደኞቹን እየመረጡ ነበር። የአሁኑ ስደት ግን ክርስቲያን በሚል ስም የሚጠራውን ሁሉ ከምድር ገጽ ለማጥፋት የታቀደ ነበር። በሽማግሌዎችና በሕፃናት÷ በወንዶችና በሴቶች÷ በድሃና በባለ ጠጋ መካከል ልዩነት ሳያደርጉ ሁሉንም ያሳድዱአቸው ጀመር።

ይህ የአሁኑ ሰዓት እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ ከከተማይቱ ጋር ይደረግ የነበረው ግንኙነት በመጠኑ የተሳካ ነበር። ከዋሻዎቹ በላይ በከተማይቱ ውስጥ የመኖር ዕድል ያጋጠማቸው ክርስቲያኖች በካታኮምቡ ውስጥ የሚኖሩትን የእምነት ወገኖቻቸውን ልዩ ልዩ ዕርዳታዎች በማድረግ ይዘክሩአቸው ነበር። በተነሣው ስደትና መከራ ምክንያት ከዚህ ቀደም ይረዱአቸው የነበሩት ክርስቲያኖች ቤታቸውንና ንብረታቸውን እየተው ወደ ካታኮምቡ ውስጥ መግባት ግድ ሆነባቸው። ለሌሎች ረድኤት የነበሩት ሁሉ ተመልሰው የሰውን እጅ የሚያዩ ሆኑ።

የሆነ ሆኖ የነበሩበት ሁኔታ ፈጽሞ ተስፋ የሚያስቈርጥ አልነበረም። ክርስቲያኖች በሮም ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ክርስቲያን ያልሆኑ ወዳጆችና የሥጋ ዘመዶች ነበሩአቸው። እነርሱም በተቻላቸው መጠን ክርስቲያኖችን ለመርዳት ይጣጣሩ ነበር። ማንኛውም ዓይነት ዐዲስ ነገር በሚፈጠርበት ጊዜ ሁኔታውን በገለልተኝነት ለመመልከት የሚወዱ ብዙ ሰዎች በሮም ይገኙ ነበር። እነርሱም ብዙ ክርስቲያን የሆኑ ወዳጆችና የሥጋ ዘመዶች ነበሩአቸው። በደረሰባቸውም ችግር ያዝኑላቸው ነበር። በበኩላቸው ከክርስቲያኖች ጋር ለመቈጠር ውሳኔ ባያደርጉም÷ ክርስቲያን ወዳጆቻቸውን ለመርዳት የተዘጋጁ ነበሩ። በአንድ ወገን ደግሞ ለጣዖታት የሚገባውን መሥዋዕት በማቅረብና በየመቅደሱ በመሳለም ለቀድሞው እምነት ያላቸውን ታማኝነት ያሳዩ ነበር። ክርስቲያኖችም ለዕለት ጉርሳቸው እነዚህን የመሳሰሉትን ሰዎች

እጅ ማየት ግድ ሆነባቸው፡፡

የሌሊቱን ጨለማ ተገን በማድረግ ወደ ከተማይቱ ያደርጉት የነበረው የስንቅ ፍለጋ ጉዞ ታላቅ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ ቀደም ብሎ ተገልጦአል። ይህን ተግባር ለመፈጸም÷ ልበ ቈራጥ የሆኑ ሰዎች ከክርስቲያኖች መካከል ምን ጊዜም ቢሆን ታጥተው ዐያውቁም ነበር።

ማርሴሉስም ይህን አደገኛ ተግባር በመፈጸም የእምነት ወገኖቹን ችግር ለማቃለል ያለውን ፈቃደኝነት ከመግለጥ አቋርጦ ዐያውቅም፡፡ በወታደርነቱ ዘመን ወደ ታላቅ የክብር ደረጃ ያደረሰው ቈራጠኝነትና ጀግንነት በመከራም ጊዜ ዋና መሣሪያ ሆነው፡፡ በየዕለቱ የሚገደሉት ክርስቲያኖች ቊጥር እጅግ የበዛ ነበር። እነዚህንም ከየቦታው እየፈለጉ አምጥቶ በካታኮምቡ ውስጥ በማዕርግ እንዲቀበሩ ማድረግ የክርስቲያኖች ተግባር ነበር። ይህንንም ተግባር መፈጸም አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የሰማዕታትን ሬሳ እንዲቀብሩ የተመደቡት ሠራተኞች ሥራው እንዲቃለልላቸው በማለት ክርስቲያኖች የዘመዶቻቸውን ሬሳ እየመጡ ሲወስዱ እንዳላዩ ሆነው ይመለከቱአቸው ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ከአፒያ አንቲካ ጎዳና አቅራቢያ ከሚኖሩት ክርስቲያኖች መካከል ሁለቱ ተይዘው መገደላቸው ተሰማ፡፡ ማርሴሉስም አንድ ሌላ ሰው አስከትሎ ሬሳቸውን ለማምጣት ቈረጠ። ወጣቱ ፖሊዮም በአንዳንድ ነገር ይረዳቸው ዘንድ አብሮአቸው ሄደ። ወደ ከተማው ቅጥር ሲደርሱ ፀሐይዋ ጠለቀች። ወዲያው ጨለማ ሸፈናቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጨረቃዋ ብቅ ብላ ለመንገዳቸው ብርሃንዋን አበረከተች፡፡

በጨለማው ውስጥ እያሳበሩ ወደ ኮሎሴዩም ደረሱ። ይህ ታላቅ የሕንፃ አደባባይ ቊጥር ስፍር የሌላቸው ክርስቲያኖች ያለቁበት መሆን ከዚህ ቀድሞ ተገልጦአል። የሕንፃውም ግርማና ሞገስ ካሠሩት የሮም ቄሣሮች ሥልጣን ታላቅነት ጋር የሚወዳደር ነበር። በብዙ የሚቈጠሩ ዘበኞች ከብረት ከተሠሩት መዝጊያዎች በስተጀርባ ቆመው በትጋት ይጠባበቃሉ። በየመግቢያው በር አጠገብ የጧፍ መብራት ይበራል።

ዘበኞቹ ማርሴሉስና ተከታዮቹ የመጡበትን ጉዳይ በመረዳት ወደ ውስጥ አስገብተው ወደ አደባባዩ እንዲከተሏቸው አዘዙአቸው። በአደባባዩም መካከል ለሮማውያን መደሰቻ የተጨፈጨፉት ክርስቲያኖች ሬሳ ተከምሮአል። የብዙዎቹ ሬሳዎች ሁኔታ የሚያሠቅቅ ከመሆኑም በላይ ሰውነታቸውን ለመለየት አስቸጋሪ ነበር። ከብዙ ድካም በኋላ የሚፈልጓቸውን ሰዎች አስከሬን አገኙ። ሬሶቹንም በጆንያ ውስጥ ከትተው ለመውሰድ ይዘጋጁ ጀመር፡፡

ማርሴሉስ ግራና ቀኝ እየተዘዋወረ የአደባባዩን ሁኔታ ተመለከተ። የግድግዳዎቹ ግርማ ሞገስ ያስፈራል። የመቀመጫዎቹ ቍጥር ብዛት ይህ ነው አይባልም። ያንን እንደ ውድቅት የጨለመውን ሕንፃ ሲመለከት እዚው ውስጥ ተውጦ የሚቀር መሰለው። በልቡም ውስጥ እንዲህ የሚል ዐሳብ ተቀረፀ።

‹‹በዚች ቦታ ላይ ስለ መድኅኔ ሕይወቱን የምሠዋበት ቀን መቼ ይደርስ ይሆን? ያ ቀን ሲመጣ በእምነቱ ጸንቼ እገኝ ይሆን? ጌታ ኢየሱስ ሆይ÷ በዚያ ቀን እንድጸና እርዳኝ።››

ጨፈቃዋ ብቅ ካለች ብዙ ጊዜ አላለፈም። ከዚህ የተነሣ አደባባዩ ገና ብርሃንዋን አላገኘም ነበር።

ፊላ የመፈለጉ ተግባር የተፈጸመው ከዘበኞቹ በተዋሱት የጧፍ መብራት ነበር። ማርሴሉስም በድንገት የአንድ ሰው ድምፅ ከተዘጉት ዋሻዎች ከአንዱ ውስጥ ሲያስተጋባ ሰማ። የሌሊቱ ጸጥታ የሰውዬውን ድምፅ ከልክ ያለፈ ግልጽ አድርጎት ነበር። ከሰውዬው አንደበት ይወጡ የነበሩት ቃላት የሚከተሉት ነበሩ።

‹‹አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል
መንግሥትም÷ የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ
ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት
የሚከሳቸው ወንድሞቻችን ከሳሽ ወድቆአልና
እነርሱም ከበጉ ደምና ከምስክራቸው
ቃል የተነሣ ድል ነሥተው ነፍሳቸውንም
እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።››

ማርሴሉስ ከጎደኞቹ አንዱን÷ ‹‹ያ ሰው ማን ይባላል?›› ሲል ጠየቀው።

ጓደኛውም እንዲህ አለው፡-

‹‹እባክህ ስለ እርሱ ብዙም አትጨነቅ። እርሱ ወንድማችን ሲና ነው። የደረሰበት ሐዘን ኅላውን አናውጦታል። መከራውና ስደቱ በተጀመረበት ጊዜ አንድ ልጁን ይዘው በእሳት አቃጥለው ገደሉት። ከዚያ ወዲህ በየሰፍራው ሁሉ እየተዘዋወረ የፍርድ ቃላትን በሮማውያን ላይ ከማውረድ አቋርጦ ዐያውቅም። ብዙ ጊዜ ዝም ብለው ያልፉት ነበር። አሁን ግን እንደምታየው ይዘውታል።››

‹‹እሥረኛ መሆኑ ነውን?››

‹‹አዎን!››

እንደ ገና አስፈሪ የሆነው የሲና ድምፅ ተሰማ፡፡

‹‹ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ÷

እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም?

ለደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ

እስከ መቼ አትበቀልም?››

‹‹ይህ ከዚህ ቀደም በካፒቶሊን ኮረብታ ላይ ያየሁት ሰውዬ ይሆን?››

‹‹ሳይሆን አይቀርም፡፡ እርሱ የማይደርስበት ስፍራ በከተማይቱ ውስጥ አይገኝም፡፡ እስከ ቤተ መንግሥቱ ድረስ እየሄደ ይህንኑ የፍርድ ቃል ይናገራል፡፡››

‹‹ከዚህ ስፍራ ቶሎ ብለን እንውጣ፡፡››

ጆንያቸውን በመተጋገዝ ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ወደ መውጫያው በር ፈጠኑ፡፡ በረኞቹ ጥቂት ጊዜ ካነጋገሩአቸው በኋላ እንዲወጡ ፈቀዱላቸው፡፡ ወደ ውጭ ወጣ እንዳሉ የሲና ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማ፡፡

‹‹ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፤ ወደቀች

የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች

የርኩሳን መናፍስት መጠጊያ

የርኩሳንና የተጠሉ ወፎች መጠለያ

ሕዝቦቼ ከእርሷ ተለዩ!››

ከኮሌሲዩም እስኪርቁ ድረስ አንዳች ቃል ሳይተነፍሱ ግስጋሴአቸውን ቀጠሉ፡፡

ማርሴሉስ÷ ‹‹እዚያ ውስጥ ይዘው የሚያስቀሩን መስሎኝ በጣም ፈርቼ ነበር፡፡››

ጓደኛውም÷ ‹‹ፍርሃትህ ምክንያት ያለው ነው፡፡ ከበረኞቹ አንዱ ግልፍ ቢልበት እዚያው ውስጥ አሥሮ ሊያስቀረን ይችላል፡፡ ይህን የመሰለውን ተግባር በምንፈጽበት ጊዜ ማንኛውም ዓይነት አደጋ ሊደርስብን እንደሚችል ማወቅ አለብን፡፡ በማንኛውም ሰዓት ለሞት የተዘጋጀን ሆነን መገኘት ይኖርብናል፡፡ ጌታችን ትጉ ሲል ያዘዘንን ቃል መዘንጋት የለብንም፡፡ ከዚህ ዓለም የመለያ ጊዜአችን ሲደርስ ዝግጁ ነኝ ለማለት እንድንበቃ ያስፈልጋል፡፡››

ማርሴሉስ፤ ‹‹ጌታችን በዓለም ሳለን ብዙ መከራ የሚያጋጥመን መሆኑን ገልጾልናል፡፡

‹‹ይህን ብቻ አስረድቶ አልተወነም። አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁ፤ እኔ ወዳለሁበት ስፍራ እናንተም ትመጣላችሁ የሚሉትን ቃላት ስናስብ ልባችን በደስታ ይሞላል። በእርሱ ረድኤት ሞትን ድል ለማድረግ እንችላለን። የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ለእኛ ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን ምንም እንዳይደለ ይሰማኛል።››

በእንደዚህ ያለ አኳኋን፥ ነዋሪ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል እየተጽናኑ መንገዳቸውን ቀጥለው በሰላም ካሰቡበት ሥፍራ ደረሱ። እንደ ደረሱም ስተደረገላቸው ጥበቃ አምላክን አመሰገኑ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ማርሴሉስ ብቻውን ስንቅ ፍለጋ ወደ አንድ የክርስቲያኖች ወዳጅ ወደ ሆነ ሰውዬ ቤት ሄደ። የሰውዬው መኖሪያ ከከተማይቱ ቅጥር ወጣ ብሎ አፒያ አንቲካ እተባለው ጎዳና አቅራቢያ ነበር። ይህ ሰውዬ ለክርስቲያኖች ብዙ ዕርዳታ ያደረገ ነበር።

ማርሴሉስም ለስንቅ የሚሆነውን ምግብ ካገኘ በኋላ ወሬ መጠየቅ ጀመረ።

ሰውዬው፥ ‹‹ወሬው እየከፋ ሄዶአል። ከመኰንኖች አንዱ ወደ ክርስትና እምነት በመመለሱ ቄሣር ከፉኛ ተቈጥቶአል።

ከዚህም የተነሣ በዚያ ክርስቲያን በሆነው መኰንን ስፍራ አንድ ሌላ ሰው ሹሞ ክርስቲያኖችን እያደነ እንዲይዝ ብርቱ የሆነ ትእዛዝ ሰጥቶአል ይባላል። በየዕለቱ ክርስቲያን የሆኑትን ሁሉ እያፈሱ ወደ ወህኒ ቤት ይከቱአቸዋል። ማንም ሰው ከቍጣቸው ሊያመልጥ አልቻለም።››

‹‹ክርስቲያኖችን እያደነ እንዲይዝ የተሾመው መኰንን ስም ማን እንደ ሆነ ታውቃለህ?››

‹‹አዎን፤ ሉኩሉስ ይባላል።››

‹‹ሉኩሉስ? እንዴት የሚያስደንቅ ነገር ነው። ከዚህ ቀደም ሉኩሉስ ብልህና ጠንካራ ሰው ነው ማለትን እሰማ ነበር።››

‹‹አዎን፥ እንዲህ ይባላል። የሆነ ሆኖ ወሬው ለክርስቲያኖች የሚበጅ አይደለም። ይህን ያመጣው የዚያ መኰንን ክርስቲያን መሆን ነው። ቄሣር በጣም ተቈጥቶአል። እርሱን ይዞ ላመጣለት ታላቅ ሽልማት ይሰጠዋል እየተባለ ይወራል። ድንገት ያጋጠመህ እንደ ሆነ ወሬውን እንድትነግረው አሳስብሃለሁ። ካታኮምብ ውስጥ ተደብቆአል ማለትን ሰምቻለሁ።››

‹‹አዎን፤ እዚያው ውስጥ ሳይሆን አይቀርም። ክርስቲያኖች ምን

ሌላ መሸሸጊያ ስፍራ አላቸው?››

‹‹ወሬው በጣም የሚያስፈራ ነው። በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ።››

‹‹ከአንድ ጊዜ የበለጠ ሊገድሉን አይችሉም።››

‹‹የእናንተ የክርስቲያኖች ድፍረትና ቈራጠኝነት ዘወትር ይደንቀኛል። እምነታችሁን በልባችሁ ውስጥ ይዛችሁ ለይምሰል ብቻ የቄሣርን አዋጅ ብታከብሩ ምን አለበት? ሞትን በገዛ እጃችሁ ለምን ትፈልጋላችሁ?››

‹‹መድኃኒታችን ለእኛ ሲል ሞቶአል። እኛም ለእርሱ ስንል ለመሞት ዝግጁዎች ነን። እርሱ ለወገኖቹ እንደ ሞተ እኛም ፍለጋውን በመከተል ለወንድሞቻችችን ስንል ለመሞት ቊርጠኞች ነን።››

‹‹እናንተ ክርስቲያኖች ልዩ የሆናችሁ ፍጥረቶች ናችሁ።››

ማርሴሉስ ተሰናብቶ ከሰውዬው ተለየ። የሰማው ወሬም አእምሮውን ያስጨንቀው ጀመር። ጕዞውንም እንዲህ እያለ ቀጠለ፦ በስፍራዬ የተተካው ለካስ ሉኩሉስ ነው! ምን ዓይነት ዐሳብ ይኖረው ይሆን? እንደ ክርስቲያን ብቻ ነው የሚመለከተኝ ወይስ እንደ ጓደኛው? ይህንን ነገር ለማረጋገጥ ብዙ ጊዜ አይወስድብኝም። በእጁ ላይ በወደቅሁ ቀን እንዴት እደነቅ ይሆን? መቼም ያለ እርሱ የሚይዘኝ የለም። እንደ ፈለገው ቢያደርግ መበሳጨት የለብኝም። ታዛዥ በመሆኑ በግዴታ የታዘዘውን መፈጸም አለበት። የወታደርነት ግዴታውን ከመፈጸም ሊያግደው አይችልም። እኔን ይዞ ላመጣ ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ ከታወጀ እኔን ለመያዝ የሚያደርገው ጥረት ከፍ ያለ መሆን አለበት። ጊዜው ተቃርቦአል፤ ተዘጋጅቼ መጠበቅ አለብኝ።

ይህንን በልቡ እያሰላሰለ በአፒያ አንቲካ ጎዳና በኩል ጕዞውን ቀጠለ። በዐሳቡ ተውጦ ወዲህና ወዲያ እያለ ሲገሰግስ ሳያስበው ሰዎች ተሰብስበው እቆሙበት ማዕዘን ደረሰ፤ ሰዎቹም ከበው አቆሙት።

ከእነርሱ መካከል አንዱ፦ ‹‹እንዲህ ቸኰል ቸኰል ማለት አያሻም። ለመሆኑ ማን ትባላለህ? ወዴትስ ነው የምትሄደው?›› አለው።

ማርሴሉስም በቍጣ ቃል ‹‹ከፊቴ ዘወር በል!›› ብሎ ሰውዬውን ገፋው። ሁኔታው ሁሉ ከዚህ ቀደም በሰዎች ላይ ሥልጣን የነበረው መሆኑን ይገልጽ ነበር።

የተሰበሰቡት ሰዎች ሥልጣናዊ ቃሉን በመስማት በጣም ደነገጡ። ወደ ኋላም ማፈግፈግ ጀመሩ። ያ መሪያቸው በመሆን ማርሴሉስን ያነጋገረው ሰውዬ እንደ ገና ‹‹ማን እንደ ሆንክ ካልነገርከን በዚህ በኩል

ማለፍ አትችልም!›› አለው፡፡

ማርሴሉስም፥ «ባክህ ከፊቴ ዘወር በል ብዬሃለሁ፡፡ እንዴት ዐታውቀኝም? እኔ ከቂሣር መኮንኖች አንዱ ነኝ» አለው፡፡

በዚህ ጊዜ ሁሉም ተደናገጡ፡፡ መንገድ ለቀቁለትና ማርሴሉስም ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ጥቂት እርምጃዎች እንደ ተራመደ ከመካከላቸው እንዲህ የሚል ድምፅ ተሰማ፡፡

‹‹ክርስቲያኑ ማርሴሉስ ነው! ያዙት! እንዳያመልጥ!›› ሁሉም በያሉበት ጩኸታቸውን አቀለጡት፡፡

ማርሴሉስም ጊዜ ሳያባክን የተሸከመውን ወዲያ ወርውሮ ወደ አንድ ዕጥፍ ወደምታደርግ መንገድ ሩጫውን ቀጠለ፡፡ ሰዎቹም ተከተሉት፡፡

ማርሴሉስም ነፍሴ አውጭኝ በማለት ግራና ቀኝ እያሰባበረ ቲቤር ወደ ተባለው ወንዝ አመራ፡፡ ሩጫውም አባራሪዎቹን ከፍ ባለ ርቀት አስቀራቸው፡፡ ወደ ወንዙ  እንደ ደረሰ ተወርውሮ ገብቶ ዋናውን ወደ ማዶ ቀጠለ፡፡ ተከታዮቹ ወንዙ ዳር ደረሱ፡፡ ከዚያ ለማለፍ ግን አልደፈሩም፡፡

## መያዝ

‹‹የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን ይሰጣችኋል፡፡››

ሖኖሪዮስ ሁለት ሦስት ከሚሆኑ ሰዎች ጋር ለጸሎት በሚሰበሰቡበት ክፍል ተቀምጦአል፡፡ አብረውት ከነበሩት ሰዎች አንዷ ሴሲሊያ ነበረች፡፡

በክፍሉ ውስጥ አንድ የሚፍ መብራት ጭል ጭል ይላል፡፡ የሰዎቹ አቀማመጥ በጣም ጸጥ ያለ ነው፡፡ ሐዘንና ሥጋት የሚያንሳቅሳቸው መሆኑ በግልጽ  ይታያል፡፡

ወዲህና ወዲያ የሚተረማመሱ ሰዎች እርምጃና የማጉረምረም ድምፅ ይሰማል፡፡ ድንገት በፍጥነት የሚራመድ የአንድ ሰው እርምጃ ወደ ነበሩበት ክፍል ሲፋጠን ተሰማ፡፡ ማርሴሉስ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ እፊታቸው ቆመ፡፡ ሁሉም ከተቀመጡባት በድንጋጤ ብድግ አሉ፡፡

ሴሲሊያ፤ ‹‹ጋሊዮ የት ነው?›› ስትል ጮኸች፡፡

ማርሴሉስም፤ ‹‹ዐላየሁትም›› ሲል መለሰላት፡፡

ሴሲሊያ የማርሴሉስን መልስ እንደ ሰማች፤ ‹‹ዐላየሁትም?››

ብላ ከመቀመጫዋ ላይ ዘፍ አለች፡፡

‹‹ምነው? ከወጣ ቆይቶአል እንዴ?››

‹‹ከስድስት ሰዓት በፊት መመለስ ነበረበት፤ አሁንማ ሥጋቱ ሊገድለኝ ነው፡፡››

‹‹ምንም አይሆንም፡፡ እርሱ እንደ ሆነ ራሱን ከአደጋ ለመጠበቅ ይችላል፡፡››

ማርሴሉስ ይህን በመሳሰሉ ቃላት የተሸበረውን ልብዋን ሊያረጋጋው ሞከረ፡፡

ሴሲሊያ ከመቀመጫዋ ላይ ብድግ ብላ÷ ‹‹እንዴት ምንም አይሆንም ትለኛለህ? በዙሪያችን የከበበንን አደጋ ደኅና አድርገን ዕናውቃለን፡፡ እንደ አሁኑ ጊዜ መውጫያ መግቢያ ጠፍቶብን ዐያውቅም›› አለችው፡፡

‹‹ከሆነስ ሆነና ማርሴሉስ፤ እስከዚህ ያዘገየህ ምንድን ነው? ተመልሰህ ትመጣለህ ብለን ፈጽሞ ተስፋ አላደረግንም ነበር፡፡››

‹‹ቪያ አልባ እተባለው መንገድ ስደርስ ጥቂት ሰዎች ሊይዙኝ ሞከሩ፡፡ እኔም ተሸክሜ የነበረውን ስንቅ ጥዬ ሸሽቴን ወደ ወንዙ አመራሁ÷ ሰዎቹም እያባረሩ ወንዝ ድረስ መጡ፡፡ እንደ ደረስኩ ወንዙ ውስጥ ዘልዬ ገብቼ በዋና ማዶ ለመሻገር ቻልኩ፡፡ ከዚያም መንገድ እያሰባበርኩ እንደምታዩኝ በሰላም እዚህ ለመድረስ ቻልኩ፡፡››

‹‹ስጥቂት ነው ያመለጥከው፡፡ ክፉኛ ይፈልጉሃል፡፡ አንተን ይዞ ያመጣ ይሸለማል እየተባለ ይወራል፡፡››

‹‹እናንተም ወሬውን ሰምታችኋል ማለት ነዋ?››

‹‹አዎን፤ ከዚህም የባሰ ብዙ ነገሮች ሰምተናል፡፡ ሁላችንንም ለመደምሰስ የሚደረገው ጥረት እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ በየጊዜው የሚደርስን ወሬ የሚያስፈራና ተስፋ የሚያስቈጥ ነው፡፡ ከተመዘዘው የአደጋ ሰይፍ ሊያድን በሚችለው በአምላካችን በበለጠ መታመን አለብን፡፡››

ማርሴሉስም ተስፋ በተሞላበት መንፈስ÷ ‹‹መውጫያ መግቢያችንን እንዳያገኙ እናደርጋለን›› አለ፡፡

ሖኖሪዮስ ግን÷ ‹‹መውጪያ መግቢያችን የሆኑትን ታላላቅ በሮች ይዘዋቸዋል ይባላል›› ሲል መለሰለት፡፡

‹‹ዐዲስ መውጫ እናበጃለን፡፡ ለዚያውስ ስንቱን በር ጠብቀው ይችላሉ፡፡››

‹‹የምእመናንን መሪዎችና ሽማግሌዎች ይዞ ላመጣልን ሽልማት እንሰጣለን ብለዋል፡፡››

‹‹በእነርሱ ላይ አደጋ እንዳይደርስባቸው ደኅና አድርገን መጠበቅ ይኖርብናል ማለት ነዋ!››

‹‹ስንቃችንም እያለቀ መሄድ ጀምሮአል። ከውጭ እናገኘው የነበረው ዕርዳታ በጣም ተቀንሶአል።››

‹‹ይህ ሁሉ እንዲያሸብረን አያስፈልግም። እንደ ቀድሞው ሊረዱን የተዘጋጁ ብዙ ሰዎች አሉ። እኛም በድፍረት እንደ ቀደሞው ስንቅ ማቅረብን ማቋረጥ የለብንም። በካታኮምቡ ውስጥ እስካለን ድረስ በምግብ በኩል ምንም ዓይነት ችግር በወንድሞቻችንና በእኅቶቻችን ላይ ሊደርስባቸው አይችልም። ይህንኑ የዕርዳታ ተግባራችንን በቈራጥነት በመፈጸም ላይ ሳለን ተይዘን ብንገደል የሰማዕትነት አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል።››

‹‹አዎን÷ ማርሴሉስ አሁን የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። እዚህ ውስጥ እስካለን ድረስ ሞትን መፍራት የለብንም። የእምነትህ ጽናት በሐፍረት ላይ ጥሎኛል። ለመሆኑ ሞት ምንድን ነው? ጥቂት ጊዜ ካሠቃየ በኋላ ለዘላለም የሚያልፍ ነገር አይደለምን? በዛሬው ቀን የሰማነው ወሬ ልባችንን ከልክ ያለፈ አስጨንቆታል። በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምእመናን ተበትነዋል። ብዙ ማኅበራነ ምእመናን በዚች ከተማ ውስጥ ተቋቁመው ምስጋናቸውና ጸሎታቸው ወደ አርያም ያስተጋባ ነበር። አሁን ግን ሁሉም ፈርሰዋል። ምእመናንም ከምድር ገጽ እንዲጠፉ ተደርገዋል።››

ሖኖሪዮስም በሐዘን የተሸነፈ ፊቱን ወደ ምድር አቀርቅሮ ዝም አለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በእንጉርጉሮ ድምፅ ለማንያኛውን መዝሙር መድገም ጀመረ።

‹‹አቤቱ የሠራዊት አምላክ እስከ መቼ ድረስ
በወገኖችህ ጸሎት ላይ ቍጣህ ይጤሳል።
የእንባ እንጀራ መገብካቸው፤ እንባቸውንም በስፍር አጠጣሃቸው።
ለጎረቤቶቻችን ክርክር አደረግኸን፤ ጠላቶቻችንም ተሳለቁብን።
አቤቱ የሠራዊት አምላክ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ እንድንማለን።››

ማርሴሉስ ይህንን ከሰማ በኋላ ሖኖሪዮስን እንዲህ አለው:-

‹‹ሖኖሪዮስ ሆይ÷ አትዘን፤ መከራችን ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ መሄዱ የታወቀ ነው። ሆኖም በእርሱ በወደደን ከአሸናፊዎች በላይ ለመሆን እንችላለን። እርሱ ራሱ በቃሉ ምን ይለናል። ‹‹ድል ለነሣው

በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ። ድል የነሣ በሁለተኛው ሞት አይጎዳም። ድል ለነሣው ከተሠወረ መና እሰጠዋለሁ። ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፤ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ ዐዲስ ስም ተጽፎአል። ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻ ቃሌን ለጠበቀው በሕዝብ ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ። የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ። ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጎናጸፋል፤ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም። በአባቴና በመላእክት ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ። ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፤ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም። የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን ዐዲሲቱን ኢየሩሳሌምን ዐዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ። እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ እንደ ተቀመጥሁ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋን ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።››

ማርሴሉስም እነዚህን ቃላት ሲናገር ፊቱ በተስፋ ብርሃን ማንጸባረቅ፥ ስሜቱ በድፍረት መጋጋል ጀመረ። የሰሙት ሁሉ ልባቸውን አክብዶትና አስጨንቆት የነበረውን መከራ በመዘንጋት ልባቸው በደስታና በዘላለማዊው ተስፋ ተሞላ። ለዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም በወርቅ ከተሠሩት መንገዶችዋ ከሚያማምሩት የዘንባባ ዛፎችዋ ጋር የበገና መዝሙርና በዙፋን ላይ የተቀመጠው ንጉሥ ብሩህ ገጽ በሥጋት የተቆራመደውን ዐሳባቸውን መሳው።

ሖሮሪዮስም ማርሴሉስን እንዲህ አለው፡-

‹‹የተናገርካቸው ቃላት ከጭንቀቴ ገላግለውኛል። ከእንግዲህ ወዲህ ለምድራዊው መከራ መሸበር የለብንም። ትላንትና የእምነት ወንድማችን የሆነው የማርሴሉስ ጽናት ሁላችንንም በሐፍረት ላይ የጣለን መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ዐሳባችን ሁሉ ወደ ፊት በሚጠብቀን ደስታ ላይ እንዲያርፍ ያስፈልጋል። የዚህ የምድራዊው ቤታችን ድንኳን ቢፈርስ እጅ ያልሠራው ሰማያዊ ቤት እንዳለን ናውቃለንና። ጠላቶቻችን እየተቃረቡ መጥተዋል። ሕይወታችንን መሥዋዕት የምናደርግበት ጊዜ ደርሷል። መሞታችን ካልቀረ እንደ ክርስቲያን ለመሞት እንዘጋጅ።››

ማርሴሉስም፥ ‹‹ይህ ሁሉ ጭንቀት ምንድነው? ከቀድሞው የባሰ ሞትን የምንፈራበት ምክንያቱ ምንድን ነው? በካታኮምቡ ውስጥ እስካለን ድረስ ምን ሊያደርስብን ይችላል?›› ሲል ጠየቀ።

‹‹አዬ ማርሴሉስ÷ እንዲያው የሆነውን ባትሰማ ይሆናል።››
‹‹ምን የሆነ ነገር አለ?››
‹‹ክሪሲፐስ መሞቱን አልሰማህም?››
‹‹ክሪሲፐስ! ሞተ? አይደረግም! መቼ? እንዴት ተደርጎ?››



‹‹የቄሣር ወታደሮች በአንድ መንገድ ዐዋቂ እየተመሩ ፍለጋቸውን ክርስቲያኖች ወደሚኖሩበት ስፍራ አመሩ።››

‹‹የቄሣር ወታደሮች በአንድ መንገድ ዐዋቂ እየተመሩ ካታኮምቡ ውስጥ ገብተው ፍለጋቸውን ጸሎት ወደሚደረግበት ዋሻ አደረጉ። መምጣታቸው እንደ ተሰማ ምእመናኑ በያለበት ተሰራጩ፡ ክሪሲፐስ ግን በእርጅና ምክንያት ይሁን ወይም ሰማዕትነት በመፈለጉ ካለሁበት ስፍራ አልንቃነቅም ብሎ እምቢ አለ። ወታደሮቹ ከስፍራው ሲደርሱ ክሪሲፑስም ከሁለት ጠባቂዎች ጋር ለጸሎት ተንበርክኮ አገኙት። ወዲያውም ራሱን ፈጥፍጠው ገደሉት። ሁለቱም ጠባቂዎቹ አብረውት ዐረፉ።››

ማርሴሉስም÷ ‹‹ከሰማዕታት ሠራዊት ጋር ለመቀላቀል እስከ ሞት ድረስ የታመኑ ሆነዋል። የሕይወትንም አክሊል ይቀበላሉ›› አለ።

ድንገት ከውጭ የሰዎች ውካታ ተሰማ። ሁሉም ከተቀመጡበት በድንጋጤ ተነሱ። ሳያስቡት ሁሉም÷ ‹‹ወታደሮች ናቸው!›› ሲሉ ጮኹ።

ዳሩ ግን ከውጭ የተሰማው ድምፅ የወታደሮች አልነበረም።

ከላይኛው ንሬ ~ጠተ ከከተማ መልእክት ይዞ አንድ ክርስቲያን መጥቶ ነበር። መልእክተኛውም እየተንቀጠቀጠና ቁና ቁና እየተነፈሰ ወለሉ ላይ ዘፍ ብሎ እጆቹን እያማታ ‹‹ጠፋን! ጠፋን!›› አለ።

የዚህም ሰው አኳኋን ሴሲሊያን በጣም አስደነገጣት። እየተንቀጠቀጠች ግድግዳውን ተጠጋች። እጆዋን ጭብጥ አድርጋ፤ ዓይኖችዋን አፍጣ ለመናገር በመሞከር ከንፈሮችዋ ይንቀጠቀጡ ጀመር። ዳሩ ግን አንዲት ቃል እንኳ መተንፈስ አቃታት።

ሖኖሪዮስ ‹‹ተናገር! ተናገር! ምንድን ነው ነገሩ? ንገረን!›› አለ።

ሰውዬውም ‹‹ፖሊዮ›› አለ።

ማርሴሉስም በቊጣ ቃል፤ ‹‹ፖሊዮ ምን ሆነ?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹ተይዞአል፤ ታሥሮአል!››

በዚህ ጊዜ ጆሮ የሚያደነቁር ጩኸት ተሰማ። ጯሂዋ ሴሲሊያ ነበረች። ወዲያውኑ ወለሉ ላይ ድፍት አለች። በዚያ ቁመው የነበሩትም አንሥተው ወደ ክፍሏ ወስደው መድኃኒት ቢጤ አደረጉላት። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነፍስ ዘራች። ዳሩ ግን ከድንጋጤውና ከመውደቅዋ የተነሣ አእምሮዋ በመናወጡ ብዙ ጊዜ በቅዠት ውስጥ ቆየች። መልእክተኛውም የዐሳቡን ማርጊያ ጊዜ በማግኘቱ ሁኔታውን በሚገባ ለማስረዳት ቻለ።

ማርሴሉስም÷ ‹‹ፖሊዮ ከአንተ ጋር ነበር?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹አይደለም ብቻውን ነበር።››

‹‹ምን ሊያደርግ ሄደ?››

‹‹ወሬ ለመጠየቅ። እርሱ ራት ብሎ እፊት እፊቴ ይሄድ ነበር። አመጣጣችን ከከተማው ወደዚሁ ነበር። በመንገዳችን ላይ ሰዎች ወደ ተሰበሰቡበት ስፍራ ደረስን። ሰዎቹም ሳይታሰብ ፖሊዮን አቁመው ይመረምሩት ጀመር። ይጠይቁት የነበረው ነገር ምን እንደ ሆነ አልሰማሁም። ዳሩ ግን እጃቸውን እያወራጩ ያስፈራሩት ነበር። በመጨረሻም ይዘው ሲወስዱት ዐየሁ። እኔም ምንም ለማድረግ አልቻልኩም። በሩቅ ቆሜ ሁኔታውን ስመለከት እኩል ሰዓት አለፈ። ወዲያው የቄሣር መኰንኖች ደረሱና ፖሊዮ ለእነርሱ ተሰጠ። እነርሱም ይዘውት ሄዱ።››

ማርሴሉስም÷ ‹‹የመኰንኖቹ መሪ ማን እንደ ነበር ተመልክተሃል?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹አዎን÷ ሉኩሉስ ነበር።››

ማርሴሉስም÷ ‹‹እርሱ ነበር?›› ካለ በኋላ እቅመበት ስፍራ ሆኖ ከዐሳቡ ጋር ይሟገት ጀመር።

# መሥዋዕትነት

‹‹ነፍስን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡››

ስፍራው የቄሣር መኰንኖች ሰፈር ነው፡፡ ቀኑ መሽቶአል፡፡ ሉኩሉስ ክፍሉ ውስጥ ቦግ ያለ መብራቱን አብርቶ ተቀምጦአል፡፡ ድንገት በሩ ተንኳኳ፡፡ ሉኩሉስም ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በሩን ከፈተ፡፡ አንድ ሰው ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ከሉኩሉስ ፊት ቆመ፡፡

ሉኩሉስም ከፍ ባለ ድምፅ ‹‹ማርሴሉስ!›› ሲል ጮኸና የሚወደውን ጓደኛውን በማየቱ በመደሰቱ እቅፍ አደረገው፡፡

‹‹ውድ ጓዴ ሆይ፥ እንደ ገና ለመገናኘት በመቻላችን ለደስታዬ ወሰን የለውም፡፡ እዚህ ቁጭ ብዬ ስለ አንተ ዐስብ ነበር፡፡ በሕይወት ለመገናኘት ዕድል ያጋጥመን ይሆን? የሚለውን ዐሳብ ሳወጣ ሳወርድ ከተፍ አልክ፡፡››

ማርሴሉስም ለጓደኛው እንዲህ ሲል መለሰለት፡-

‹‹ውድ ወዳጄ ሆይ፥ ወደ ፊት ብዙ ጊዜ ለመተያየት የምንችል አይመስለኝም፡፡ ዛሬም የመጣሁት ሕይወቴ በአደጋ ላይ ትወድቅ ይሆን? እያልኩ ስፈራ ስቸር ነው፡፡››

‹‹እውነት ነው ማርሴሉስ፤ በጥብቅ እንድትፈለግ ተደርጓል፡፡ ይዞ ለቄሣር ያቀረበህ ታላቅ ሽልማት እንደሚያገኝ ታውጆአል፡፡ በእኔ በኩል አንዳችም ዓይነት ችግር ሊደርስብህ እንደማይችል የምታውቅ መሆንህን አልጠራጠርም፡፡ ጓደኝነታችን ያው እንደ ጥንቱ ነው፡፡ ይህ የያዝህ ዕብደት ቢለቅህ አሁንም እንደ ድሮአችን በደስታ አብረን ለመኖር እንችላለን፡፡ እባክህ ማርሴሉስ...››

‹‹እባክህ ሉኩሉስ አታስቸግረኝ፡፡ እኔ እንደ ሆንኩ ዐሳቤን ልለውጥ ፈጽሞ አልችልም፡፡ ለአንተ ሁኔታዬ የሚያሳዝን መስሎ ይታይህ ይሆናል፡፡ እውነቱን ልንገርህ፤ በሕይወቴ የአሁኑን ያህል ተደስቼ ዐላውቅም፡፡››

‹‹ጉድ አትፈራም! ተደስቼአለሁ ትላለህ?››

‹‹አዎን፥ ሉኩሉስ፤ የአሁኑ ደስታዬ በቃላት ሊገለጥ አይችልም፡፡ እርግጥ ነው ብዙ መከራ ይደርስብኛል፡፡ ዳሩ ግን አልጨነቅም፤

እሰደዳለሁ እንጂ ተስፋ አልቈርጥም፡፡››

‹‹ቄሣር በክርስቲያኖች ላይ እንዲደርስ የሚያውጀው ስደትና መከራ ቀላል እንዳይመስልህ፡፡››

‹‹ደኅና አድርጌ ዐውቃለሁ፡፡ በየዕለቱ ብዙ የእምነት ወገኖቼ ሲገደሉ የማየው ነው፡፡ የከበበን የአደጋ ቀለበት በየዕለቱ እየጠበበ መሄዱ ይሰማኛል፡፡ ብዙ ጓደኞቼ ከሄዱበት ስፍራ ሬሳቸው ሲመለስ አዘውትሬ ተመልክቼአለሁ፡፡››

‹‹ይህን ሁሉ እያየህ ነው ደስተኛ ነኝ የምትለው?››

‹‹አዎን÷ ሉኩሉስ፤ ልቤ ዓለም ሊረዳው በማይችል ሰላም ተመልቶአል፡፡ ይህም ሰላም ሰማያዊና ከማስተዋል ሁሉ በላይ የሆነ ነው፡፡››

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ ለሞት የማትበገር መሆንህን ዐውቃለሁ፡፡ የሆነ ሆኖ ይህን ያህል መከራ እስከ አሁን ትታገሣለህ ብዬ ዐላሰብኩም ነበር፡፡ ቈራጥነትህ ከሰው አቅም በላይ ሆኖ ይታየኛል፡፡ ምናልባትም ከዕብደት የሚገኝ ድፍረትና ቈራጠኝነት ሳይሆን አይቀርም፡፡››

‹‹ተሳሳትክ ሉኩሉስ፤ ይህ የምታይብኝ ጽናት ከላይ የተሰጠኝ ነው፡፡ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓለም ብልጽግና ሁሉ ይበልጥብኛል፡፡ ከዚህ ቀደም ይህን ምሥጢር ለመረዳት አልቻልኩም ነበር፡፡ አሁን ግን አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉ ታድሶአል፡፡ በተሰጠኝ በዐዲሱ ኃይል አማካይነት ማንኛውንም ዓይነት መከራ መታገሥ እችላለሁ፡፡ በዙሪያዬ አስፍስፎ የሚጠብቀኝ መከራ አሠቃቂ ቢሆንም እንኳ የእምነቴን መሠረት ሊያናጋው አይችልም፡፡››

በዚህ ጊዜ ሉኩሉስ በሐዘን ድምፅ እንዲህ አለ፡-

‹‹የዐሳብህ ጽናት በጣም አድርጎ ያሳዝነኛል፡፡ አንድ የማመንታት ምልክት እንኳ ባይብህ ኖሮ ጊዜ ይመልሰዋል የሚል ተስፋ ያድርብኝ ነበር፡፡ ሁኔታህ ሁሉ የሞኝ እምነት ከጅማት ይጠነክራል የሚለውን ተረት ያሳሰበኛል፡፡››

ማርሴሉስም÷ ‹‹እስከ መጨረሻው ድረስ በእምነቴ ጸንቼ እንድገኝ እግዚአብሔር ብቻ ይርዳኝ!›› ሲል የልቡን ቍርጠኛ ፍላጎት ለወዳጁ ገለጸ፡፡ ቀጥሎም በሚከተሉት ቃላት የመጣበትን ጕዳይ ለሉኩሉስ አስታወቀ፡፡

‹‹ዛሬ እዚህ እስከ መምጣት ያደረሰኝ የራሴ ጉዳይ አይደለም:: የመጣሁት ዕርዳታህን ፈልጌ ነው:: ከዚህ ቀደም ማንኛውም ዓይነት ችግር ሲገጥምህ ዕርዳታዬን ለመጠየቅ ትችላለህ ብለኸኛል። የመጣሁት ያንን ተስፋህን መሠረት በማድረግ ነው::››

‹‹ከሥልጣኔ ሥር ያለውን ማንኛውንም ነገር ላደርግልህ የተዘጋጀሁ ነኝ፡፡ የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ::››

‹‹አንድ እሥረኛ አንተ ዘንድ አለ::››

‹‹አዎን÷ ካልክስ ስሞኑን ብዙ ክርስቲያኖችን ይዘናል::››

‹‹እኔ ያሰብኩት በተለይ ስለ አንድ ልጅ ነው::››

‹‹ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ልጅ መያዙን ሰምቻለሁ::››

‹‹ምንም እንኳ ቄሣር ክርስቲያኖች እንዲታደኑ ቢያዝም ይህን የመሰለው ሕፃን መያዝ አልነበረበትም። አሁንም ያለው በእጅህ ውስጥ ስለ ሆነ እንዲለቀቅ እለምንሃለሁ::››

‹‹እንዴት አድርጌ ማርሴሉስ! የሮምን ሥነ ሥርዓትና መሐላ ዘነጋኸው መሰለኝ፡፡ ይህንን የምትጠይቀኝ ነገር ባደርግ እንደ ከሐዲ የሚያስቈጥረኝ መሆኑን ዐታውቅም? ይህንን ከምትለምነኝ በገዛ ሰይፍህ ራስህን ግደል ብትለኝ ይሻላል::››

የወታደርነትን መሐላና ሥነ ሥርዓት አልዘነጋሁም። ዳሩ ግን ይህ ልጅ ገና ሕፃን በመሆኑ እንደ እሥረኛ ሊቈጠር አይገባውም:: የቄሣር ትእዛዝ ሕፃናትንም ይመለከታል?››

‹‹ትእዛዙ ምንም ዓይነት የዕድሜ ልዩነት አያደርግም። ከተያዘው ልጅ በዕድሜ ያነሱ ሕፃናት በኮሊሲዩም ውስጥ ሲገደሉ በዓይንህ ያየኸው አይደለም?››

ማርሴሉስም÷ ‹‹አዎን ዐይቻለሁ›› ሲል ከመለሰለት በኋላ ዐሳቡ ወደ እነዚያ የደስታ መዝሙር እየዘመሩ ሕይወታቸውን መሥዋዕት ወዳደረጉት ልጃገረዶች ነጎደ::

‹‹ይህም ወጣት የመከራን ጽዋ ሊቀምስ ነዋ?››

‹‹እምነቱን ካልተወ አይቀርለትም::››

‹‹ከእምነቱስ ዝንፍ እንደማይል ዐውቃለሁ::››

‹‹ራሱን ይጎዳል። የሆነ ሆኖ ማርሴሉስ! ይህን ሁሉ የሚያደርገው ሕጉ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ እባክህ እኔን አትውቀሰኝ::››

‹‹ምንም ለልወቀበህም፡፡ ታዛዥና ቅን አገልጋይ መሆንህን ዐውቃለሁ፡፡ እዚህ እስካለህ ድረስ ግዴታህን መፈጸም አለብህ፡፡ አንድ ነገር ልጠይቅህ፡፡ እሥረኛ መልቀቅ ከሕግ ውጭ ነው ብለኸኛል፡፡ አንድ እሥረኛ ለቆ በስፍራው ለመግባት የሚፈልገውን ሰው ማሠር ይቻላል;

‹‹አዎን፡፡››

‹‹ከዚህ ልጅ ይልቅ በጣም ተፈላጊ የሆነ እሥረኛ ባቀርብልህ ትለቀዋለህ?››

‹‹ከእኛ ሰዎች ውስጥ ያሠራችኋቸው አሉ?››

‹‹የሉም፡፡ ከእኛው መካከል በጥብቅ የሚፈለጉ መኖራቸውን ታውቃለህ፡፡ የብዞዎቻቸውመም ሕይወት ከፍ ባለ ሽልማት ተገምቶአል፡፡ የእነዚህ ሰዎች መያዝ በመቶ የሚቈጠሩ ሕፃናት ሊያስለቅቅ ይችላል፡፡››

ሉኩሉስም በመደነቅ÷ ‹‹በክርስቲያኖች መካከል አንዱ ሌላውን አሳልፎ ይሰጣል?›› ሲል ጥያቄውን አቀረበ፡፡

‹‹ከእኛ ውስጥ አንዱ ሌላው አሳልፎ የሚሰጥ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን፤ ክርስቲያን የሆነ የወንድሙን ሕይወት ለማዳን ራሱን አሳልፎ ይሰጣል፡፡››

‹‹በፍጹም የማይመስል ነገር ነው!››

‹‹የተቈረጠ ዐሳብ ነው!››

‹‹ለመሆኑ ለዚህ ልጅ ቤዛ እንዲሆን የተመደበው ማን ነው?››

‹‹እኔ ማርሴሉስ!››

በዚህ ጊዜ ሉኩሉስ ጥቂት እርምጃዎች ወደ ኋላው አፈገፈገና ‹‹አንተ!?›› ሲል ጮኸ፡፡

‹‹አዎን እኔ ራሴ!››

‹‹ትቀልዳለህ መሰለኝ፡፡ የማይመስል ነገር ለምን ታወራለህ፡፡››

‹‹የምነግርህ ሁሉ የምሬን ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ሕይወቴን ለአደጋ አጋልጬ አንተ ዘንድ ለመምጣት ባልሞከርኩም ነበር፡፡ ለዚህ ልጅ መለቀቅ የተቻለኝን ለማድረግ ቆርጬ ተነሥቻለሁ፡፡ ከዚህም ሌላ ላስረዳህ የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ ፖሊዮ የጥንቶቹ የሮም መኳንንቶች ወገን ነው፡፡ እናቱም ያለ እርሱ ሌላ ልጅ የላትም፡፡ አባቱ የሞተው በጦርነት ላይ ነው ወገኖቹም ሰርቢሊዎች ናቸው፡፡››

‹‹ሰርቢሊዎች! የሴሊሊያ ልጅ መሆኑ ነዋ!››

‹‹አዎን፡፡››

‹‹እርስዋም ለጊዜው የምትገኘው በካታኮምቡ ውስጥ ነው፡፡ ለዚህ ልጅ ያላት ፍቅር ይህ ነው አይባልም፡፡ በየዕለቱ ወደ ከተማ ይላካል፡፡ እስኪመለስ ድረስ ያለባት ጭንቀትና ሥጋት ከፍ ያለ ነው፡፡ ወደ ከተማም እንዲላላክ የምትፈቅደው ካታኮምቡ ውስጥ መጥፎ አየር ወጣት ሕይወቱን እንዳይቀጨጨው በመፍራት ነው፡፡ በካታኮምቡ ውስጥ ተዘግቶ በመኖር በጤና ላይ የሚደርሰው አደጋ ከፍ ያለ መሆኑን በመረዳት በየጊዜው ከከተማይቱ ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ትፈቅድለታለች፡፡ ይህ ልጅ ከሥልጣንህ ሥር ታሥሮ ይገኛል፡፡ እናቱም የልጅዋን መያዝና መታሰር በሰማች ጊዜ የተሰማት ድንጋጤ በሞትና በሕይወት መካከል ጥሏታል፡፡ የዚህ ልጅ ሕይወት በአደጋ ላይ የወደቀ እንደሆነ የእናቱ መሞት የተረጋገጠ ነው፡፡ የእነርሱም መሞት የሮም ቅሬታ የሆኑትን የመኳንንት ዘሮች ከመካከላችን ማጥፋት ነው፤ ራሴንመም በዚህ ልጅ ፈንታ ለመስጠት ቁርጤ የመጣሁት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የእኔ ሕይወት ምንም አይደለችም፡፡ በዓለም ላይ እስከ አሁን የነበርኩት ብቻዬን ነው፡፡ ሞቴ ማንንም አይጐዳም፡፡ የማንንም ልብ ጭንቀት ላይ አይጥልም፡፡ የምጠረውም ሆነ የምደግፈው የለኝም፡፡ የማይቀረውን ሞት መፍራት አይገባኝም፡፡ አንድ ቀን መሞቴ ስለማይቀር ሕይወቴን ለወዳጄ ቤዛ ለማድረግ ወስኜአለሁ፡፡ ሉኩሉስ ሆይ፤ አንተ ዘንድ ያመጣኝን ምክንያት በሚገባ ዘርዝሬልሃለሁ፡፡ አሁንም በጓደኝነታችንና በሰጠኸኝ የተስፋ ቃል ስትል ልጁን ለቀኸው በምትኩ እኔ እንድታሠር እለምንሃለሁ፡፡››

ሉኩሉስም ከመቀመጫው ተነሥቶ ክፍሉ ውስጥ ወዲህ ወዲያ ይንጎራደድ ጀመር፡፡

በመጨረሻም፤ ‹‹ምነው ማርሴለስ? ለምን እንዲህ አድርገህ ትፈትነኛለህ? ሲል ተናገረ››

‹‹ዐሳቤን መቀበል በጣም ቀላል ነገር ነው፡፡››

‹‹የአንተ ሕይወት ከማንኛውም ነገር የሚበልጥብኝ መሆኑን ዘነጋኸው?››

‹‹የወጣቱን ልጅ ሁኔታ ተመልከት፡፡››

‹‹የልጁ ሁኔታ የሚያሳዝን መሆኑን አልክድም፡፡›› የሆነ ሆኖ

የአንተ ሕይወት በእርሱ ፊንታ እንዲጠፋ እንዴት አድርጌ የምፈቅድ ይመስልሃል?››

‹‹ሕይወቴ አንድ ጊዜ ተቈርጦባታል፡፡ መሞቴ የማይቀር ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ሕይወቴን በፈቃዶ ለዚሁ ልጅ አገልግሎት እንዳውለው ፍቀድልኝ፡፡››

‹‹ሕይወቴ እስካለ ድረስ ዓይኔ እያየ አትሞትም፡፡ ሕይወቴ ተቈርጦባታል የምትለውንም አልቀበልም፡፡ እንደ ቀሩት ክርስቲያኖች በአደባባይ በሕዝብ ፊት የሕይወትህ ፍጻሜ ይሆናል ብዬ ከቶ አላምንም፡፡››

‹‹አንድ ጊዜ ከተያዝኩ ሊያድነኝ የሚችል የለም፡፡ የተቻለህን ያህል ልታድነኝ የምትሞክር መሆንህን አልጠራጠርም፡፡ ዳሩ ግን የሚሳካልህ አይመስለኝም፡፡ ከቄሣር ቍጣ ከቶ ማን ሊያድነኝ ይችላል?››

‹‹በተቻለኝ መጠን ከአደጋ እንድትርቅ እታገላለሁ፡፡ የሚሆነውን ነገር ምን ታውቃለህ? የሆነ ሆኖ የአሁኑን ልመናህን ፈጽሞ ልሰማው አልፈልግም፡፡››

‹‹በቀጥታ ቄሣር ፊት ቀርቤ ለአንተ የነገርኩህን እንዲያደርግልኝ እለምነዋለሁ፤ እንደሚፈቅድልኝም አምናለሁ፡፡››

‹‹አንተንም እሣሥሮ ሁለታችሁንም እንድትነዱ እንደሚያደርግ አትጠራጠር፡፡››

‹‹ፍላጎቴ በመልእክተኛ በኩል እንዲቀርብለት አደርጋለሁ፡፡››

‹‹እርሱም አያዋጣህም፡፡ መልእክተኛውን ቄሣር ፊት እንዲቀርብ ማን ይፈቅድለታል?››

ማርሴሉስ ተስፋ በመቍረጥ፥ ‹‹ምንም ተስፋ የለም ማለት ነዋ?›› አለ፡፡

‹‹ምንም ለማድረግ የሚቻል አይመስለኝም፡፡››

‹‹ልመናዬን ሁሉ እምቢ ማለትህ ነው?››

‹‹ማርሴሉስ ሆይ፥ ዓይኔ እያየ ጓደኛዬን እንዴት አድርጌ ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ? ይህን የማይመስል ልመናህን ለመቀበል ባለመቻሌ ይቅርታ እንድታደርግልኝ ከልብ እለምንሃለሁ፡፡››

ማርሴሉስም ዕቅዱ እንዳልተሳካለት በመረዳት÷ «የጌታ ፈቃድ ይፈጸም። የልፋቱ ውጤት ይህ ከሆነ ቶሎ ብዬ ወደ መጣሁበት ልመለስ። ይህን ተስፋ አስቆራጭ መልእክት እንዴት አድርጌ ይዤ እንደምመለስ ዐላውቅም» አለ።

ሁለቱ ጓደኞች ለጥቂት ጊዜ አንዳች ቃል ሳይተነፍሱ ተቃቅፈው ከቆሙ በኋላ ማርሴሉስ ወደ መጣበት ለመመለስ ፈጠነ። ሉኩሉስም ጓደኛው ከሄደ በኋላ በሰማው ሁሉ በመደነቅ ጊዜውን በትካዜ አሳለፈ።

ማርሴሉስ በደኅና ወደ ካታኮምቡ ተመለሰ። ይዞ የሚመጣውን ወሬ በሥጋት ይጠባበቁ የነበሩት ሁሉ በመምጣቱ ተደሰቱ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ሴሲሊያ በሚገባ ነፍስ አልዘራችም ነበር። በዙሪያዋ የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ የምታስተውለው በከፊል ነበር። በቅዠትዋም የመልካሙን ዘመን ሕይወትዋን እያወሳች ታወራ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በካታኮምቡ ውስጥ ባሳለፈችው ጊዜ የደረሰባት የተስፋና የፍርሃት÷ የደስታና የሐዘን መፈራረቅ እንዲሁም ዘወትር የማይለየው ሥጋትና የቦታው ጤና ጎጂ የሆነው አየር ሰውነትዋንና አእምሮዋን ክጉዳት ላይ የጣለው መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር። በቅምጥል የኖረው የእመቤትነት ሰውነትዋና ቅስሟ በልጅዋ የመታሠር ወሬ እየደቀቀ ሄደ።

የዚህ ዕለት ማታ ወዳጆችዋ የሆኑ ሁሉ በአልጋዋ ዙሪያ ሁነው ሁኔታዋን ይጠባበቁ ጀመር። ከሰዓት ወደ ሰዓት እየደከመች ሄደች። የመሞትዋ ጊዜ የተቃረበ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ግልጽ ሆነ። ሁኔታዋን የልጅዋ መመለስ እንኳ ሊያሽለው አይችልም ነበር። የሕይወትዋ መጨረሻ እየተቃረበ በመሄዱ ለረጅም ጊዜ ጸጥ አለች፤ መናገርም ተሳናት።

ዓይኖችዋ መንቀጥቀጥ ጀመሩ። በመጨረሻም የከሳውና የገረጣው ፊቷ አበራ። ተጣጥራም÷ «ጌታ ኢየሱስ ና!» የሚሉትን የተስፋ ቃላት ለመተንፈስ ቻለች።

እነዚህን ቃላት እንደ ተነፈሰች ነፍስዋ ከሥጋዋ ተለየች። መንፈስዋም ወደ ባለቤቱ ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ።

# የፖሊዮ ፍርድ ፊት መቅረብ

‹‹ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋና አዘጋጀህ፡፡››

ከቤተ መንግሥቱ አቅራቢያ በሚገኝ ታላቅ ሕንፃ ውስጥ አንድ ሰፊ አዳራሽ ነበር፡፡

የአዳራሹ ወለል በዕብነ በረድ የተለበጠ ነው፡፡ ጣራው ለዓይን የሚያስደስት ቅርፅና ውበት ባላቸው ዓምዶች ተደግፎአል፡፡ በአዳራሹ በአንደኛው ወገን አንድ ጣዖት የቆመበት መሠውያ ይታያል፡፡ በአንፃሩ የክብር ልብሳቸውን የለበሱ ዳኞች ተሠይመዋል፡፡ በዳኞቹ ፊት ለፊት ወታደሮች አንድ እሥረኛ ይዘው ቆመዋል፡፡

እሥረኛው ወጣቱ ፖሊዮ ነበር፡፡

ከደረሰበት ጉስቁልና የተነሣ ፊቱ ገርጥቶአል፡፡ አቋቋሙና ሁኔታው ግን ያው እንደ ቀድሞ ጽናቱንና ልበ ሙሉነቱን የሚያመለክት ነበር፡፡

የሚመለከተው ሰው ሁሉ ብልህነቱንና አርቆ አሳቢነቱን በቀላሉ ሊረዳ ይችላል፡፡ የወጣትነት ሕይወቱን ያለ ጊዜው የሚቀጭ ፍርድ የተደገሰለት መሆኑን ቢረዳም የፍርሃትና የብረክረክ ምልክት ፈጽሞ ዐይታይበትም ነበር፡፡ የውድ እናቱን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ጧቱን ሰምቶ ስለ ነበር ከዚህ ዓለም ጋር ያቆራኘው ጽኑ የሆነ የፍቅር ሰንሰለት የተበጠሰ መሆኑን ተረድቶታል፡፡

የእናቱን መሞት ወሬ ለፖሊዮ የነገረው ማርሴሉስ ነበር፡፡ ይህንንም ያደረገው ለእናቱ ሲል ዐሳቡ እንዳይላላ በማለት ነው፡፡ ማርሴሉስና ፖሊዮ በምሥጢር ተገናኝተው እንዲነጋገሩ ያደረገው ሉኩሉስ ነበር፡፡ ፖሊዮ በእሥር ቤት በነበረበት ጊዜ ስለ እናቱ በጥብቅ ያስብ ነበር፡፡

መሞትዋን ከሰማ በኋላ ግን ከዚህ ዓለም ወደምትገኝበት ዓለም የሚያሸጋግረው ድልድይ መስሎ ታየው፡፡ ይህን በመሰለው ተስፋ በመጽናናት የሚቀርብለትን ጥያቄ ለመስማትና የሚወሰንበትንም ፍርድ ለመቀበል ተሰናድቶ ይጠባበቅ ጀመር፡፡

‹‹ማን ትባላለህ?››

‹‹ማርቆስ ሰርቬሉስ ፖሊዮ፡፡››

‹‹ዕድሜህ ምን ያህል ነው?››

‹‹ዐሥራ ሦስት ዓመት፡፡››

የልጁ ስም በአዳራሹ ውስጥ በተሰማ ጊዜ በተሰበሰቡት ሰዎች

ላይ የርኅራኄን ስሜት ፈጠረ። ምክንያቱም የፖሊዮ ዘሮች ስም በሮም ከተማ በጣም የታወቀና የተከበረ ነበር።

‹‹ክርስቲያን በመሆን ወንጀል ተከሰሃል? ምን መከላከያ አለህ?››

ፖሊዮም÷ ‹‹እኔ ምንም የሠራሁት ወንጀል የለም። ክርስቲያን መሆኔ ግን እውነት ነው። ክርስቲያንነቴንም በሰዎች ፊት ለማስታወቅ ዕድል በማግኘቴ በጣም ደስ ይለኛል›› አለ።

ከዳኞቹ አንዱ÷ ‹‹ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ ይኸው ናቸው። የሚናገሩት ቃል ተሰናድቶ የቀረበላቸው ይመስላል›› ሲል ተናገረ።

‹‹ወንጀልህ የሚያስከትለው ነገር ምን እንደ ሆነ ታውቃለህን?››

‹‹እኔ ምንም ወንጀል አልሠራሁም። እምነቴ እግዚአብሔርን መፍራትና ንጉሥን ማክበርን ያስተምረኛል። ትክክለኛ የሆነውን ሕግ ሁሉ አከብራለሁ። ስለዚህ ከዳተኛ ወይም አጥፊ አይደለሁም።››

‹‹ክርስቲያን መሆን አገርን እንደ መክዳት የሚያስቈጥር ወንጀል ነው።››

‹‹ክርስቲያን መሆኔ እርግጥ ነው። ከዳተኛ ግን አይደለሁም።››

‹‹የመንግሥት ሕግ ክርስቲያን የሆኑትን ሁሉ በሞት ቅጣት እንዲቀጡ ያዛል። ክርስቲያን ነኝ ብለህ ካመንህ መሞት አለብህ።››

ፖሊዮም በማያወላውል ቃል÷ ‹‹አዎን÷ ክርስቲያን ነኝ›› አለ።

‹‹እንግዲያው ትሞታለህ?››

‹‹እንዳላችሁት ይሁን።››

‹‹አንተ ልጅ÷ ሞት ምን ማለት እንደ ሆነ ታውቃለህ?››

‹‹አዎን÷ ባለፉት ወራት ውስጥ ብዙ የእምነት ወገኖቼ በብዛት ሲገደሉ የዓይን ምስክር ለመሆን በቅቻለሁ። እኔም ተራዬ ሲደርስ ለጌታዬ ሕይወቴን መሥዋዕት ማድረግ ያለብኝ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።››

‹‹አንተ ገና ሕፃን ነህ፤ ነገርን አውጥቶ አውርዶ ለማመዛዘን ዕድሜህ አይፈቅድልህም፤ ወደዚህ ስሕተት የገባኸው በገዛ ፈቃድህ አለመሆኑን ሳንገነዘበው አልቀረንም። ይህን ሁሉ ችላ ብለን ለማለፍ የተዘጋጀን ነን። ይህ እንዲህ ድርቅ የሚያደርግህ እምነት ፍጹም ከንቱነት ነው።››

‹‹ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ተሰቅሎ የሞተውን አንድ አይሁዳዊ እንደ አምላክ ተቀብለህ ማመንህ በጣም የሚያስገርም ነገር ነው። ከዚህ የባሰ ምን ሞኝነት አለ! የእኛ እምነት ግን የመንግሥት እምነት ነው። ይህም እምነት ሐዋርያትና ሽማግሌዎችን የተማሩትንም ሆነ ማይሞችን ሊያረካ ይችላል። ይህንን የጭፈናና የሞኝነት እምነት ትተህ ወደ

ቀድሞው እምነትህ እንድትመለስ።››

‹‹አላደርገውም።››

‹‹መኳንንት ከሆኑት ወገኖች የቀረህ አንተ ብቻ ነህ። መንግሥትም የወገንህን የሴርቪልን ታላቅነት አልዘነጋም። አያት ቅድመ አያትህ በተድላና በደስታ በመኖር ጊዜአቸውን ያሳለፉ ናቸው። አንተ ግን ድሃና እሥረኛ ሁነህ ትገኛለህ። አስተውል ፖሊዮ ሆይ÷ የአያት የቅድመ አያቶችህን ዝናና ክብር በማስታወስ ከእነርሱ ደረጃ አውርዶ በአደጋ ላይ ሊጥልህ የተዘጋጀውን መሰናክል በፍጥነት አስወግድ።››

‹‹አልችልም!››

‹‹ሕገ ወጥ በመሆን እስካሁን ያሳለፍከውን አሳፋሪ ሕይወት አትዘንጋ። ከአንተ ይልቅ በሮም ውስጥ የሚገኝ ለማኝ ይሻላል። ያለ ብዙ ድካምና ውርደት የዕለት እንጀራውን ማግኘት ይችላል። ከዚህም በቀር በነፃነት ፀሐይን ሲሞቅና በሰላም ያለ ሥጋት ሲኖር መብት አለው። የሮምንም ፍርድ በመፍራት በመበርገግና በሥጋት አይሰቃይም። የአንተ ኑሮ ግን በጨለማ ውስጥ በችግርና በዕጦት የተመረዘ ነው። ይህ እንዲህ የመጥኝ የምትለው እምነትህ ምን አደረገልህ? ወይስ ይህ አምላክ ያደረጋችሁት አይሁዳዊ ምን ፋይዳ ሠራልህ? ከዚህ ከአታላይ መንገድህ ተመለስ።››

‹‹እንዲህ ብታደርግ ሀብትና ምቾት÷ ወዳጅና ክብር÷ እንዲሁም የቄሣር ሞገስ ያንተ ሊሆን ይችላል።››

‹‹አላደርገውም።››

‹‹አባትህ ታዛዥና ጀግና ወታደር ነበር። ሕይወቱንም መሥዋዕት ያደረገው ለአገሩ ሲል በጦር ሜዳ ላይ ነው። አንተንም ስሙን እንድታስጠራለት የክብሩና የሀብቱ ወራሽ አደረገህ። አሁን የያዝህ አጉል መንፈስ ይህን ወደ መሰለው የስሕተት ጎዳና ላይ ይጥልሃል ብሎ ዐላሰበም። በሐዘን የተጎዳው የእናትህ አእምሮ ይህንኑ አጥፊ ትምህርት እስከ መቀበል አደረሳት። አንተም የእርሷኑ አርአያ ተከተልክ። አባትህ በሕይወት ቢኖር ኑሮ ይህ ሁሉ ባልደረሰም ነበር። አንተም ሆንክ እናትህ የመልካም ዘራችሁን ስም ከማስጠራት የሚያግዳችሁ ነገር ባልተገኘም ነበር። የአባትህን መታሰቢያ ታከብራለህ? የልጅነት ተግባርህን እንድትፈጽም በመካከላችን የተከበረ ስም ማርከስና ማስነወር የሚገባ ይመስልሃል? ዓይንህን ካሳወረው ስሕተት ተመለስ። ስለ አባትህ መታሰቢያና ስለ ወገኖችህ ክብር ስትል ከዚህ አጉል መንገድ ተመለስ።››

‹‹ወገኖቼን የሚያዋርድ ምንም ነገር አልሠራሁም። በዚህም በቀር እምነቱ ቅዱስና ንጹሕ ነው። እሞታለሁ እንጂ መድኃኒቱን ልክድ አልችልም።››

‹‹ያሳየንህን ምሕረትና ርኅራኄ አትናቅ። ይህንንም ለማረግ ያስገደደን ዕድሜህና ስምህ ነው።››

‹‹እንደ ማንም ተራ እሥረኛ ብትሆን ኖሮ ከሞትና እምነትህን ከመተው መካከል ምርጫ እንድታደርግ በአንድ አፍታ በጠየቅንህ ነበር። ከአንተ ጋር እንደዚህ አታካራ የገጠምነው አንተን የመሰለ የጨዋ ልጅ በስሕተቱ ምክንያት አደጋ እንዳይደርስበት በማለት ነው።››

‹‹ስለ ርኅራኄያችሁ ከልብ አመሰግናለሁ። ዳሩ ግን ክርክራችሁ ምንም ሊያጠግበኝ አልቻለም። ጌታዬ እንድፈጽመው የሚፈልግብኝን ግዴታ ከእናንተ ክርክር የላቀ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።››

‹‹ምን ያለኸው ሞገደኛ ልጅ ነህ! እኛ አንተን ለማዳን ያደረግነው ጥረት ከንቱ መስሎ ከታየህ ከባድ የሆነውን የቄሣርን ቍጣ ትቀምሳለህ።››

‹‹የበጉ ቍጣ ከቄሣር ቍጣ የላቀ ነው።››

‹‹ብዙውን ጊዜ ንግግርህ ሁሉ መላ ቅጥ የሌለው ነው። የበጉ ቍጣ የምትለው ምንድን ነው? ፊትህ ያለውን ነገር አልተመለከትክም?››

‹‹ከእኔ በፊት ያለፉት ወንድሞቼ አሠቃቂ በሆነ መንገድ ሞትን ቀምሰዋል። እኔም እንደ እነርሱ ኃይል እንደማገኝ አምናለሁ።››

‹‹ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የሚደርስብህን ሥቃይ ትታገሣለህ?››

‹‹ከሰዎች ችሎታ በላይ የሆነ ኃይል እንደሚሰጠኝ አልጠራጠርም።››

‹‹ከአንበሶችና ከነብሮች ጋር ለመጋጠም ትችላለህ?››

‹‹የምታመንበት መድኅን በመከራዬ ጊዜ እንደማይተወኝ አምናለሁ።››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹እርግጠኛ ሊያደርገኝ የሚችለው በወደደኝና ሕይወቱን ለእኔ በሰጠው መታመኔ ነው።››

‹‹በእሳት እንድትቃጠል የተደረገ እንደ ሆነስ?››

‹‹የእሳቱን ነበልባል ትችላለህ? ስለ እርሱስ ዐስበሃል?››

‹‹ማንኛውም ነገር ቢደርስብኝ ወደ ኋላ አላፈገፍግም። ሥቃዩም ቶሎ ያልፋል፤ ከዚያም በኋላ ከጌታ ጋር በደስታ ለዘለዓለም እኖራለሁ።››

‹‹እንደዚህ አድርጎ ዓይንህን ያሳወረው ይህ የጭፈና እምነትህ ነው። የተደገሰልህ መከራ ምን እንደ ሆነ የተረዳኸው አይመስልም።

በአማን ጊዜ ጀግና ሆኖ መታየት አስቸጋሪ አይደለም። ከመከራ ጋር ፊት ለፊት በምትገጥምበት ጊዜ ምን ይውጥህ ይሆን?››

‹‹ወገኖቹን በመከራቸው ጊዜ እንደሚረዳቸው ተስፋ ወደ ሰጠው እመለከታለሁ።››

‹‹እስካሁን ድረስ ምንም አላደረገልህም።››

‹‹እርሱ ያላደረገልኝ አንዳች ነገር የለም። እኔ ለዘለዓለም እኖር ዘንድ ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎልኛል። አሁን ልትወስዱብኝ ከተዘጋጃችሁት ከሥጋዊ ሕይወት የበለጠ ሕይወት አዘጋጅቶልኛል።››

‹‹ይህ ሁሉ ቅዠት ነው። ይህን የምትለውን ሁሉ አንድ አይሁዳዊ እንዴት ሊያደርግልህ ይችላል?››

‹‹እርሱ የመለኮት ሙላት ነው። በሥጋ የተገለጠው አምላክ እርሱ ነው። የዘላለምን ሕይወት እንድናገኝ በሥጋው መከራ ተቀበለ።››

‹‹እባክህ አንተ ልጅ ዓይንህን ሊከፍተው የሚችል ነገር የለም? ይህ አጉል እምነትህ እስካሁን ያመጣብህን መከራ አትረዳም? ላልረባ እምነት ከመሞት መሰንበትን ብትመርጥ ይሻልሃል!››

‹‹ሞትን ድል የማደርግበት ኃይል ስለሚሰጠኝ ምንም አልፈራም። ሞትም ከዚህ መከራና ሥቃይ ከሞላበት ዓለም ዘላለማዊ ደስታ ወዳለበት የሚያስተላልፍ መሸጋገሪያ ነው። የምሞተው በአውሬዎች ተቦጫጭቄ ወይም በእሳት ተቃጥዬ ቢሆን ምንም ልዩነት አያመጣም። ያመንኩበት መድኃኔ በእምነቱ ጸንቼ እንድገኝ ያደርገኛል። ከሞትኩ በኋላም የዘላለምን ሕይወት ይሰጠኛል። እናንተ ማስፈራሪያ ያደረጋችሁትን ሞት ከምንም አልቈጥረውም። ልትሰጡኝ የተዘጋጃችሁት ሕይወት ግን የሞት ሞት መስሎ ይታየኛል።››

‹‹ብትወድም ባትወድም የመጨረሻ ዕድል እንሰጥሃለን፤ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለህ ይህ የእብድነት መንገድህ ሊያስከትልብህ የሚችለውን አደጋ ማስተዋል አለብህ። እነዚህ አጥፊ የሆኑ መምህራንህ የነገሩህን ለጥቂት ጊዜ እርሳው። ሕይወት ከክብር÷ ከሀብትና ከወዳጆች ጋር በደጅህ ቆማ ተቀበለኝ ትልሃለች። የወላጆችህ የጨዋነት ክብር እጁን ዘርግቶ ይጠብቅሃል። ይህ ሁሉ የአንተ እንዲሆን ከፈለግህ በዚህ ጾዋ ውስጥ ያለውን መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ ከማፍሰስ የበለጠ አይፈለግብህም። ቶሎ ብለህ ያዘዝንህን በመፈጸም ሕይወትህን ከሞት አድን!››

በዚህ ጊዜ በፍርድ አዳራሹ ውስጥ የተሰበሰበው ሕዝብ ዓይን ፖሊዮን ትክ ብሎ ይመለከት ጀመር። ወጣቱ ፖሊዮ ይህን ሁሉ ሲሰማ

ፍንክች አለማለቱ ሁሉንም በአድናቆት ላይ ጣላቸው። ይህን ያህል ድፍረት የሰጠው አንድ ከሰብአዊ ችሎታ ውጭ የሆነ ኃይል መሆኑን ተገነዘቡ።

ፖሊዮም ጽኑ በሆነ መንፈስ፥ «ምንም ቢሆን መድኃኒቴን አልክድም!» ሲል የመጨረሻ ቃሉን አሰማ።

ለጥቂት ጊዜ በአዳራሹ ውስጥ ጸጥታ ሆነ። ዋናው ዳኛም፥ «አንተው በራስህ ላይ ፈርደሃል፤ ውሰዱት!» ሲል ወታደሮቹን አዘዛቸው።

# የፖሊዮ ሞት

«እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን፤ እኔም የሕይወት

አክሊል እሰጥሃለሁ።»

በፖሊዮ ላይ የተወሰነበት ፍርድ ጽኑ ነበር። ፍርድ በተሰጠው በማግሥቱ በኮሎሴዩም ውስጥ ታላቅ ትርእይት ይዘጋጅ ጀመር። በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ደም የተጠሙ ሮማውያን እንደ ልማዳቸው ስፍራውን አጣበውት ይታያሉ።

በአሠቃቂነቱ የባሰው ትርእይት የሕዝቡን ጭብጨባና ውካታ ያመነጭ ነበር።

ብዙዎቹ ተዋጊዎች በሕዝቡ ፊት በጨበጣ እየተጨፋጨፉ አለቁ። በአደባባዩ ውስጥ የሚታዩት ትርእይቶች ሁሉ ታዩ።

እየተደጋገመ ስፍራው በደም ታጠበ፤ አሸናፊውም ዘላቂ ያልሆነ የምሥራች ቃል ከተመልካቾቹ ተቀበለ። ሰዎች ከሰዎች ጋር ግብ ግብ በመግጠም ወይም ከተራቡ ነብሮች ጋር በመታገል ብዙዎቹ አለቁ። የቈሰለውም ተዋጊ ምሕረት እንዲደረግለት ወደ ተመልካቾቹ ዓይኑን ሲያቀና የሞት ምልክት ከሆነው ወደ ምድር ከተዘቀዘቀው አውራ ጣት በስተቀር የሚያየው ሌላ ነገር አልነበረም።

የደም ጥማታቸው ጥቂት ጋብ ያለው ሮማውያን የብዙ ሰዎችን በአንድ ጊዜ መተላለቅ ለማየት ያላቸውን ጉጉት መግለጽ ጀመሩ። ስዚህ መጨረሻ ትርእይት የሚቀርቡት ክርስቲያኖች መሆናቸውን ተመልካቾቹ ስለሚያውቁ የእነርሱን መታየት በታላቅ መቍነጥነጥ ይጠባበቁ ጀመር። ከቄሣሩ መቀመጫ አጠገብ ሉክሉስ ከሌሎቹ መኰንኖች ጋር ቆሞአል። በፊቱም የሐዘን መልክ ይታይበታል።

ከሉክሉስ በስተጀርባ በሚገኘው ከፍተኛ መቀመጫ ላይ ፊቱን ቀጭም አድርጎ አንድ ሰው ተቀምጦአል። እርሱም ትክ ብሎ

የሚመለከተው ትርእይቱ የሚፈጸምበትን አደባባይ ነበር። በፊቱ ላይ የተቀረፀው የሥጋት ምልክት በዙሪያው ካሉት ሰዎች የተለየ አድርጎታል። ከዋሻዎቹ ያንዱ በር ተከፈተ። አንድ ነብር እየተዘናከተ አደባባዩ ውስጥ ገባ። ጅራቱን ወዲህና ወዲያ እያማታ ደም በጎረሱ ዓይኖቹ በዙሪያው የከበበውን ሕዝብ ይቃኝ ጀመር።

ወዲያው ሕዝቡ አጉረመረመ። አንድ ወጣት ልጅ አደባባዩ ውስጥ ተገፍቶ ሲገባ ታየ። የልጁ ሰውነት ቀጭን÷ ፊቱ የከሳና የገረጣ ነበር። ወገ እንዳይቀር ተብሎ የተዋጊ ልብስ ቢያለብሱትም በነዚያ ደም በተጠሙ አራዊቶች ፊት ቁሞ ሲታይ ከምንም የሚቈጠር አልነበረም።

ምንም እንኳ ልጁ በዕድሜው አነስተኛ÷ ሰውነቱ ከሲታ ቢሆንም የፍርሃት መልክ ዐይታይበትም ነበር። አስተያየቱ ሁሉ በቈራጠኝነትና በጸጥታ የተሞላ ነበር። ጕዞውን በጸጥታ ወደ አደባባዩ መካከል ቀጠለ። እዚያም እንደ ደረሰ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አቅንቶ መጸለይ ጀመረ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ነብሩ ወዲህ ወዲያ ይንጐራደድ ነበር። የልጁ አደባባዩ ውስጥ መግባት አንዳችም ስሜት አልሰጠውም። ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ የሚመለከተው በዙሪያው የተቀመጡትን ተመልካቾች ነበር። አልፎ አልፎ የሚያሰማው የቍጣ ድምፅ ልብን የሚያሸብር ነበር።

ያ ፊቱን ቅጭም አድርጎ የተቀመጠው ሰውዬ አደባባዩ መካከል ቁሞ የሚጸልየውን ልጅ ትክ ብሎ ይመለከት ጀመር።

ነብሩ በጸሎት ላይ ያለውን ልጅ ለማጥቃት ፍላጎት የሌለው መሆኑ በሁሉ ዘንድ ግልጽ ሆነ።

ተመልካቾቹ መቍነጥነጥ ጀመሩ። በጩኸታቸውና በፉጨታቸው ነብሩን ለማነሣሣት ሞከሩ።

በውካታውም መካከል አንድ አስፈሪ የሆነ ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማ።

«ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ÷
እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም?
ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ
እስከ መቼ አትበቀልም?»

በስፍራው ታላቅ ጸጥታ ሆነ። አንዱ ሌላውን ዞር እያለ በመደነቅ ይመለከት ጀመር። ጸጥታውም መጀመሪያ በተሰማው አስፈሪ ድምፅ ዳግመኛ ታወከ።

«እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል

ዓይነትም ሁሉ ያኮራል

የወጉት ሁሉ

የምድርም ወገኖች ሁሉ

ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ

አዎን፥ አሜን።

ያለህና የነበርህ ጌታ ሆይ፥

ቅዱስ ሆይ፥

እንዲህ ስለ ፈረድህ ጻድቅ ነህ

የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ

ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል

የሚገባቸው ነውና።

አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ ሆይ፥

ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው።››

የሕዝቡ ጩኸትና ውካታ እየባሰበት ሄደ። ወዲያውም የሽብሩ ምክንያት ታወቀ። ጥቂቶቹ ተመልካቾች እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር።

‹‹ይህ ድምፅ የተሰማው ከአንድ ርኩስ ክርስቲያን ነው! እንዲህ ሊረግመን የደፈረው ክርስቲያኑ ሲና ነው። አውጡና ለነብሩ ይስጥ፤ ይሙት!››

የሰዎቹ ጩኸት ጆሮ የሚያደነቁር ሆነ። ነብሩም ከጩኸቱ የተነሣ ይቅበዘበዝ ጀመር። በር ጠባቂዎቹም የታዘዙትን ለመፈጸም ወደ ዋሻው በር ፈጥነው ሄዱ።

በሩ ሲከፈት ተሰማ። አንድ በጣም የከሳና የገረጣ ሽማግሌ ወዲህ ወዲያ እየተወላገደ አደባባዩ ውስጥ ገባ። ዓይኖቹ ልዩ በሆነ ብርሃን የሚያንጸባርቁ፥ ጉንጮቹናም የመሰሉ ነበሩ። ጥንታቂ የጉደለው ጸጉሩም ተንጨባርሯል።

ነብሩ ዐይቶት ኖሮ እየዘለለ ተጠጋው። ጥቂት እርምጃዎች እንደ ቀረው ከሹ ተኛ። ይጸልይ የነበረው ልጅ ቀና ብሎ በዙሪያው የሚፈጸመውን ነገር ተመለከተ። ሲና ግን የነብሩን መቅረብ አልተመለከተም። ዓይኖቹን በተመልካቾቹ ላይ ትክል አድርጎ በሚያስፈራ ድምፅ እንዲህ አለ፡-

‹‹ወዮላችሁ! ‹‹ወዮላችሁ! በምድር የምትኖሩ ወዮላችሁ!››

በዚህ ጊዜ ነብሩ ዘሎ ጉብ አለበት። ሲናም ወደቀ። ድምፁም በደመ ጅረት ውስጥ ሰጥሞ ቀረ።

የነብሩ የደም ፍላጎት ከፉኛ ተነሣሥቶ ስለ ነበረ ጸጉሩን ገትሮ

ደም የለበሱ ዓይኖቹን እያንሬለጠረጠ ጅራቱን ግራና ቀኝ እያማታ ወደ ልጁ ፊቱን አዞረ።

ልጁም የመጨረሻ ጊዜው እንደ ደረሰ በመገንዘቡ እንደ ገና ተንበርክኮ ጸሎቱን ቀጠለ። ተመልካቾቹም የሚቀጥለውን ትርእይት ለመመልከት ልባቸው ስቅል አለ። ያ የልጁን ሁኔታ አትኩሮ ይመለከት የነበረው ሰውዬ ሳያስበው ከመቀመጫው ላይ ተነሥቶ ቆመ። ከኋላው የተቀመጡት ሰዎችም በቍጣ ቃል፥ «ተቀመጥ! ተቀመጥ! ማየት ከለከልከን!» እያሉ ጮኹ።

ሰውዬው ግን ጩኸታቸውን ችላ በማለት ዝም ብሎ ቆሞ ወደ አደባባዩ መመልከቱን ቀጠለ። የሰዎቹ ጩኸት እየተጋጋለ በመሄዱ ዝቅ ብለው ቆመው የነበሩት መኰንኖች ጕዳዩን ለመረዳት ዞር ብለው ተመለከቱ።

ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ሉኩሉስ ነበር። ወደ ኋላው ዞር ብሎ ያየው ነገር ክፉኛ ድንጋጤ ላይ ጣለው።

«ማርሴሉስ!» ሲል ከጮኸ በኋላ እየተንገዳገደ ረብሻው ወደ ተነሣበት ስፍራ ሄደ። ከሕዝቡ ዘንድ የማጕረምረም ድምፅ ተሰማ። ቍጣው እስኪገነፍል ድረስ ልጁን ዐሥር ጊዜ ይዞር የነበረው ነብር ለዝላይ ሲመቻች ታየ። ልጁም ከተንበረከከበት ተነሣ። ፊቱ እንደ መልአክ ፊት ያበራ ጀመር። ዐሳቡ ሁሉ ከግዙፉ ሕንፃ በብዙ ሺህ ከሚቈጠሩት ተመልካቾች ወይም ጨካኝ ከሆነው አውሬ የራቀ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር። እርሱ በዚያን ጊዜ ይታየው የነበረው የዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም በር ሲከፈትና የክብርዋ ተካፋይ ሲሆን ነበር።

«አማምዬ መጣሁልሽ! ጌታ ኢየሱስ ነፍሴን ተቀበል»

እነዚህ ከልጁ አንደበት የወጡት ቃላት በተመልካቾቹ ዘንድ በግልጽ ተሰሙ። ነብሩም ዘሎ ፖሊዮ ላይ ተከመረበት። ለጥቂት ጊዜ ትግሉ ቀጠለ። በመጨረሻም የወጣቱ የፖሊዮ ሰውነት በደምና በአቧራ ውስጥ ተለውሶ ቀረ።

ሕዝቡም ለጥቂት ጊዜ ጸጥ እንዳለ አንድ ግልጽ የሆነ ድምፅ እንዲህ ሲል ተመልካቾቹን አስደነገጠ፤ «ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? መቃብር ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።»

በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች በጩኸትና በቍጣ ከመቀመጫቸው ተነሥተው እጃቸውን ወደ ሰውዬው እያመለከቱ እንዲህ አሉ፦

አደባባዩ ውስጥ ወርውሩት!››

ለዚያ ድምፅ የተሰጠው መልስ ይህን የመሰለ ነበር። ሉኩሉስም በጊዜ ደርሶ ሊቦጫጭቁት ካቆበቆቡት ሮማውያን እጅ ማርሴሉስን ለማዳን ቻለ።

በአደባባዩ መካከል ወዲያ ወዲህ የሚንጎራደደው ነብር የሕዝቡን ያህል ደም አልተጠማም። ጭካኔአቸውም ወደር አልነበረውም።

ሉኩሉስም ማርሴሉስን አድኖ ለተከተሉት ወታደሮች ወደ ውጭ አውጡት ብሎ አዘዛቸው። ውጭ እንደ ወጡም ሁለቱ ጓደኞች ንግግር ጀመሩ፤ ወታደሮችም ተከትለዋቸው ነበር።

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ ብለህ ብለህ ነፍስህን ለአደጋ መስጠት ትሞክራለህ?››

‹‹ምን ላድርግ? ያ የምወደው ልጅ ፊቴ ላይ ሲሞት አላስችል አለኝ። ራሴን መግታት ፍጹም አቃተኝ፡፡ በተናገርኩት ቃል ምንም አልጸጸትም። እኔም ለንጉሤና ለአምላኬ ለመሠዋት ተዘጋጅቻለሁ።››

‹‹ከአንተ ጋር ለመከራከር ጊዜ የለኝም። ከዚህም በቀር በክርክር የማትመለስ መሆንህን ደኅና አድርጌ ዐውቃለሁ።››

‹‹እንደ እውነቱ ከሆነ ራሴን አሳልፌ ለመስጠት ምንም ዐሳብ አልነበረኝም። ከሆነ ወዲያ ግን ምንም ወደ ኋላ የማፈገፍግበት ፍላጎት አልነበረኝም። በመድኃኒቴ ስም የመሞትን ክብር በማግኘቴ በጣም ደስ ይለኛል።››

‹‹ውድ ወዳጄ ሆይ÷ ለሕይወትህ ምንም ግምት አትሰጣትም?››

‹‹ከሕይወቴ ይልቅ መድኃኒቴን እወደዋለሁ።››

‹‹ተመልከት ማርሴሉስ÷ መንገዱ ክፍት ነው። ይኸው ሸሽተህ በማምለጥ ሕይወትህን ለማዳን ትችላለህ፤ ዕወቅበት።››

ወታደሮቹ ጥቂት ፈንጠር ብለው ቆመዋል። ሉኩሉስም እነዚህን ቃላት የተናገረው እየተንሾካሾከ ነበር። የሆነ ሆኖ ማርሴሉስ ሮጦ ሊያመልጥ ይችል ነበር።

ማርሴሉስ የጓደኛውን እጅ ጨብጦ እንዲህ አለ።

‹‹ሉኩሉስ ሆይ÷ የአንተን ስም በማጥፋት ሕይወቴ እንድትድን አልሻም። ሁልጊዜ ለደኅንነቴ ስለምታስብልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። በእኔ ምክንያት እንድትቸገር አልፈልግም።››

ሉኩሉስም የጓደኛውን ንግግር ከሰማ በኋላ በሐዘን አቀርቅሮ ወደ መሣዘት ተመለሰ።

# መፈተን

‹‹ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ፡፡››

የዚያን ዕለት ማታ ሉኩሉስ ጓደኛው እታሠረበት ክፍል ውስጥ አመሸ፡፡ በተቻለው መጠን ውሳኔውን እንዲለውጥ ለማድረግ ሞከረ፡፡ ማባበሉና ክርክሩ ሁሉ ጓደኛውን አንድ ስንዝር እንኳ ሊያንቀሳቅሰው ሳይችል ቀረ፡፡ የማርሴሉስ እምነት በጽኑ መሠረት ላይ ያረፈ በመሆኑ ስጠላት ማስፈራራትም ሆነ ለወዳጁ ልመና አልበገር አለ፡፡ ማርሴሉስም በሚከተሉት ቃላት ዐሳቡን ለጓደኛው ገለጸ፡- ‹‹ማንኛውም ነገር ቢደርስብኝ አንድ ጊዜ የተቈረጠ ውሳኔ አድርጌአለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁት ሊደርስብኝ የሚችለውን ነገር በመዘንጋት አይደለም፡፡ የሆነ ሆኖ አሁን የመረጥኩትን መንገድ ትቼ ወደ ኋላ የምልበት ምክንያት የለኝም፡፡

ሉኩሉስም እንዲህ አለ፡-

‹‹እኔ ለጊዜው የምለምንህ አንድ ትንሽ ነገር ነው፡፡ እምነትህን ጨርሰህ እንድትተው አልፈልግም፡፡ ያሁኑ ስደት ማንንም የማይምር በመሆኑ ነፍስህን ለማዳን ብቻ እምነቱን ትቼአለሁ ብትል መልካም መስሎ ይታየኛል፡፡ ጊዜው የከፋ መሆኑን አንተው ራስህ በዓይንህ አይተሃል፡፡ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ፖሊዮ መሞት አልነበረበትም ነበር፡፡ በወጣትነቱ ምክንያት ርኅራኄአቸውን የገለጹለት ብዙዎች መሆናቸው አይጠረጠርም፡፡ የዕድሜው ማነስም ሆነ የታላቅ ወገንነቱ ሊረዳው አልቻለም፡፡ የሕጉን ጥብቅነት በዚህ ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ሲናን የመሰለ ሽማግሌ መግደል አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ከዚህም በቀር ሁኔታው ሁሉ ከአበደ ሰው ምንም የተሻለ አልነበረም፡፡ ይህ ሁሉ ሊያስረዳን የሚችለው በሰዎች ልብ ውስጥ የተፈጠረው የክርስቲያኖች ጥላቻ ምን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑን ነው፡፡››

‹‹ይህን ሁሉ ደኅና አድርጌ ዐውቃለሁ፡፡ የጨለማው ገዥ የእግዚአብሔርን ወገኖች ለማጥፋት መጣጣሩ ዛሬ የተጀመረ ነገር አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑ ሁሉ የቆሙት በጥንቱ አምባ መሠረት ላይ በመሆኑ የገሃነም ደጆች እንኳ ሊያጠቁአቸው አይችሉም፡፡ መልካሞቹ÷ ንጹሖቹ÷ ቅዱሶቹና ምንም ወንጀል ያልሠሩት ሲሠቃዩና ሲሞቱ ዐላየሁም? ለክርስቲያኖች ምንም ምሕረት የማይደረግላቸው መሆኑን ዐላውቅም? ይህ ሁሉ ከመጀመሪያው እንዶሥቶ ደኅና አድርጌ የተረዳሁት ነገር ነው፡፡ ክርስቶስን መድኃኒቴና ጌታዬ አድርጌ

በተቀበልኩበት ጊዜ ብዙ ችግርና መከራ የሚደርስብኝ መሆኑን ተገንዝቤዋለሁ። ዐውቄ የገባሁበት በመሆኑ ምንም አያሠጋኝም።››

‹‹ስማኝ ማርሴሉስ÷ እኔ የጠየቅሁህ ትንሽ ነገር ነው ብዬሃለሁ። ይህንን እንዲህ የምትጨነቅለትን እምነት ተው አልልህም። ዳሩ ግን የጊዜውን ሁኔታ በመመልከት የሚያዋጣውን መንገድ መከተል ያስፈልጋል። ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩልህ ስደቱና መከራው እየከፋ ሄዷል። በዚህ ጊዜ ብልህነት እንጂ እንደ ሞኝ ድርቅ ማለት ምንም አያጠጣም።››

‹‹ምን አድርግ ነው የምትለኝ?››

‹‹እንድታደርግ የምፈልገው ነገር የሚከተለው ነው። በጥቂት ዓመታት ውስጥ አንድ ለውጥ ሳይሆን አይቀርም። ስደቱና መከራው ይቋረጣል ወይም የሕዝቡ አስተያየት እየተለወጠ ይሄድ ይሆናል። ከዚህም በቀር የአሁኑ ቄሣር ሞቶ የተሻለ አስተያየት ያለው ቄሣር ይነግሥ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ክርስቲያን መሆን እንደ አሁኑ አስቸጋሪ አይሆን ይሆናል። አሁን ነፍሳቸውን ለማዳን በካታኮምቡ ውስጥ የተሸሸጉት ሁሉ በነፃነት ወደ ቀድሞ ስፍራቸው ይመለሱ ይሆናል። ይህን በማስታወስ ለመንግሥትህና ለወገኖችህ ታላቅ አገልግሎት ሊያተርፍ የሚችለውን ሕይወትህን በገዛ እጅህ በአደጋ ላይ መጣል የለብህም። የጊዜውን ሁኔታ በማመዛዘን ይህን ዐዲሱን እምነትህን ትተህ ወደ መንግሥት እምነት እንድትመለስ እለምንሃለሁ። ይህንንም የምታደርገው ለጊዜው ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለብህም። የተሻለ ጊዜ ሲመጣ እንደ ገና ክርስቲያን መሆን ትችላለህ።››

‹‹ሉኩሉስ ሆይ÷ ይህንን የምትለኝን ነገር ፈጽሞ ሳደርገው አልችልም። አንተ የምትጠይቀኝን ነገር ማድረግ የግብዝ ግብዝ ያደርገኛል። በሕይወቴ ውስጥ የተፈጸመውን ነገር ለመረዳት ብትችል ኖሮ ሕያው በሆነው አምላኬ ፊት ሐሰት በመናገር ነፍሴን እንድበድላት ባልጠየቅኸኝም ነበር። እንዲህ ከማድረግ ይልቅ ታላቅ ሥቃይ ተቀብሎ መሞትን እመርጣለሁ።››

‹‹የአስተያየትህን ጥንካሬ ስመለከተው ተስፋ ወደ መቍረጥ እያደረሳለሁ። ጉዳዩን በአእምሮህ ውስጥ አውጥተህ ብታወርደው መልካም ነው። እኔ የምጠይቅህ ዘይኛ እንድትሆን እንጂ ሐሰተኛ እንድትሆን አይደለም። በብልሃት ከአደጋ ማምለጥ ግብዝነት አያሰኝም።››

‹‹ይህን አድርጌ ከመገኘት እግዚአብሔር ይሠውረኝ።››

‹‹እስቲ ጉዳዩን እርቀህ ተመልከተው፤ እኔ የምለምንህን ብታደርግ

ራስህም ተጠቅመህ ሌሎችንም ትጠቅማለህ። የአንተ በሕይወት መቆየት የምትወዳቸውን ክርስቲያኖች በብዙ ሊጠቅማቸው ይችላል። እስከ አሁንም ክርስቲያኖች ሊንቀሳቀሱ የቻሉት በግልጽ የመንግሥትን እምነት በማይደግፉ ሰዎች እርዳታ ነው። ታዲያ እነዚህን የመሰሉትን ሰዎች ግብዞችና ሐሰተኞች ልትላቸው ትችላለህ? ረዳቶቻችሁና ወዳጆቻችሁ አይደሉም?››

‹‹እነዚህ የምትላቸው ሰዎች ስለ ክርስትና እምነትና ይህም እምነት በሰው ልብ ውስጥ ስለሚፈጥረው ተስፋ የእኔን ያህል አልተረዱም።

‹‹የዐዲሱ ልደት÷ የዐዲሱ ፍጥረት÷ የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ማደር÷ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ያለንን ግንኙነት ምሥጢር የእኔን ያህል አልገባቸውም። የዐዲሱ ተስፋና የዐዲሱ ፍላጎት ምንጭ የሆነው ዐዲስ ስሜት በልባቸው ውስጥ አልተፈጠረም። እነርሱ ክርስቲያኖችን መርዳትና ለክርስቲያኖች መራራትን እንደ መልካም ነገር ይቈጥሩታል። እምነቱን ለመክዳት÷ መድኃኒቱን ለማዋረድ የሚደፍር ክርስቲያን ግን በችግር ላይ የወደቁትን ወንድሞቹን የመርዳት ፍላጎት ሊኖረው ከቶ አይችልም።››

‹‹ማርሴሉስ ሆይ÷ አሁን የቀረኝ አንድ የመጨረሻ ሙከራ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ መንገዴን እቀጥላለሁ። የሚሳካልኝ መሆን አለመሆኑን ዐላውቅም። የመጨረሻ ተስፋዬ በመሆኑ እሞክራለሁ። የማቀርብልህም ዐሳብ የሚከተለው ነው። እምነትህን ማራከስ አይፈለግብህም። ለጣዖታት መሥዋዕት እንድታቀርብ አትጠየቅም። የማትፈቅደውን ማናቸውንም ነገር እንድታደርግ የሚያስገድድህ የለም። ያለፈው እንዳለፈ ይቈጠር። ቀድሞ ወደ ነበርክበት ከልብ እንኳ ባይሆን ከአንገት በላይ ተመለስ። በዚያን ጊዜ ግዴታውን ለመፈጸም የሚጣጣር ቈራጥ ወታደር መሆንህን የማያስታውስ የለም። ስለ እምነት ያለህ ዝንባሌ እስከዚህ ድረስ አልነበረም። በመቅደሶች ውስጥ የምትታየው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነበር። አብዛኛውን ጊዜህን የምታሳልፈው በሰፈራችን ውስጥ ነበር። ማንኛውንም የእምነት ምርምር ታደርግ የነበረው በምሥጢር ነበር። ማንኛውንም ዓይነት ዕውቀት ትቀስም የነበረው ፈላስፋዎች ከጻፉዋቸው መጻሕፍት እንጂ ከቀሳውስት አንደበት አልነበረም። ይህ ሁሉ አንድ ጊዜ ሆኖአል። አሁን ዝም ብለህ ወደ ቀድሞው ተግባርህ ተመለስ።

‹‹ከእኔ ጋርም በገሀድ በመታየት÷ የወትሮ ሥራህን በማከናወንና ከተደሰቱት ጋር በመደሰት ቅን አገልጋይ መሆንህን ግለጥ። ይህም

የሚያዋርድና የሚያበክፉ ነገር ለአኔ ነው። ነገ ሥልጣኖቹ ጠፍተህ መሰንበትህን ችላ እንደሚሉትና የዚህ ሰሞን ጠባይህን በምሕረት እንደ ሚያልፉት አምናለሁ። የቀድሞ ማዕረግህን ባይመልሱልህ እንኳ ካሃኝነት ደረጃ እንደማያወርዱህ እርግጠኛ ነኝ። ከዚህ በኋላ ማንኛውም ነገር የተቃና ይሆናል። በዝምታና በብልሃት እንዲሁም የዕለት ተግባርህን በሚገባ በማከናወን ያለፈውን ነገር እንዳልነበረ ለማድረግ ትችላለህ። ሮም የቆየህ እንደ ሆነ ወደ ክርስቲያን እምነት የመመለስህ ወሬ ሐሰት ነው ይባላል። ያለፈውንም ነገር የሚያነሣው አይኖርም።››

‹‹አይሆንም ሉኩሉስ፤ የአንተን ዐሳብ እንዳልቀበል የሚያደርጉኝ ብዙ ምክንያቶች አሉኝ። ስለ እኔ አዋጅ መታወጁንና ለያገቸ ሽልማት እንደሚሰጥ ተስፋ መደረጉን ታውቃለህ። ከዚህም በቀር ቄሣር ባለበት በኮሎሲዩም ውስጥ በግልጥ መታየቱ ከምሕረት ውጭ አድርጎኛል። ከሁሉም በላይ የአንተን ዐሳብ በመከተል የመድኃኒቴን ስም ለማዋረድ አልሞክርም። የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ሁሉ እምነታቸውን በግልጽ ማስታወቅ አለባቸው። ራሱ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ እንዲህ ብሎአል፦ ‹‹በሰው ፊት ያመነብኝ እኔም በእግዚአብሔር መልአክ ፊት አምነበታለሁ።›› መድኃኒቴን በሥውር መክዳት በገሀድ ከመክዳት የሚያንስበት ምክንያት የለውም። አስቀድሞ የወደደኝና ሕይወቱን ስለ እኔ ድኅነት መሥዋዕት ያደረገውን መድኅን ከልክ ያለፈ አፈቅረዋለሁ። በሰዎች ፊት ስለ እርሱ መመስከርን እንደ ታላቅ ክብር እቈጥረዋለሁ። ለእርሱ ከመሞት የበለጠ መልካም ተግባር ያለ አይመስለኝም። የሰማዕትነት አክሊል ከሁሉ የበለጠ የብዕዕና ዋጋ ነው።››

ሉኩሉስም ጥረቱ ሁሉ ፍሬ ቢስ መሆኑን በመገንዘብ ልመናውን አቆመ። የተረፈውንም ጊዜ ስለ ሌሎች ነገሮች በመነጋገር አሳለፉ። ማርሴሉስ በበኩሉ ከጓደኛው ጋር እንዲያሳልፈው የተሰጠው ጊዜ በከንቱ እንዲባክን አልፈለገም። ጓደኛው ነፍሱን ለማዳን ያደረገውን ከልብ የሆነ ጥረት በመገንዘብ ስለ ክርስቶስ እምነት እያብራራ በማስረዳት በመልካም አኳኋን ብድር ሊመልስ ተጣጣረ።

ሉኩሉስም ወዳጁ የሚነግረውን ሁሉ ለእምነት ጉዳይ ባለው ዝንባሌ ሳይሆን ለወዳጅነቱ ሲል በጥንቃቄ ያዳምጥ ነበር። ከስማቸው ምሥጢራት ውስጥ አንዳንዶቹ በአእምሮው ውስጥ ሳይቀረው አልቀሩም።

በማግሥቱ ማርሴሉስ አፍርድ ፊት ቀረበ። የፍርዱም አሰጣጥ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተፈጸመ። ማርሴሉስም ወዲህ ወዲያ ሳያወላውል

የተሰጠውን ፍርድ በጀግንነት ተቀበለ። እንዲሞት የተወሰነው የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ነበር። የአሟሟቱም አኳኋን በአውሬዎች ተዘነጣጥሎ ወይም ከተዋጊዎች ጋር ግብ ግብ ገጥሞ ሳይሆን በእሳት ተለብልቦ እንዲሞት ነበር።

ማርሴሉስ ሕይወቱን ስለ እምነት መሥዋዕት እንዲያደርግ የተወሰነው ከዚህ ቀደም አያሌ ክርስቲያኖች የሰማዕትነት ማዕረግ ባገኙበት ስፍራ ላይ ነበር።

በኮሎሴዩም አደባባይ መካከል የጭራሮው ቁልል ጉልቶ ይታይ ነበር።

ማርሴሉስም አደባባዩ ውስጥ ጨካኝ በሆኑ ዘበኞች እየተመራ ገባ። እነርሱም ያለ ምሕረት ይገፈታትሩትና ይጉሻሽሙት ነበር። ዞር ዞር እያለ ትርእይቱን በመመልከት የተከማቹትን ሮማውያን ጨካኝና ርኅራኄ የራቀውን አስተያየት ተመለከተ። እርሱ በቆመበት ስፍራ ላይ በእምነታቸው በመጽናት ብዙ መከራና ሥቃይ በመቀበል ከሰማዕታት ሠራዊት ጋር የተቀላቀሉት ምእመናን ትዝ አሉት። በሥቃይ ሲሞቱ በዓይኑ ያያቸው ሕፃናት በአእምሮው ውስጥ ተቀርፀው በግልጽ ይታዩት ጀመር። የመዝሙራቸውንም ዜማ የነፋሱ ሽውታ አመጣለት።

‹‹ለእርሱ ለወደደን
ከኃጢአታችንም
በደሙ ላነጻን።››

ወታደሮቹ እያንሳቀሉ እንጨቱ ወደ ተከመረበት ስፍራ ወሰዱት። እንዳያመልጥ በማለት ከአንድ ግንድ ጋር በሰንሰለት አሠሩት።

በዚህ ጊዜ ማርሴሉስ እንዲህ ሲል ተሰማ፡- ‹‹ለመሠዋት ዝግጁ ነኝ። ከዚህ ዓለም የመለያ ጊዜዬም ደርሶአል። ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል። ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል።››

‹‹እሳቱ ተቀጣጠለ። ለጥቂት ጊዜም ጀግናው ሰማዕት በጢሱ ውስጥ ተሠወረ። ጢሱ እንደ ተወገደ ራሱን ወደ ሰማይ አቅንቶ እጆቹን ጭብጥ አድርጎ እንደ ቆመ ታየ።

የእሳቱ ነበልባል እየቀረበው ሄደ። የእሳት ምላስ ከበበው። ጢሱ ጠቈረ። የነበልባሉም ወላፈን ይገርፈው ጀመር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሰማዕቱ ማርሴሉስ ፍንክች ሳይል እንደ ቆመ ይታይ ነበር። ጭንቀቱና መከራው በበለጠ ወደ መድኅኑ እንዲጠጋ

አደረገው። ምንም እንኳ ሰዎቹ በግዙፍ ሊያዩት ባይችሉም ታማኙ መድኅን ከቅዱስ መንፈሱ ጋር ተከታዩን በማበረታታትና በማጽናናት ላይ ነበር።

የእሳቱ ነበልባል መላ ሰውነቱን አሰበሰው። ሕይወቱ እየደከመች ሄደች። መንፈሱም ወደ ዘላለም ዕረፍትዋ ለመግባት ትዘጋጅ ጀመር።

በመጨረሻውም ሥቃዩ ኃይሉን ሊቀንስበት ሞከረ።

ጥርሱን ነክሶ የመጨረሻ ሥቃዩን ለመቀበል ቈረጠ። እጆቹን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ በመጠኑ አርገበገበ። ተጣጥሮም የሚከተለውን ቃል ተነፈሰ።

‹‹ድል!››

ከዚህ ቃል ጋር ነፍሱ ከሥጋው ተለየች። በእሳቱ ነበልባል ላይ በግንባሩ ተደፋ። የማርሴሉስ ነፍስ ከሁሉ ይልቅ ከሚሻለው ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ዐረገች።

# ሉኩሉስ

«የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው።»

በዚያ ትርኢት ላይ የተፈጸመውን ሥቃይና ሞት በሐዘን በመመልከት ዓይኖቹን ከማርሴሉስ ላይ አንድ አፍታ እንኳ ያላነሣ÷ የሁኔታውን ዝርዝር በአእምሮው ውስጥ የቀረፀ÷ በአደባባዩ ውስጥ የተነገሩትን ቃላት ልቅም አድርጎ የሰማ አንድ ተመልካች ነበር። አደባባዩን የሞሉት ሰዎች ከዚያ ታላቅ ሕንፃ ውስጥ አንድ በአንድ እየወጡ ወደ መጡበት ሲመለሱ እርሱ ብቻ መቀመጫውን እንደ ያዘ ቀረ። ብዙ ከቆየ በኋላ ተነሥቶ መንገዱን ቀጠለ።

እርምጃው ሁሉ እንደ ወትሮው የፈጠነና የቀለጠፈ አልነበረም። ዐቅሉ ጥሎት ሄዶአል። አስተያየቱ ታሞ የተነሣ አስመስሎታል። በአቅራቢያው የሚገኙትን ጠባቂዎች ከጠቀሳቸው በኋላ ወደ አደባባዩ የሚገባውን በር ከፈቱለት።

ከዘበኞቹ አንዱን የሙታን አመድ ማስቀመጫ የሚሆን ዕቃ እንዲያመጣለት አዘዘው። ቀጥሎም በመጥፋት ላይ ወዳለው እሳት ተጠጋ።

ከዚያም ሊያገኝ የቻለው ጥቂት ከእሳት የተረፉ አፅሞችን ነበር። የቀረው የማርሴሉስ ቅሬታ ሁሉ አመድ ሆኖ ነበር።

ሉኩሉስም ዘበኛው ባመጣለት ዕቃ ውስጥ የማርሴሉስን ቅሬታና አመድ በጥንቃቄ አስቀመጠ። ከአደባባዩም ወጥቶ ሊሄድ ሲል ከአንድ ዕድሜው ገፋ ካለ ሰው ጋር ተገናኘ።

ሉኩሉስም ትሕትና በተመላበት አኳኋን፦

«ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?» አለው።

«እኔ የክርስቲያኖች ማኅበር ሽማግሌ ሖኖሪዮስ እባላለሁ። በዛሬው ቀን በዚህ ስፍራ ውስጥ አንድ የቅርብ ወዳጄ ተገድሎአል። እዚህ ድረስ የመጣሁት የሟቹ ወንድማችንን ቅሬታ ለመውሰድ ነው።»

ሉኩሉስም፦ «ከእኔ ጋር በመገናኘትህ በጣም ዕድለኛ ነህ» አለው። «ስምህን ለሌሎች ሰዎች ነግረህ ቢሆን ኖሮ በአንድ አፍታ በተያዝህ ነበር። አንተን ይዞ ያቀረበ ሽልማት እንደሚሰጠው ታውጆአል። የሆነ ሆኖ የለመንከውን ለማድረግ የምችል አይመስለኝም። እርግጥ ነው ማርሴሉስ በዛሬው ቀን በሞት ተለይቶአል። አመዱና አፅሙም እኔው ዘንድ ይገኛል። በዘመዶቹ መቃብር መካከል በክብር እንዲያርፍ ወስኜአለሁ። ማርሴሉስ የልብ ወዳጄ ነበር። ሞቱ ምድርን ባዶ÷

ሕይወቱን ከንቱ አድርጎታል፡፡››

ሖኖሪዮስም መልሶ እንዲህ አለ፥ ‹‹አንተ በመላም ሉኩሉስ ሳትሆን አትቀርም፡፡ ማርሴሉስ አንድ ቀን እንኳ ከአፉ ለይቶህ ዐያውቅም፡፡ ለአንተ የነበረው ፍቅር እጅግ የላቀ ነበር፡፡››

‹‹እርግጥ ነው እኔ ሉኩሉስ ነኝ፡፡ የሁለታችን ጓደኝነት የመሰለ ከዚህ ቀደምም አልነበረም፤ ወደፊትም ይኖራል ብዬ አላምንም፡፡ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ነፍሱን ከማንኛውም ዓይነት አደጋ ለማዳን ዝግጁ ነበርኩ፡፡ ራሱን ለሕግ አሳልፎ ባይሰጥ ኖሮ ለመታሠር አይችልም ነበር፡፡ የሚያሳዝን ዕድል ገጠመው፡፡ እንዳይያዝና እንዳይታሰር ልዩ ጥረት በማደርግበት ጊዜ በድፍረት ቄሣሩ ያለበት ድረስ መጣ፡፡ እኔም ያንን የምመወደውን ጓደኛዬን ይገፍ አሣሠርኩት፡፡ የመጨረሻውም ሁኔታው እንዲህ አሳዛኝ ሆኖ ቀረ፡፡››

‹‹ለአንተ አሳዛኝ መስሎ የሚታይህ አሟሟት ለእርሱ ፍጹም ደስታው ነው፡፡ እርሱ የዘለዓለማዊው ፍሥሐ ወራሽ ሆኖአል፡፡››

ሉኩሉስም፥ ‹‹ሞቱ የድል ሞት ነበር›› ሲል መሰከረ፡፡ ‹‹ብዙ ክርስቲያኖች ሲሞቱ ከዚህ ቀደም የዓይን ምስክር ሆኜአለሁ፡፡ ተስፋቸውና ድፍረታቸው እንዳሁን ልቤን ነክቶት ዐያውቅም፡፡ ማርሴሉስ ሞትን እንደ አንድ ታላቅ በረከት አድርጎት ነበር፡፡››

‹‹እርሱ ብቻ ሳይሆን በምንኖርባቸው አሠቃቂ ዋሻዎች ውስጥ የተቀበሩት ሰማዕታት ሁሉ የሞትን ሸለቆ የተሻገሩት በደስታና በምስጋና ነው፡፡ የማርሴሉስ ቅሬታ ከእነርሱ ጋር የክብር ስፍራውን እንዲይዝ እፈልጋለሁ፤ ልትሰጠኝ ትፈቅዳለህ?››

‹‹የተወደድህ ሖኖሪዮስ ሆይ፥ ምንም እንኳ እንደዚያ የምወደው ጓደኛዬ በሞት ቢለየኝም ለአስከሬኑ የሚገባውን ሥርዓት በማድረግ በመቃብሩ ላይ ለማልቀስ ወስኜአለሁ፡፡››

‹‹የተከበርክ ሉኩሉስ ሆይ፥ ጓደኛህ በዐዲሱ እምነቱ መሠረት የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ቢፈጸምና ስሙም ከቀደሙት ሰማዕታት ስም ጎን ተቀርፆ ቢያርፍ የሚመርጥ አይመስልህም?››

ሉኩሉስም ምንም ሳይናገር ለጥቂት ጊዜ ቆየ፡፡

በመጨረሻውም እንዲህ አለ፦

‹‹አንተ ያልከውን እንደሚመርጥ ምንም አልጠራጠርም፡፡ እኔም ምኞቱን ለማስተጓጎል አልፈቅድም፡፡ አስቤው የነበረውም የቀብር ሥነ ሥርዓት ይቅር፡፡ ሖኖሪዮስ ሆይ፥ ይኸውልህ ውሰደው ዳሩ ግን አንድ

ነገር የምለምንህ አለኝ። እንደ ጠላታችሁ የምትመለከቱትን ወታደር ሥነ ሥርዓታችሁን እንዲመለከት ትፈቅዱለታላችሁ?››

‹‹አዎን ሉኩሉስ፥ ማርሴሉስን እንደ ተቀበልን አንተንም በሰላም ለመቀበል የተዘጋጀን ነን። ምናልባት ማርሴሉስ የተቀበለው በረከት ለአንተም ይደርስህ ይሆናል።››

ሉኩሉስም መልሶ፥ ‹‹ከቶ እንዳይመስልህ›› አለው። ‹‹እኔና ማርሴሉስ አንድ አይደለንም። እኔ ከእርሱ በብዙ ዓይነት መንገድ የተለየሁ ነኝ። ከእናንተ ጋር መገናኘቴ በበለጠ ሁኔታችሁን እንድረዳና እንዳዝንላችሁ ያደርገኝ ይሆናል። ከእናንተ ጋር አንድ ለመሆን ግን ፈጽሞ አልሞክረውም።››

‹‹ምንም ዓይነት ሰው ብትሆን ግድ የለንም። ለጓደኛህ በምናደርግለት ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት ብትችል በጣም ደስ ይለናል። ነገ ወዳለንበት ስፍራ የሚያደርስህን መልእክተኛ እንልክልሃለን።››

ሉኩሉስም ክርስቲያኖች ወደሚኖሩበት ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ መሆኑን ከገለጸና የማርሴሉስን ቅሬታ ለሖራሪዮስ ካስረከበ በኋላ ወደ ሰፈሩ ተመለሰ።

በማግሥቱም ከተላከለት መልእክተኛ ጋር ወደ ካታኮምቡ ሄዶ የክርስቲያኖችን ኑሮና የሚኖሩበትን ስፍራ ሁኔታ በቅርብ ለመመልከት ቻለ። የስፍራው ሁኔታ የክርስቲያኖች ሥቃይና ችግር ከዚህ ቀደም ማርሴሉስ እንዳስረዳው ሆኖ አገኘው። በዋሻው ውስጥም የአንድን ምእመን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የሚያበሥር የልቅሶና የሐዘን ድምፅ ተሰማ።

ከዚህ በቀር የምእመናን ነፍስ በዘለዓለማዊው ሕይወት የሚጠብቃት የደስታና የብፅዕና የምሥራች በግልጽ ታወጀ። ሖራሪዮስም የተከበረውን የብራና ጥቅል አንሥቶ በጭንቀትና በመከራ ቀን የታላቅ መጽናናት ምንጭ የሆነውን ክፍል ከመጀመሪያ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች አነበበ።

ይህም ክፍል ትውልድ አልፎ ትውልድ በሚተካበት ጊዜ ሁሉ የትንሣኤን የምሥራች በማብሠር የምእመናን የተስፋ መልሕቅ ሆኖአቸዋል።

ሖራሪዮስም እጆቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ ሞትንና መቃብርን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አማላጅ በሆነው በክርስቶስ ላሸነፈው ሕያውና ቅዱስ አምላክ ልባዊ ጸሎቱን አቀረበ።

ሉኩሉስ ለጓደኛው ከልብ ያዘነ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር።

ምንም እንኳ ከክርስቲያኖች እንደ አንዱ ባይሆንም ግሩም የሆነ ትምህርታቸውንና ታላቁን ተስፋቸውን ማድነቁ አልቀረም። የማርሴሉስን ቅሬታዎች በመጨረሻው የማረፊያ ስፍራው ውስጥ ያስቀመጠ÷ ስሙንና መታሰቢያውን በመቃብሩ አጠገብ የሰቀለ ሉኩሉስ ነበር።

ሉኩሉስም ከካታኮምቡ ውስጥ ሁኔታው ሁሉ ተለውጦ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ። በጓደኛው ሞት ምክንያት የተሰማው ሐዘን የቀድሞ ብሩሕ ገጹን አጥቁሮት ነበር።

ሉኩሉስ «ክርስቲያን ፈጽሞ አልሆንም» ብሎ ለሖኖሪዮስ የተናገረው የምሩን ነበር። የጓደኛው ሞት ልቡን በሐዘን ከማንሳቀሉ በቀር በኃጢአት የመጸጸት፤ ንስሐ የመግባትና እውነተኛውን አምላክ የማወቅ ፍላጎት አላሳደረበትም። እንደ ቀድሞው በዓለም መደሰቱን ቢተውም በምትኩ ደስታ የሚሰጥ ነገር አላገኘም ነበር።

የሆነ ሆኖ የጓደኛው መታሰቢያ አንድ ስሜት ሳይፈጥርበት አልቀረም። ማርሴሉስ ለተጠጋቸውና በስደት ውስጥ ለሚንገላቱት ክርስቲያኖች የነበረው ርኅራኄ እየጠነከረ ሄደ። ለጽናታቸው የነበረው አድናቆት፤ በማይገባ አኳኋን በሚደርስባቸው ጭቆና ይሰማው የነበረው ሐዘን ሥር ሰደደ። በሮም የተረፈው እውነት፤ ደግነትና ጨዋነት ከእነዚህ ምስኪኖች ዘንድ መሆኑን ተገነዘበ።

እነዚህም ስሜቶች ዋና የክርስቲያኖች ረዳት አደረጉት። ከዚህ ቀደም ለማርሴሉስ ሰጥቶት የነበረውን ተስፋ በማስታወስ ክርስቲያኖችን በተቻለ መጠን ለመርዳት ቆርጦ ተነሣ። ወታደሮቹም ክርስቲኖችን እንዳያሥሩ አዘዘ። የታሠሩትም በልዩ ልዩ ምክንያት እንዲያመልጡ አደረገ። ክብሩን÷ ሥልጣኑንና ሀብቱን የችግረኞች ክርስቲያኖችን ሥቃይ ማቃለያ አደረገው። ክርስቲያኖችም ወዳጅነቱን በመገንዘብ መኖሪያ ቤቱን ያዘወትሩና ስሙን ያከብሩ ጀመር።

ማንኛውም ነገር ማለፉ ስለማይቀር ማርሴሉስ በሞተ በዓመቱ ዶሊክዮስ ከዙፋኑ ወርዶ ሌላ ቄሣር በስፍራው ተተካ። የክርስቲያኖችም መከራና ስደት ፍጻሜ አገኘ። ከካታኮምቡ ዋሻዎች ወጥተው በሰላምና በጸጥታ የፀሐይ ብርሃንና ንጹሕ አየር በሚገኝበት ቦታ ለመኖር ቻሉ። ለአዳኛቸውና ለጠባቂያቸው የሚያሰሙት ምስጋና በየማዕዘኑ መሰማት ጀመረ። ከክፉው ሠራዊት ጋር የሚያደርጉትን ውጊያ በገሀድ ቀጠሉ።

ብዙ ዓመታት አለፉ። ዳሩ ግን በሉኩሉስ ሕይወት ውስጥ ምንም ለውጥ ሳይታይ ቀረ። ሖኖሪዮስ ከካታኮምቡ ውስጥ እንደ ወጣ ሉኩሉስ ተቀብሎ በቤቱ ውስጥ እየጦረ አስቀመጠው። እርሱም በበኩሉ በትጋት

የክርስቶስን እምነት ያስረዳው ነበር። ዳሩ ግን ሉኩሉስን ወደ ክርስትና እምነት ሊመልሰው ሳይችል ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

የማርሴሉስና የሖኖሪዮስ ድካም ከንቱ ሆኖ አልቀረም። ሉኩሉስም በመጨረሻው የዓለምን ከንቱነት እየተረዳው ሄደ። ክብር÷ ሥልጣንና ሀብት ፍጹም የሆነ ደስታ ሊሰጠው የማይችል መሆኑን ተረዳ። በሽምግልና ዘመኑም ሕይወቱን ለክርስቶስ አሳልፎ ሰጠ። የእግዚአብሔርም ቅዱስ መንፈስ በክርስቶስ ደኅንነት ልቡ እንዲረካ አደረገው። ከዚህ ቀደም ያየው ነገር ሁሉ ለልቡ ጽናት ሰጠው።

የሮም ቄሣሮች ክርስቲያኖችን በዚያ አሠቃቂ በሆነው ካታኮምብ ውስጥ እንዲኖሩ ካስገደዱአቸው አያሌ ሙቶ ዘመናት አልፈዋል። እስቲ በአፒያ አንቲካ ጎዳና ላይ ቆመን ሁኔታውን እንመልከት። በፊታችን የሚታየው የመቃብሮች ሰልፍ እስከ ከተማይቱ ድንበር ድረስ ይደርሳል። ይህም አንድ ጊዜ የሮም ኃያላን ማረፊያ ስፍራ ነበር። በሕይወታቸው ዘመን ሳሉ የነበራቸውን ክብርና ብልጽግና በመቃብራቸው ውበትና በመታሰቢያቸው ጽሕፈት ለመረዳት ይቻላል። ከቆምንበት ስፍራ ሥር ከምድር በላይ የሚገኘውን አየር እንዳይተነፍሱ የተከለከሉት ክርስቲያኖች መቃብር ይገኛል።

አሁን ግን ሁሉም እንዳልነበረ ሆኖአል። ከዚህ ቀደም በግርማቸው የተደነቁት መቃብሮች ክብራቸው ተዋርዶ÷ ሕንፃቸው ፈርሶ ከአፈር ጋር ተቀላቅሎአል። ትቢያቸውም በአራቱ ማዕዘናት በኖ ጠፍቶአል። የብዙዎቹም ስም ተረስቶአል። የመሠረቱትም ታላቅ መንግሥት ወድቆአል። ያዙት የነበረውም ሠራዊት በየስፍራው ተበትኖ ቀርቶአል።

እነዚያ ከምድር ገጽ ተባረው በምድር ማኀፀን ውስጥ እንዲያርፉ የተገደዱት ክርስቲያኖች መታሰቢያ ግን እስከ ዘመናችን በታላቅ አክብሮት ተጠብቆ ይገኛል። ብዙ ምእመናን ከአራቱ ማዕዝነ ዓለማት እየመጡ ይጐበኙታል፤ ያደንቁታልም። ይህም በካታኮምቡ ዋሻ ውስጥ የሚገኘው የቀደሙት ሰማዕታት ማረፊያ የሆነው ስፍራ እስከ ጌታ መመለስ ድረስ እንደ ተከበረና ትውልድ እንዳደነቀው ይኖራል።

እነዚያ የተናቁት÷ የተጠሉትና የተሰደዱት ምእመናን ስማቸው በታሪክ ገጽ ላይ እንዲውል የሚያደርግ ዝና አልነበራቸውም። ዳሩ ግን የተከበረ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተመዘገበ የታወቀ ነው።

ክፍላቸውም የሚከተሉት ቃላት ከተነገሩላቸው ቅዱሳን ጋር መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

‹‹እነዚህ ከታላቅ መከራ የመጡ ናቸው
ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ
ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ
ሌሊትና ቀንም በዙፋኑ ፊት ያመልኩታል
በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው
በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።
ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሙም
ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ አይወርድባቸውም
በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናል
ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋል
እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ
ከዓይናቸው ያብሳል።››

# ከመጽሐፉ የተወሰዱ

የእናንተ የክርስቲያኖች ድፍረትና ቈራጠኝነት ዘወትር ይደንቀኛል። እምነታችሁን በልባችሁ ውስጥ ይዛችሁ ለይምሰል ብቻ የቄሣርን አዋጅ ብታከብሩ ምን አለበት? ሞትን በገዛ እጃችሁ ለምን ትፈልጋላችሁ?

መድኃኒታችን ለእኛ ሲል ሞቶአል። እኛም ለእርሱ ስንል ለመሞት ዝግጁዎች ነን። እርሱ ለወገኖቹ እንደ ሞተ እኛም ፍለጋውን በመከተል ለወንድሞቻችን ስንል ለመሞት ቍርጠኞች ነን።

እሳቱ ተቀጣጠለ። ለጥቂት ጊዜም ጀግናው ሰማዕት በጢሱ ውስጥ ተሠወረ። ጢሱ እንደ ተወገደ ራሱን ወደ ሰማይ አቅንቶ እጆቹን ጭብጥ አድርጎ እንደ ቆመ ታየ።

የእሳቱ ነበልባል እየቀረበው ሄደ። የእሳት ምላስ ከበበው። ጢሱ ጠቈረ። የነበልባሉም ወላፈን ይገርፈው ጀመር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሰማዕቱ ማርሴሉስ ፍንክች ሳይል እንደ ቆመ ይታይ ነበር። ጭንቀቱና መከራው በበለጠ ወደ መድኀኑ እንዲጠጋ አደረገው። ምንም እንኳ ሰዎቹ በግዙፍ ሊያዩት ባይችሉም ታማኙ መድኀን ከቅዱስ መንፈሱ ጋር ተከታዩን በማበረታታትና በማጽናናት ላይ ነበር።

የእሳቱ ነበልባል መላ ሰውነቱን አለበሰው። ሕይወቱ እየደከመች ሄደች። መንፈሱም ወደ ዘላለም ዕረፍትዋ ለመግባት ትዘጋጅ ጀመር። በመጨረሻውም ሥቃዩ ኃይሉን ሊቀንስበት ሞከረ።

ጥርሱን ነክሶ የመጨረሻ ሥቃዩን ለመቀበል ቈረጠ። እጆቹን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ በመጠኑ አርገበገበ። ተጣጥሮም የሚከተለውን ቃል ተነፈሰ።

ድል!

እንዚያ ከምድር ገጽ ተባረው በምድር ማኅፀን ውስጥ እንዲያርፉ የተገደዱት ክርስቲያኖች መታሰቢያ ግን እስከ ዘመናችን በታላቅ አክብሮት ተጠብቆ ይገኛል። ብዙ ምእመናን ከአራቱ ማዕዘን ዓለማት እየመጡ ይጎበኙታል፤ ያደንቁታልም። ይህም በካታኮምቡ ዋሻ ውስጥ የሚገኘው የቀደሙት ሰማዕታት ማረፊያ የሆነው ስፍራ እስከ ጌታ መመለስ ድረስ እንደ ተከበረና ተውልደ እንዳደነቀው ይኖራል።